መፈወስ በጣም አስቸጋሪ ይሆናል::

ሁለተኛ፣ ባለመግባባቱ ውስጥ የሚሳተፉት ሰዎች ቁጥር ይጨምርና በሰዎች መካከል ሰላም ማምጣቱ በጣም አስቸጋሪ ይሆናል:: ባልና ሚስት ሲጣሉ፣ ሰዎች እንዲራሩላቸው ለማድረግ ሲሉ ጉዳታቸውን ለሰው ማውራት ይጀምራሉ:: ስለዚህ ልጆቻቸው ከእነርሱ ጐን እንዲቆሙ ይገፋፋሉ:: ከዚህ የተነሣ ቤተሰቦቻቸውን ችግሩ ውስጥ ያስትታሉ:: ከዚያም ችግሩን ለጓደኞቻቸው ስለሚያማክሯቸው፣ ጓደኞቻቸውም ከጐናቸው ይቆማሉ:: አሁን መሪው ሰላም ማምጣት ያለበት በባልና በሚስት መካከል ብቻ ሳይሆን፣ በችግሩ ውስጥ በተሳተፉት ወገኖች መካከል በሙሉ ነው::

ሦስተኛ፣ ግጭቱ በተራዘመ ቁጥር፣ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ከመድረሱ በፊት ችግሩን መፍታት አስቸጋሪ ይሆናል:: አትክልቱን ሳይጐዱ ገና ያቆጠቆጠን አረምን መንቀል በጣም ቀላል ነው:: ነገር ግን ያ አረም የተክሉን ያህል ካደገና ሥሩ በጥልቀት ካደገ፣ አረሙን መንቀል አትክልቱን ይጐዳዋል:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ አንድ ጊዜ አለመግባባት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከተስፋፋ፣ መሪው አንዱ ወገን ፍትሐዊ እንዳልሆነ በማመን እርቁን እምቢ ስለሚል አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል::

ይህ ማለት መሪዎች በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ሰላም ከፈለጉ፣ ሰላም በማምጣት ላይ በንቃት ሊሳተፉ ይገባል:: አለመግባባቶችን ልንቆጣጠርና አለመግባባቱ ከመስፋፋቱ በፊት እርቅ ለመፍጠር አፋጣኝ እርምጃ ልንወስድ ይገባል:: በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በሳል የሆኑ መሪዎች እግዚአብሔር ሰላምን ለማምጣት ጣልቃ እንዲገቡ እንደሚፈልግ ያውቃሉ:: በችግሩ ላይ መጸለይ ብቻ እንዳልሆነ ያውቃሉ:: ኃጢአትን ልንጋፈጠውና የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ዳግም ጤነኛ እንድትሆን ሰላም መስፈን አለበት::



9ኛ ጥያቄ:- ሀ) በመሪዎች መካከል መከፋፈል የሚፈጠረው እንዴት እንደ ሆነ አብራራ:: ይህ ሲፈጠር ሰላም አምጪው ምን ሚና ሊኖረው ይችላል? ለ) በቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል መከፋፈል የሚፈጠርባቸውን ምሳሌዎች ስጥ:: ሰላም የሚያመጣ ሽማግሌ የሚጫወተው ሚና ምንድን ነው? ሐ) ልዩነቶች ሲፈጠሩ በቶሎ አለመፍታት እንዴት ችግሩን ለመፍታት አስቸጋሪ እንደሚያደርገው ግለጽ:: መ) አብዛኛዎቹ ሽማግሌዎች ችግሩን ቶሎ ለመፍታት ጥረት ውስጥ የማይገቡት ለምን ይመስልሃል? ሠ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የምታውቃቸው አንዳንድ ልዩነቶች ምን ምን ናቸው? ሰላምን ለማምጣት እግዚአብሔር ምን ዓይነት ሚና እንዲያመጣ ይፈልጋል:

## 9. ነገሮች ከሚገባው በላይ የሚሰማው ሰው አለመሆን:- ቅያሜንና ነቀፋን መቀበልን መማር::

በብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነገሮች እነርሱ በሚፈልጉት መንገድ ካልሆኑ ስሜታቸው በጣም ስስ ስለሆነ በቀላሉ ይጐዳሉ:: ለምሳሌ፣ አንድ ሰው ሰላም ሳይላቸው ካለፈ፣ ያ ሰው አይወደኝም ብለው ያስባሉ:: ወይም ከሌላ ብሔር የሆነ ሰው ስብሰባ ከቀረ፣ ሰውየው ያንን ያደረገው የእርሱን ብሔር ስለማልወደው ነው ብለው ያስባሉ:: በጣም በቀላሉ የሚሰማው (የሚቀየም) ሰው መሆን መሪዎችን በተለያዩ መንገዶች ምላሽ እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል:-

ሀ. መሪው በጣም ቁጥጥር ያበዛል:: ብዙ ጊዜ መሪዎች ቁጥጥር ሲያበዙ፣ ያንን የሚያበዙት ለራሳቸው ዋስትና ስለሌላቸውና በእግዚአብሔር ስለማያምኑ ነው:: ሰዎች እነርሱ የማይፈልጉትን ነገር ያደርጋሉ ብለው በመፍራት፣ ብዙ መሪዎች ውሳኔውን ሁሉ ሌሎች ሰዎችን ሳያሳትፉ ይወስናሉ:: ወይም ከእነርሱ በተሻለ ሁኔታ መስበክና ማስተማር የሚችል ሰው ይመጣል ብለው ስለሚፈሩ፣ ሌሎች ሰዎች እንዳያገለግሉ በማድረግ የተቀቡ ወጣቶችን ያባርራሉ:: መሪዎች ይበልጥ ዋስትና የሚሰማቸው በእግዚአብሔር መታመንን በመማር ነው:: የእግዚአብሔርን ክብር ይፈልጋሉ፣ ስለዚህ ማን ለስኬት በቃ

ወይም ክብርን አገኘ የሚለው ነገር እያሳሰባቸውም። እግዚአብሔር በማንኛውም ሰው እንደሚሠራ ያውቃሉ፣ ስለዚህ ሕዝቡ ሕዝቡ በእግዚአብሔር እንደሚመራና እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር እንደሚያደርግ ያምናሉ። የራሳቸውንና የሌሎች ሰዎችን ስጦታ ያውቃሉ። ስለዚህ እነርሱ የሚበረቱበትን ነገር በማድረግ ሌሎች እግዚአብሔር በሰጣቸው ስጦታ እንዲሠሩ ነፃ ያደርጓቸዋል።

ለ. አንዳንድ መሪዎች በአገልግሎታቸው ላይ በሚሰጥ በማንኛውም ዓይነት አስተያየት ይጐዳሉ። አንድ ሰው በእነርሱ እሳብ ካልተስማማ፣ በእነርሱ ላይ እንደ ተቃጣ ጥቃት ይመለከቱታል። ወይም አንድ ሰው የሚያደርጉትን ከተቸ፣ በጣም በማማረር አብዛኛውን ጊዜ ሰውየውን በቃላት ማጥቃት ወይም ማማት ይጀምራሉ። ሰዎች ሁልጊዜም መሪዎችን ይተቻሉ። ትችት የማይቀር ስለሆነ፣ እንደ መሪነታችን እንዴት እንደምንይዘው ማወቅ አለብን። የሚከተሉትን ማስታወስ ይረዳናል፡-

1) ትችት በሚሰጥብህ ሰው ላይ መቆጣት አይጠቅምም። ለመቆጣትና ለማማረር የምትፈቅድ ከሆነ፣ ዳግም እንድትጐዳ ፈቅደሃል ማለት ነው፣ ከሰውየው ተምረህ ክርስቶስን ወደ መምሰል ማደግ ሲገባህ ችግሩ እያደገ ይሄዳል።

2) ተጠሪነትህ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሕዝቡ አለመሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል። በመጨረሻ፣ አስፈላጊው እነርሱ ያሉት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ያለው ነው። የእርሱ ፍርድ ብቻ ለውጥ ያመጣል። እርሱ የሚፈልገውን ማድረግ ከፈለግን፣ የእኛን ውሳኔ የማይወድዱ ሰዎችን ትችት ችላ ማለት አለብን።

3) ራስህን «ከዚያ ትችት ውስጥ እውነት የሆነና ንስሐ መግባት የሚገባኝ ነገር አለ?» ብለህ ጠይቅ። ከብዙ ውሸቶች መካከል፣ ትንሽ እውነት ሊኖር ይችላል። ስለዚህ የተባልካቸውን ነገሮች ሁሉ በተጨባጭ መርምር። በተሻለ ሁኔታ መሥራት የምትችልባቸው መንገዶች ካሉ ወይም ሁኔታዎችን በተሻለ ሁኔታ



መያዝ የምትችልበት ሁኔታ ካለ ተቀበልና ከዚያም ለመማር ሞክር። የተሳሳተ አመለካከት እንዳለህ ከተረዳህ ወይም የተሳሳተ ነገር ካደረግህ፣ እነዚያን ነገሮች ለእግዚአብሔርና ለሌሎችም ለሚመለከታቸው ተናዘዝ።

4) የተሳሳተ ነገር ከተወራብህ ትኩረት ላለመስጠት ወስን። ብዙ ጊዜ ሰዎች ይሳሳታሉ። አንተን በተመለከተ የተሳሳተ አመለካከት አላቸው። ይህንን ተረድተህ አትናደድ።

ሐ. ብዙ ጊዜ መሪዎች በሕዝቡ ወይም ተበሩ እንዳደረጉት ነገሮች ባለመሄዳቸው ይናደዳሉ። አንተም ሰው እንደ ሆንክና ፍጹም እንዳልሆንክ አስታውስ። የምትለውን ያህል ጥሩ አድርገህ ከሠራህ፣ ያ እግዚአብሔር ከአንተ የሚጠብቀው ነው። እግዚአብሔር የሚገመግመው ውጤቱን ሳይሆን፣ ነገሩን ለእርሱ ክብር ስናደርገው በልባችን የነበረውን ምክንያት ነው። ሰይጣን እኛን ድል ከሚያደርግባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ ነገሮች እኛ እንደምንፈልገው ካልመጡ ሙከራችንን እንድናቆም ማድረግ ነው። በጣም ስኬታማ የሆኑት ነጋዴዎች በሚችሉት አቅም ሁሉ ጥሩ ዕቅድ በማውጣት አዲስ ነገር የሚያደርጉት ናቸው። ያ እልሳካ ሲላቸው፣ ሊሳካ ያልቻለበትን ምክንያት በማጥናት እንደገና ይሞክራሉ። ለምሳሌ፣ የኤሌክትሪክ አምፖልን ለመጀመሪያ ጊዜ የሠራው ኤዲሰን ከብዙ ያልተሳኩ ሙከራዎች በኋላ ነው አምፖሉን የፈለሰፈው። የመጀመሪያው ሙከራው ሳይሳካ ሲቀር ተበሩ ቆርጦ ትቶት ቢሆን ኖሮ፣ ዛሬ በዓለም ላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች የሚጠቀሙበት የኤሌክትሪክ ብርሃን ባልተፈጠረ ነበር። ስለዚህ ጥረትህን ቀጥል። ልክ እንደ ኤዲሰን እግዚአብሔር ታላቅ ነገር ለመሥራት ይጠቀምብህ ይሆናል።

10ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዋስትና አለማግኘት መሪን ሲበዛ ተቆጣጣሪ እንዲሆን እንዴት ሊያደርገው እንደሚችል ምሳሌ ስጥ። ለ) መሪዎች ሌሎችን መቆጣጠር እንዳለባቸው ከማሰብ ይልቅ ሌሎችን ማመንን ይማሩ ዘንድ ሊያስታውሷቸው የሚገቡ እንዳንድ እውነቶችን ዘርዝር። ሐ) ከትችት

*የተነሣ ሲበዛ የተጐዳና ያመረረ መሪ ምሳሌ ስጥ። ያ መሪ ትችቱን እንዴት መያዝ ነበረበት ብለህ ታስባለህ? መ) ነገሮች እንዳሰበው ካለመሆናቸው የተነሣ ተስፋ የቆረጠና ከዚያ የተነሣ ለውጥ ለማምጣት የሚያደርገውን ጥረት የተወ መሪ ካለ ምሳሌ ስጥ። ነገሮች ልክ እኛ እንዳሰብነው ባይሳኩ እንኳን ተስፋ ቆርጦ ከመተው ይልቅ ሙከራችንን መቀጠል የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?*

## ሁለተኛ ቀን፡- ለመንፈሳዊ አመራር የሚያስፈልጉ ቁልፍ ባሕርያት (ክፍል 7)

*ለስኬታማ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚያስፈልጉ ባሕርያት፡- መሪው ከሥራ ጋር ካለው ግንኙነት ጋር የሚዛመዱ ባሕርያት*

እግዚአብሔር ስለምንሠራው ነገር ብቻ ሳይሆን እንዴት እንደምንሠራውም ያሳስበዋል። ለእግዚአብሔር የምንሰጠውን አገልግሎት በትክክለኛ ወይም በተሳሳተ አመለካከት ልናደርግ እንችላለን። በ 1ኛ ቆር. 3:10-15 ላይ ጳውሎስ ሁላችንም በእግዚአብሔር ቤት ግንባታ ላይ የራሳችን ድርሻ እንዳለን ያስጠነቅቃል። አንዳንዶች በክበረ ድንጋይና ወርቅ ይገነባሉ። ሌሎች ደግሞ እንደ እንጨት፣ ገለባና ሣር ባሉ ነገሮች ይገነባሉ። የሁላችንንም አገልግሎት የሚገመግመው እግዚአብሔር ነው። አገልግሎታችን የተገነባው በክበረ ድንጋይ ከሆነ፣ ለዘላለም ይቆይልናል። ነገር ግን አገልግሎታችን ውድ ባልሆኑ ነገሮች ከተሠራ፣ ይደመሰሳል። ለእነዚያም አገልግሎቶች ዋጋ አናገኝም። በውድ ዕቃ በተሠራውና ለዘላለም በሚቆየው እና ውድ በሆነ ዕቃ የተሠራውና በሚደመሰሰው መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? <u>አንደኛ</u>፣ በሰጠን ጸጋና ስጦታ መጠቀም አለመጠቀማችንን ይገመግማል። እርሱን ለማገልገል እነዚህን ጸጋዎችና ችሎታዎች ካልተጠቀምን፣ የጌታውን ገንዘብ እንደ ደበቀው ባሪያ ሽልማትን አናገኝም። (ማቴ. 25:14-30ን ተመልከት።) <u>ሁለተኛ</u>፣ ኢየሱስ አንድን ነገር «ለምን» እንደምንሠራ ይመረምራል። የምንሠራው በተሳሳተ አመለካከት ከሆነ፣ ማለትም ለኢየሱስ ክብርን ከማምጣት



ይልቅ ለራሳችን ክብር የምናገለግል ከሆነ፣ ሽልማትን አናገኝበትም። <u>ሦስተኛ</u>፣ ነገሮችን «እንዴት» እንደምናደርግ እንገመግማለን። በምንችለው የመጨረሻ አቅም ካልሠራን፣ አገልግሎታችን ሽልማትን አያገኝም። አንድ መሪ እግዚአብሔር እንዲጠቀምበት ከፈለገ አገልግሎቱን በተመለከተ የተስተካከለ አመለካከትን መማር አለበት።

### 1. ልቀት (ምርጥ የሆነ ነገር መሥራት)፡- በምንችለው አቅም ሁሉ ምርጥ አድርገን የመሥራት ባሕሪ።

*11ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንድን ነገር በግማሽ ልብ በአነስተኛ ጥረት በመሥራትና በምንችለው አቅም ሁሉ ተረባርበን በጥሩ ሁኔታ በመሥራት መካከል ያለውን ልዩነት ግለጥ። ለ) አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጥራት ላይ ከማተኮር ይልቅ ሥራውን በመሥራት ላይ ብቻ እንዴት እንደሚያተኩሩ ግለጥ። ሐ) ሚል. 1:6-14ን አንብብ። እግዚአብሔር ካህናቱን የሚከስሳቸው ምን በማድረግ ነው? ይህ ነገር አንድን ነገር ምርጥ አድርጎ ካለመሥራት ጋር ምን ያገናኘዋል?*

በሚልክያስ ዘመን፣ መሪዎች እግዚአብሔርን የሚያመልኩት በግድ የለሽነት ነበር። በገበያ ውስጥ በጥሩ ዋጋ ሊሸጡ የማይችሉ ሽባና እንካሳ እንስሳትን ይሠዉ ነበር። «እግዚአብሔር በምንሰጠው ስጦታ ሁሉ ይረካል፣ ስለዚህ የከሱትንና ሽባ የሆኑትን ልንሠዋለት እንችላለን» ብለው ያስባሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር ለአይሁዳውያን በእነርሱ አመለካከት እንደ ተሰደበ ነው የነገራቸው። ለመንግሥት ባለ ሥልጣናት ምርጥ ያልሆነውን ነገር አይሰጡም። ታዲያ ለምንድን ነው ምርጥ ባልሆነ መሥዋዕት እግዚአብሔር የሚረካ የመሰላቸው? ከሁሉም በላይ ምርጥ መሪ አይደለምን? የሰማይና የምድርን ጌታ ልናከብረው አይገባምን?

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር የሚረካው አንድን ነገር በምንችለው አቅም ስናደርገው እንደ ሆነ ልናስተውል ይገባል። ችሎታ ከሰው ሰው ይለያያል። ሆኖም፣ እግዚአብሔር እያንዳንዳችን በምንችለው አቅም እንድንሠራ ይጠብቅብናል። የልቀትን (ምርጥ

እድርጎ የመሥራትን) ባሕሪ ልናዳብር ይገባል፡፡ አገልግሎታችንን በምንችለው አቅም ምርጥ እድርገን ብንፈጽም ነው እግዚአብሔርን የምናከብረው፡፡ ይህም ማለት ስንሰብክ፣ በሚገባ መዘጋጀት አለብን፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት መተርጐም እንዳለብን ለመረዳት በጥንቃቄ ማጥናት አለብን፡፡ መልእክታችንን ሰዎች በግልጽ መረዳት እንዲችሉ አሳባችንን ማቀናበር አለብን፡፡ ለጆሮ የሚጥሙ መልካም ቃላትን እንመርጣለን፡፡ ወይም በመዘምራን ቡድን ውስጥ ካለን ወይም የሙዚቃ መሣሪያ የምንጫወት ከሆነ፣ ሁሉም ሰው በአንድ የድምፅ ከፍታ ጥሩ አድርጐ እንዲዘምር ወይም ትክክለኛ የሆኑ ኅብረ ድምጾችን ለማግኘት መጣር አለብን፡፡ ወይም እንደ ቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ያዥ እያንዳንዱ ገንዘብ በምን ላይ እንደ ዋለ ልንመዘግብ ይገባል፡፡ በበቂ ሁኔታ አለመዘጋጀት እግዚአብሔርን መስደብ ነው፣ ምክንያቱም ያለንን ምርጥ ነገር ባለማቅረባችን ነው፡፡ እግዚአብሔር የሚጠቀምበት መንፈሳዊ መሪ መሆን ከፈለግን፣ የምናደርገውን ሁሉ በምንችለው አቅም ምርጥ አድርገን ለመሥራት መስጠት አለብን፡፡

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በአገልግሎትህ ለእግዚአብሔር የምታደርገውን ነገር ዘርዝር፡፡ ለ) ዝርዝሩን ቃኝና እያንዳንዳቸውን በምትችለው አቅም ሁሉ ምርጥ አድርገህ መሥራት አለመሥራትህን ገምግም፡፡ ካልሆነ፣ ይህንን ኃጢአት ለእግዚአብሔር ተናዘዝ፡፡ ሐ) የምትሠራውን ነገር በሙሉ ምርጥ አድርገህ ብትሠራ አገልግሎትህ በምን ዓይነት ሁኔታ ይለወጣል? |

**2. መልካም ነገር ተስፋ ማድረግ፡- እግዚአብሔር ነገሮችን መልካም እንደሚያደርግ የማመን ችሎታ፡፡**

ሁለት ዓይነት ሰዎች አሉ፡፡ ነገሮችን አይተው ምንም ተስፋ የማይታያቸው ሰዎች አሉ፡፡ እነርሱ ጨለምተኞች ይባላሉ፣ የሚያስቡት ሁሉ ነገሮች መጥፎ እንደሚሆኑ ነው፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ፣ አብዛኛዎቹ ሰዎች፣ አብዛኛዎቹ መሪዎችም እንኳ እንደዚህ ናቸው፡፡ አንድን ነገር ለእግዚአብሔር ምርጥ አድርጐ ለለ መሥራት ሲወራ፣ ነገሩ ሊሠራ የማይችልባቸውን በሙቶ



ጥሩ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን በአስተዳዳሪነት ይሾማል፡፡ ከዚያ በኋላ ግን ሽማግሌዎች ስውየው በአገልግሎቱ ለምን ደስተኛና ውጤታማ እንዳልሆነ ይገረማሉ! ይህንን ስናደርግ መንፈስ ቅዱስን እየተቃረንን ነው፡፡ የሰዎችን መንፈሳዊ ስጦታዎች የሚወስነው መንፈስ ቅዱስ ከሆነ፣ ለእርሱም ፍላጐት መገዛትና ሰዎችን እርሱ በሚፈልገው አገልግሎት ማስቀመጥ አለብን፡፡ እርሱ ብዙ ጊዜ ፍላጐቱን የሚገልጠው አንድን ሰው ለዚያ አገልግሎት በመቀባት ነው፡፡

ለ. መንፈሳዊ ስጦታዎቻችንን መረዳት በተለያዩ መንገዶች ከተቀቡ ሌሎች መሪዎች ጋር በጋራ መሥራት ያስችለናል፡፡ ከኋላ ባሉ ትምህርቶች፣ እንደ መሪዎች እንዴት በቡድን መሥራት እንደምንችል በአጭሩ እንወያያለን፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለሰዎች የሚሰጠውን ጸጋ የሚገድበው አውቆ ነው፡፡ ያም የሆነው የትኛውም መሪ ብቻውን ቤተ ክርስቲያንን መምራት እንደሚችል እንዳያስብ ነው፡፡ እያንዳንዳችን ሌሎች ስጦታዎች ካሉዋቸው ሰዎች ጋር በጋራ መሥራት ላይ ልናተኩር ይገባል፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ሽማግሌ የአስተዳደር ስጦታ ሳይኖረው በሊቀመንበርነት ቢመረጥ፣ የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር ሥራ ከመሥራት ይልቅ፣ የአስተዳደር ስጦታ ካለው ሌላ ሽማግሌ ጋር ተቀራርቦ መሥራት ይኖርበታል፡፡ የአስተዳደር ስጦታ፣ የወንጌል ስጦታና የማስተማር ስጦታ ያላቸው ሰዎች ሲኖሩ ነው ቤተ ክርስቲያን የተመጣጠነና ለእግዚአብሔር ክብር የሚያመጣ አገልግሎት የሚኖራት፡፡

ሐ. መንፈሳዊ ስጦታዎችን ስንረዳ፣ ሰዎችን እንዴት ለመንፈሳዊ አገልግሎት እንደምንመርጥ ለማወቅ ይረዳናል፡፡ አዲስ ኪዳን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን እንዴት እንደምንመርጥና እንደምንሾም የሚሰጠው መመሪያ አነስተኛ ነው፡፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ለተለያዩ ሰዎች እንደ ፈቃዱ ጸጋን እንደሚሰጥ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ እናም ሁሉም መሪዎች ከተለያየ ስጦታቸው ጋር ለቤተ ክርስቲያን ጤናማነት አስፈላጊ ናቸው፡፡ ስለዚህ ጤናማ

አንደኛ፣ መልካምን ነገር ተስፋ ማድረግ ሊሆን የማይችል አሳብ መያዝ አይደለም። አንዳንድ መሪዎች አነስተኛ የስኬት ዕድል ያላቸውንና ዕቅዱን የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለ መሆኑ ምንም ማረጋገጫ የሌላቸውን ትልልቅ ፕሮጀክቶች ያልማሉ። አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ፕሮጀክቶቹ ለተሳሳተ ዓላማ የሚገነቡ ናቸው፣ ምናልባትም ለዚያ መሪ ክብር፣ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ወይም ለሰዎች የሥጋ ጥቅም ነው የሚገነቡት። እግዚአብሔር አእምሮን የሰጠን እንድናስብበትና ሊሆኑ የሚችሉ ዕቅዶችን እንድናወጣበት ነው። መሪዎች በጣም አናሳ የስኬት ዕድል ያላቸውን ትልልቅ ዕቅዶች አውጥተው ሳይሳካላቸው ቢቀር ሕዝቡ ከአቅማቸው በላይ የሆነን ነገር እግዚአብሔር እንደሚያደርግ ያላቸው እምነት ይገደባል። በጉዳዩ ላይ እግዚአብሔር ያሰውን ፈቃድ በጥንቃቄ ከመረመርን በኋላ መልካምን ነገር ተስፋ ማድረግ እንችላለን። እግዚአብሔር የአስተሳሰብ አንድነት ከሰጠን በኋላ፣ ስለ ውጤቱ ልናምነው ይገባል።

ሁለተኛ፣ ባለ ተስፋ ማለት መሪ እንደ መሆናችን መጠን የምንፈልገው ነገር ሁሉ ይሆናል የሚል መተማመን አይደለም። ይልቁንም፣ እግዚአብሔር የገባቸውን የተስፋ ቃሎች እንደሚፈጽም በእርግጠኝነት ማመን ነው። ስለዚህ መሪዎች አንድ ነገር እንደሚሆን ተስፋ ለማድረግ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በጥንቃቄ መፈለግ ይኖርባቸዋል። መሪዎች ሊያደርጉ የፈለጉት ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ከተረዱ በኋላ ነው እግዚአብሔር ለዚያ አገልግሎት ስኬት እንደሚሰጥ ተስፋ ማድረግ የሚችሉት። ከቤተ ክርስቲያን አባላት አቅም በላይ የሆነ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ መገንባት የጀመሩ መሪዎች አሉ። ሕንጻው ሳይጠናቀቅ ሲቀር፣ ያላመኑ ሰዎች በክርስቲያኖች ሞኝነት ይስቃሉ፣ የክርስቶስም ስም ይሰደባል። እንዲህ ያለው «ባለ ተስፋነት» አደገኛና የወንጌል ጸር ነው።



13ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ጨለምተኛ መሪ የቤተ ክርስቲያንን እድገት እንዴት ሊያደናቅፍ እንደሚችል ግለጥ። ለ) መልካምን ነገር ተስፋ የሚያደርግ መሪ እንዴት ሕዝቡን በእምነት አነሣስቶ ለእግዚአብሔር ትልቅ ነገር ሊያመጣ እንደሚችል ግለጥ? ሐ) ባሕሪህ ምን ይመስላል? እግዚአብሔር ነገሮችን ለእርሱ ክብር እንደሚሠራ በማመን ላይ የተመሠረተን ባለ ተስፋነት ተምረሃልን? ካልተማርክ፣ እግዚአብሔርን በይበልጥ ለማመን ምን ማድረግ ይጠበቅብሃል? መ) እነዚህ ሁለት ዓይነት የተሳሳቱ ባለ ተስፋዎች የቤተ ክርስቲያን ስም እንዴት እንደሚያጎድፉ ግለጥ።

## 3. መንፈሳዊ ስጦታችንን ማወቅና በተሰጠን መንፈሳዊ ስጦታ ላይ የተመሠረቱ አገልግሎቶች ላይ ትኩረት ማድረግ።

14ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ቆሮ. 12:4-11፣ 27-30፣ ኤፌ. 4:11-13ን አንብብ። ሀ) ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ አማኝ ሁሉ ስጦ ያለው ምንድን ነው? ለ) የመንፈሳዊ ስጦታዎች ዓላማ ምንድን ነው? ሐ) የቤተ ክርስቲያንን አመራር የሚያንጸባርቁ የጸጋ ስጦታዎችን ዘርዝር። መ) መንፈሳዊ ስጦታችንን ማወቅና መረዳት ለቤተ ክርስቲያን መሪ አስፈላጊ የሆነው ለምን እንደ ሆነ አብራራ።

ብዙ ጊዜ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ስናስብ፣ አእምሮአችን በፍጥነት የሚሄደው አስገራሚ ወደ ሆነ የፈውስ ስጦታ፣ ስለ ትንቢትና በልሳን መናገር ነው። ነገር ግን ጳውሎስ ብዙ መንፈሳዊ ስጦታዎች እንዳሉ ተናግሯል። እነዚህ መንፈሳዊ ስጦታዎች ለእያንዳንዱ አማኝ የሚሰጡት እንደ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ነው። የእነዚህ ስጦታዎች ዓላማ እያንዳንዱ አማኝ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ቦታ እንዲኖረው ነው። አንዳንዶች መንፈሳዊ ስጦታዎች የመሪነት ስጦታዎች ናቸው። ጳውሎስ ከጠቀሳቸው የመሪነት ስጦታዎች መካከል ሐዋርያነት፣ ነቢይነት፣ ወንጌላዊነት፣ አስተዳደር፣ መጋቢነትና አስተማሪነት ይገኙበታል። (ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ይበልጥ የተሟላ ትምህርት ለማግኘት በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተጻፈውን የቲ.መ.ማ መጽሐፍ አንብብ።)

እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን መሪ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ

ቤተ ክርስቲያን ሆን ብላ ለአገልግሎት የምትመርጣቸው ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት የሚያስችል የተለያየ ጸጋ ያላቸው ሰዎች ናቸው። እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ስጦታና የወንጌል ስብከት ስጦታ ያላቸው ሰዎች ያስፈልጓታል። ሌላ የማስተማርና የእረኝነት ስጦታ ያለው ሽማግሌም ያስፈልጋል። ቤተ ክርስቲያን ሌላ ምሕረትን በማድረግና ድሃን የመርዳት ስጦታ ያለው ሽማግሌም ያስፈልጋታል። እነዚህ አራት ዓይነት ሽማግሌዎች በጋራ ሲሠሩ፣ ሁሉም አስፈላጊ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች በሥራ ላይ ይውሉ ዘንድ አገልግሎቶችን ይቆጣጠራሉ። እነዚህን ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚያገለግሉ ሰዎችን ስንመርጥ፣ ቤተ ክርስቲያናችን ጤናማ ትሆናለች።

ይህም በዋና ዋና ሽማግሌዎች በኩል ለእውነተኛ ትሕትና ጥሪ ያስተላልፋል። በአንዳንድ የአገልግሎት ክፍል ላይ ያለውን ድካም ለመቀበል ፈቃደኛ መሆንና በእነዚያ ክፍሎች ጠንካራ የሆነው ሰው እንዲረዳው መጠየቅ አለበት። አንዳንድ ሥራዎችን ለሌሎች ሽማግሌዎች መስጠትና ጥሩ አድርገው ሊሠሩ እንደሚችሉ ማመን አለበት። በዚህ መንገድ ብቻ ነው የእግዚአብሔር ሥራ እርሱን በሚያስከብር መንገድ የሚሠራው።

| |
|---|
| *15ኛ ጥያቄ:- ይህ መሪነትና የጸጋ ስጦታን የመረዳት ነገር በተለምዶ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመሪነት ቦታ ከሚመረጡበት መንገድ ጋር ምን ያህል የተለየ እንደ ሆነ አብራራ። ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በዚህ መንገድ መምረጥ ምን ጥቅም ያስገኛል? ሐ) በዚህ መንገድ መሪዎችን መምረጥ ምን ዓይነት ድካም እንዳለው ዘርዝር። መ) የአንተ መንፈሳዊ ስጦታዎች ምን ምን ናቸው? የሌሎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መንፈሳዊ ስጦታዎችስ ምንድን ናቸው? የሌሎቹ መሪዎች መንፈሳዊ ስጦታ በመሪነት ላይ የሚያመጣውን ሚዛናዊነት ግለጥ። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆኑ እንዴት ይረዳቸዋል? ሠ) ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ስጦታ ያላቸው ሰዎች በቡድን በመሥራታቸው ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆኑ ሽማግሌዎች ስለ አመራር ያላቸው የትኛው ግንዛቤ መቀየር አለበት?* |



## 4. ባሕሪያችንንና ሕይወታችንን ሚዛናዊ ማድረግ።

ንጉሥ ሰሎሞን አንድ ጊዜ አጅግም ሃይማኖተኛ ወይም ጻድቅ መሆን ጉዳት እንዳለው ተናግሯል (መክ. 7:16-18)። ሰሎሞን ለማለት የፈለገው መንፈሳዊ ጥበብና ባሕሪ በሕይወታችን መመጣጠን መቻል አለበት ነው። በአንደኛው ላይ ትኩረት በምናደርግበት ጊዜ፣ በራሳችን ላይ ጥፋት እናመጣለን። ለምሳሌ፣ በ«ፍቅር» እና በ«አንድነት» ላይ ከማተኮራችን የተነሣ «እውነት» እና «ቅድስና» ከደበዘዙብን፣ ሐሰተኛ ትምህርቶችና ርኩሰትን መታገሥ እንችላለን። ሆኖም፣ «በእውነት» እና «በቅድስና» ላይ አተኩረን «ፍቅር» ላይ ካላተኮርን፣ እግዚአብሔር ለኃጢአተኞች ጸጋ እንዳለው በመርሳት ክፉና ፈራጅ እንሆናለን። እነዚህን ሁለት ባሕርያት ማመጣጠን አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ውጤታማ መሪ ለመሆን፣ ባሕሪያችንን ሚዛናዊ ማድረግ ያኖርብናል።

ነገር ግን ውጤታማ የሆኑ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ውጤታማ ለመሆን ሁሉም የሕይወታችን ክፍል ሚዛናዊ መሆን እንዳለበት መገንዘብ አለባቸው። ብዙ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጊዜያቸውን በሙሉ በአገልግሎት ላይ በማጥፋታቸው ቤተሰቦቻቸውን ችላ ሲሉ ይታያሉ። «ለእኔ ሲሉ ሚስታቸውንና ልጆቻቸውን ከሚተዉ ይባረካሉ» ብሎ የለ እንዴ ብለን በተሳሳተ መንገድ ጥቅሱን እንተረጉማለን። ነገር ግን ጳውሎስ ቤተሰቡን እንደሚገባ የማያስተዳድርና ልጆቹን በእግዚአብሔር ቃል የማያሳድግ ሰው ለመሪነት ብቁ እንዳልሆነ ይገልጣል (1ኛ ጢሞ. 3:4)። እንዲያውም ልጆቻቸውን በሚገባ የማይዙ ሰዎች እንደማያምኑ እንዲቆጠሩ ተናግሯል (1ኛ ጢሞ. 5:8)።

የቤተ ክርስቲያንን ዝና በማያደፈርስ ሁኔታ እግዚአብሔር ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚጠቀምበት መሪ ለመሆን፣ ሁሉም የሕይወታችን ክፍል ሚዛናዊ በሆነ መልኩ መጠበቅ መቻል አለበት። ለቤተሰባችንና ለአገልግሎት የምንሰጠው ጊዜ መመጣጠን

ማገልገል ከመጀመሩ በፊት መንፈሳዊ ስጦታዎች ምን ምን እንደ ሆኑ መረዳቱ በጣም አስፈላጊ ነው። መንፈሳዊ ስጦታዎቻችንን መረዳት መሪዎችን በሚከተሉት መንገዶች ይረዳል፡-

ሀ. መንፈሳዊ ስጦታን ወይም ስጦታዎችን ስንረዳ፣ መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጉልበታችንን በምን ላይ እንድናተኩር እንደሚፈልግ እንረዳለን። መንፈስ ቅዱስ የማስተማርን ሳይሆን የወንጌል ስብከትን ስጦታ ከሰጠን፣ ያ ማለት መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትኩረቱ ማስተማር የሆነን አገልግሎት እንዳንቀበል በግልጽ ተናግሮናል ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ ከሰጠን ስጦታ ውጪ የሆነ አገልግሎት ለማገልገል ስንሞክር፣ እኛም ቤተ ክርስቲያንም እንጎዳለን። እኛ የምንጎዳው አገልግሎቱ ሳይመቸን ሲቀርና ፍሬ ማፍራት ሳንችል ስንቀር ተስፋ ስለምንቆርጥ ነው። የቤተ ክርስቲያን አባላት የሚጎዱት የአስተማሪነት ጸጋ ከሌለን ጥሩ ትምህርት የማግኘት ፍላጎታቸው ስለማይሟላላቸው ነው።

እግዚአብሔር ከመንፈሳዊ ስጦታችን ውጪ እንድናገለግል የሚጠይቅበት ጊዜ አለ። ነገር ግን ብዙ ጊዜ ያ ጊዜአዊ አገልግሎት ነው። መንፈስ ቅዱስም በዚህ የመሪነት ክፍል ድካማችንን ለማገዝ ተጨማሪ ችሎታ ይሰጠናል። መንፈስ ቅዱስ በግልጽ ስጦታ በሌለን አቅጣጫ እንድናገለግል ካልተናገረን በስተቀር፣ ልናተኩር የሚገባን ጠንካራ በሆንንበትና በመንፈስ ቅዱስ በታጠቅንበት አገልግሎት ነው።

ይህ እውነት ማለት ልንቀበለው የሚገባው የአመራር ክፍል ከጸጋ ስጦታችን ጋር አንድ ዓይነት የሆነውን ነው ማለት ነው። ይህ ማለት ሰዎችን ለአገልግሎት ስንቀበል፣ በመንፈሳዊ ስጦታቸው ነው ቦታ ልንሰጣቸው የሚገባው። ብዙ ጊዜ ቤተ ክርስቲያናት ስጦታውን ምንም ሳያውቁ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ምሩቅ የሆነን ሰው ይቀጥራሉ። በማስተማር የተቀባ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን በወንጌላዊነት ይሾማል። ወይም ተመራቂው ወንጌልን በመስበክ



የባሕሪያችን ክፍል መሆን አለበት (ማር. 12:28-33)። የእግዚአብሔርን ቃል ስናነብ የሕይወታችን ክፍል ልናደርጋቸው የሚገቡ አስፈላጊ ባሕርያትን እናገኛለን። እያነበብንና እየጸለይን በሄድን ቁጥር፣ መንፈስ ቅዱስ ባሕሪያችንን ይበልጥ ወደ ኢየሱስ ባሕሪ እያቀረበው ይመጣል (2ኛ ቆሮ. 3:18)። እግዚአብሔር ክርስቶስን በመምሰል በማደግ ይባርካችሁ።

17ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ውጤታማ መሪ የሚያደርጉና ያጠናናቸውን ባሕርያት በሙሉ ዘርዝር። ለ) ለመንፈሳዊ መሪ ያስፈልጋል የምትላቸውን ሌሎች ባሕርያት በዝርዝሩ ውስጥ አካት። ሐ) በጸሎት ሆነህ ዝርዝሩን አንብብ። በየትኞቹ ባሕርያት ጠንካራ፣ በየትኞቹ ደግሞ ደካማ ነህ? መ) በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ፣ ደካማ በሆንክባቸው ባሕርያት ለማደግ ምን ታደርጋለህ?

## ሦስተኛ ቀን፡- የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይበልጥ የተጋለጡባቸው ኃጢአቶች (ክፍል 1)

ዳዊት እንደ እግዚአብሔር ልብ የሆነ መሪ ነበር (የሐዋ. ሥራ 13:12)። ጥሩ ሙዚቀኛ፣ ደፋር ተዋጊ፣ ጥበበኛ አስተዳዳሪና መንፈሳዊ መሪ ነበር። ለ20 ዓመታት በመሪነት ከቆየ በኋላ፣ እስራኤል ዓይታ የማታውቀውን ሰላምና ብልጽግና አየች። የአገሪቱ ድንበር በታሪኳ ሰፊ የነበረው ያኔ ነው። በስኬቱ ጣራ ላይ ሆኖ፣ በአካሉም በመንፈሱም ራሱን ዘና አደረገ። በድንገት ዝሙትን ፈጸመና ነፍስ ገዳይ ሆነ።

18ኛ ጥያቄ፡- 2ኛ ሳሙ. 12:7-14ን አንብብ። ሀ) ምንም እንኳን እግዚአብሔር የዳዊትን ኃጢአት ይቅር ቢልም፣ በኃጢአቱ የተነሣ እግዚአብሔር ምን ይመጣበታል ነበር ያለው? ለ) ከዳዊት ሕይወት ከምታውቀው ተነሥተህ የእግዚአብሔር ትንቢት እንዴት እንደ ተፈጸመ ግለጽ። ሐ) ስለ መሪና ስለ ኃጢአት ምን ያስተምረናል? መ) ያዕቆብ 3:1ን አንብብ። ይህ ጥቅስ መሪዎች በሆኑ ሰዎች ላይ ስለሚመጣው ቅጣት ምን ያስተምረናል?

ምንም እንኳን እግዚአብሔር የዳዊትን ኃጢአት ይቅር ቢለውና

አለበት:: ከሁለት አንዳቸው ከተዛነፉ፣ እግዚአብሔርን አናከብርም:: በቤተ ክርስቲያን የምናሳልፈው ጊዜና በማኅበረሰባችን ውስጥ የምናሳልፈው ጊዜ መመጣጠን አለበት:: ጊዜአችንን ሁሉ ከክርስቲያኖች ጋር ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሳለፍን፣ በማኅበረሰባችን ውስጥ ጨውና ብርሃን የመሆን ችሎታችንን እናጣለን:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን የወንጌል ስርጭት፣ የማስተማርና የተጐዱትን መርዳት (የልማት) አገልግሎቶች ማመጣጠን አለብን:: ከእነዚህ ውስጥ አንደኛው ላይ በማተኮር ሌላውን ችላ ካልን፣ ቤተ ክርስቲያናችን ለእግዚአብሔር ክብር አታመጣም:: በተወሰኑ የእግዚአብሔር ቃል እውነቶች ላይ ካተኮርን ወይም በተወሰነ የጸጋ ስጦታ ላይ (ለምሳሌ:- በልሳን መናገር፣ ፈውስ) በማተኮር ማስተማር፣ መርዳትና ወንጌልን መሰበክ) የመሳሰሉትን ችላ ካልን፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግር እንፈጥራለን::

> *16ኛ ጥያቄ:- ሀ) በሰው ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በባሕርያት መካከል ያለ አለመመጣጠን ምን ዓይነት ችግር ሊፈጥር እንዳየህ አብራራ:: ለ) በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ላይ ያለ ሚዛን ማጣትና በተወሰነ አስተምህሮ ላይ ማተኮር እንዴት ችግር ሊፈጥር እንዳየህ አብራራ:: ሐ) ከክርስቲያኖች ጋር የምናጠፋው ጊዜ በማኅበራዊ አገልግሎት ላይ ከምናጠፋው ጊዜ ጋር ባለመጣጣሙ የቤተ ክርስቲያን መሪን ውጤታማነት እንዴት እንደሚቀንስ እንዳየህ አስረዳ:: ሠ) ሕይወትህን መርምር:: ሚዛናዊ ያልሆንክባቸው የሕይወትህ ክፍሎች ምንድን ናቸው? መንፈሳዊ ሚዛናዊነትን ለመጠበቅ ምን ማድረግ አለብህ?*

መጽሐፍ ቅዱስ መሪ ሊኖሩት ስለሚገቡ ሌሎች በርካታ ባሕርያት ያስተምረናል:: ለምሳሌ፣ በማቴ. 5:3-12 ኢየሱስ ሁሉም ተከታዮቹ፣ በተለይም መሪዎች፣ ሊያዳብሩዋቸው የሚገቡ ሌሎች ባሕርያትን ዘርዝሯል:: መጽሐፈ ምሳሌ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በዓለማውያን መንገድ ሳይሆን በጥበብ መንገድ የምትመራበትን ጥበብ እንዴት እንደምናገኝ ይናገራል:: በአዲስ ኪዳን፣ እርስ በርስ እንድንዋደድ ታዘናል፣ ስለዚህ እግዚአብሔርንና ሌሎችን መውደድ



የሚቆጠሩ ምክንያቶች ይዘረዝራሉ:: ነገር ግን በጣም ውጤታማ የሆኑ መሪዎች መልካምን ነገር ተስፋ የሚያደርጉቱ ናቸው:: እነዚያኑ ችግሮች አይተው፣ ሊሠሩ የሚችሉባቸው ብዙ መንገዶች ይታዩዋቸዋል::

ዋና ዋና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መልካምን ነገር ተስፋ የሚያደርጉ መሆናቸው አስፈላጊ ነገር ነው:: መልካምን ነገር ተስፋ ማድረግ የመንፈሳዊ ብስለት ውጤት ነው:: ይህ የሚመነጨው በእግዚአብሔር ላይ ጥልቅ የሆነ እምነት ከማሳደርና ነገሮች ምንም ያህል ቢከፉ እርሱ ሊያደርገው እንደሚችል ከማመን፣ እንዲሁም እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ራሱን በሚያስከብር መንገድ እንደሚሠራ ከማመን ነው:: ልክ እንደ ጳውሎስ፣ «እግዚአብሔር፣ ለሚወዱትና እንደ ሐሳቡ ለተጠሩት፣ ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲሠራ እንደሚያደርግላቸው እናውቃለን::» በተጨማሪም፣ «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፣ ማን ሊቃወመን ይችላል?» ማለት እንችላን (ሮሜ 8:28፤ 31)::

መሪዎች ቤተ ክርስቲያን ምን መሆን እንዳለበትና እግዚአብሔር የሚፈልገውን እንድታደርግ ሲፈልጉ መልካም ነገር ተስፋ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: ዋና ዋና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጨለምተኞች ከሆኑ፣ ምንም ዓይነት አዲስ ነገር ፈጽሞ አይሞክሩም:: ያ ጨለምተኝነት አስተሳሰብ ወደ ሕዝቡ ስለሚተላለፍ፣ አባላት በእምነት በእግዚአብሔር ምንም አዲስ ነገር አያደርጉም:: ነገር ግን መሪዎች መልካምን ነገር ተስፋ የሚያደርጉ ከሆነ፣ እነርሱና የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ችግሩን እንደሚወጡትና ታላቅ ነገር እንደሚያደርግ በእግዚአብሔር ይታመናሉ:: ነህምያ «የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል» እንዳለው፣ በእምነት ተነሥተን ብዙ ጨለምተኞች አይሆንም ያሉትን ቅጥር እንገነባለን (ነህ. 2:17-20)::

ሆኖም፣ መሪዎች ዕቅድ ሲያወጡ፣ መልካም ነገር ተስፋ አድራጊነትን በተመለከተ ሁለት ጥንቃቄዎቻችን ማድረግ አለባቸው::

በሥጋ ሞት ባይቀጣውም፣ ኃጢአቱ በቤተሰቡ ላይም ሆነ በአገሪቱ ላይ ክፉ መዘዝ እንደሚያመጣበት ነግሮታል፡፡ ለመጨረሻዎቹ 20 የአገዛዙ ዓመታት፣ ዳዊት የኃጢአቱን መዘዝ አጭዷል፡፡ የገዛ ልጁ እኅቱን ደፈረ፡፡ ሌላኛው ልጁ የገዛ ወንድሙን ገድሎ የዳዊትን ዙፋን ለመውሰድና ሊገድለው ፈለገ፡፡ አቤሴሎም ሳይሳካለት ቀርቶ ተገደለ፡፡

ለኃጢአት የተከፈለ እንዴት አስከፊ ዋጋ ነው! የኃጢአት ስርየት አገኘን ማለት በኃጢአታችን የተነሣ የሚመጣው መዘዝ ይቀርልናል ማለት እንዳልሆነ እወቅ፡፡ ይቅርታ መጠየቅ ክእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት እንደ ነበር ያስተካክለዋል፡፡ ነገር ግን የኃጢአታችን መዘዝ እኛን እንዳይከታተለን ማስቆም አይችል ይሆናል፡፡ ይህ ነገር አናጺ በጠረጴዛ ላይ ሚስማር ክሚመታበት መንገድ ጋር ይመሳሰላል፡፡ አናጺው የመታውን ሚስማር መልሶ መንቀል ይችላል፡፡ ነገር ግን በእንጨቱ ላይ የተፈጠረውን ቀዳዳ መሸፈን አይችልም፡፡ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር እንዲለን በመጠየቅ የኃጢአት ሚስማሮቻችንን ማስነቀል እንችላለን፡፡ ነገር ግን ቀዳዳዎቹ፣ ወይም ሥቃይን የሚያመጡ የኃጢአታችን መዘዞች፣ በሕይወታችን እንዳይቀጥሉ ማድረግ ይከብደናል፡፡ ጳውሎስ እንዳለው፣ «የዘራነውን ያንኑ እናጭዳለን» (ገላ. 6:7-8)፡፡ የሠራነው ኃጢአት መዘዝ ሌሎች ሰዎችንም ይጐዳል፡፡ ባለቤታችንን፣ ልጆቻችንን፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት የመሳሰሉትን ይጐዳል፡፡ ኃጢአት ረጅም መዘዝ የለውም ብሎ ሰይጣን ሲነግራችሁ አትመኑት፡፡ ልክ የሁለት በሬዎች ውጊያ በማየት ላይ ያለውን ሕፃን እንደሚጐዳ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ኃጢአትም ሌሎችን ይጐዳል፡፡ ከዚያ ነው ያዕቆብ አስተማሪ መሆንን (ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪ መሆንን) እንዳንፈልግና የሚበልጥ ኀላፊነትን ስንቀበል የሚበልጥ ፍርድ እንደሚጠብቀን ያስጠነቀቀው፡፡

እግዚአብሔር ዳዊትን ለዚህ ኃጢአቱ በጣም የቀጣው ለምንድን



ነው? ለዚህ የሚሆኑ በርካታ ምክንያቶች አሉ፡-

1. የመሪዎች ኃጢአት በሰዎች ዓይን የእግዚአብሔርን ክብር ክፉኛ ይጐዳል፡፡ ዓለም መሪዎች ኃጢአት ሲሠሩ ሲያይ፣ በመሪው ማሾፍ ብቻ ሳይሆን፣ ኢየሱስንም ያቃልሉታል፡፡ ኢየሱስ በዓለም ያለውን ዝና በማበላሸት፣ ኃጢአት የሚሠራ መሪ በዓለም ላይ ያለውን ክብር ያደበዝዛል፡፡ አንድ ሰው ሲጽፍ፣ «ግልጹና ተገቢው ትምህርት እግዚአብሔር የመሪዎችን ኃጢአቶች በጽኑ እንደሚቀጣ ነው፣ በተለይም የእነርሱ ይፋዊ ድርጊቶች የእርሱን ክብር የሚነካ በሚሆንበት ጊዜ፡፡»

2. እግዚአብሔር መሪ ካልሆኑ ሰዎች ይልቅ መሪ ለሆኑት ከፍተኛ መመዘኛ አለው፡፡ እግዚአብሔር ልክ የቤተ ክርስቲያን መሪ መንፈሳዊ ባሕሪ ያለውና በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበሰለ እንዲሆን እንደሚጠይቀው ሁሉ፣ የተሻለ ቅድስና እንዲኖረንም ይጠይቃል፡፡ እግዚአብሔር ለዳዊት የሠራው ኃጢአት በመንግሥታት መካከል የነበረውን ክብሩን እንዳጐደፈበት ተናግሯል፡፡ ሌላው ቀርቶ የሚያምኑ ሰዎች እንኳን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልዩ እንዲሆኑ ይጠብቃሉ፡፡ መሪዎች በኃጢአት ሲወድቁ፣ የቤተ ክርስቲያን ስም፣ በይበልጥ ደግሞ የኢየሱስ ስም ይሰደባል፡፡

3. የመሪዎች ኃጢአት መውደቅ ብዙ ሰዎችን ይነካል፡፡ የቤተ ክርስቲያን አባላት ለክርስቶስ ስለ መኖር ምሳሌ አድርገው የሚያዩት መሪዎችን ነው፡፡ ነገር ግን አንድ መሪ በኃጢአት ሲወድቅ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት ከዚያ በኋላ በቅድስና መኖር የሚያስፈልጋቸው አይመስላቸውም፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በራስ ወዳድነት ሲጣሉ፣ ወዲያውኑ የቤተ ክርስቲያን አባላት በቡድን መከፋፈል ይጀምራሉ፣ ቤተ ክርስቲያንም ትከፋፈላለች፡፡ ሰይጣንም ድል ያገኛል፡፡

| |
|---|
| 19ኛ ጥያቄ:- 2ኛ ሳሙ. 24ን አንብብ፡፡ ሀ) በዚህ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር መቅጣት የፈለገው ማንን ነው? ለ) ያንን ቅጣት ለመፈጸም |

እግዚአብሔር ማንን ተጠቀመ? ሐ) ይህ ስለ መሪና በሌሎች ላይ ስለሚመጣ የኀጢአት መዘዝ ምን ያስተምረናል?

ይህ ታሪክ የመሪው ኃጢአት በሌሎች ላይ እንዴት ፍርድ እንደሚያመጣ ያሳያል:: ዝርዝሩን አናውቅም፣ እስራኤል በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ስለ ሠራ እግዚአብሔር ሊቀጣቸው ወሰነ:: ነገር ግን ያልተለመደ የቅጣት መንገድን ነበር የመረጠው:: እግዚአብሔር ሰይጣን ዳዊት ባለው የጦር ኃይል እንዲኩራራ በማድረግ እንዲፈትነው ፈቀደለት:: የወታደሮቹን ብዛት ለመቁጠር በመፈለጉ፣ ዳዊት ባለው የጦር ኃይል ተመጻደቀ:: ድል የሚሰጠው እግዚአብሔር ነው ብሎ በመዝ. 3 እና 91 ላይ ቢጽፍም እንኳ፣ ድል ለማድረግ በእግዚአብሔር መመካቱን አቆመ:: መሪው ዳዊት በሠራው ኃጢአት፣ እግዚአብሔር እስራኤልን ቀጣ፣ 70 ሺህ ሰዎችም ሞቱ::

በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ መሪ መሆን ከባድ ነገር ነው! የምንወስዳቸው እርምጃዎች በሙሉ በሰዎች ሕይወት ውስጥ የረጅም ጊዜ ተጽዕኖ ያመጣሉ:: ቅዱስ ስንሆንና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስንከተል፣ ብዙዎች እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ አዎንታዊ ተጽዕኖ እናሳድርባቸዋለን:: ነገር ግን ኃጢአት ስንሠራ፣ በሌሎች ላይ አሉታዊ በሆነ መልኩ ለክፋት ተጽዕኖ እናመጣለን:: መሪዎች በዘፈቀደ ሲመሩና ለእግዚአብሔር ቃል እውነት ካልቆሙ፣ ምእመኑ በሐሰት ትምህርት መናጥ ይጀምራል:: መሪዎች ገንዘብ በአግባቡ ካልተጠቀሙ፣ ምእመናን በሙሉ አሥራት መክፈል ያቆማሉ:: መሪዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ግብ በግልጽ ካልተረዱ፣ ቤተ ክርስቲያን ገንዘቧን አላስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ላይ ታባክናለች:: ስለዚህ መሪዎች የሚያደርጉት ነገር በሙሉ በቤተ ክርስቲያን ላይ ትልቅ ተጽዕኖ አለው::

20ኛ ጥያቄ:- 2ኛ ቆሮ. 2:11ን አንብብ:: ከሰይጣን ጋር ባለን ግንኙነት ምን እንድናደርግ ነው ጳውሎስ የተናገረው?

ሰይጣንን ተቃውሞ መጻለይና እኛና ቤተ ክርስቲያናችንን



እንዲርቅ መጸለይ በቂ አይደለም:: ጳውሎስ የሰይጣንን ዕቅድና ቤተ ክርስቲያንን ሊያሸንፍበት ያለውን መንገድ ማወቅ ያስፈልገናል ብሏል:: አንዳንዴ ሰይጣን እኛን ብዙ ጊዜ የሚያጠቃበትን መንገድ ከተረዳን፣ እነዚያን መንገዶችና ጥቃቶች ልንጠነቀቅባቸው ይገባል:: ሰይጣን እንዴት ሊያጠቃን እንዳሰበ ካላወቅን፣ በሚያስገርም መንገድ በፍጥነት ያሸንፈናል::

ሰይጣን እኛን ለማሸነፍ የሚያደርገውን ነገር ድል ከምናደርግባቸው ምርጥ መንገዶች አንዱ ሰይጣን በክርስቲያኖች በተለይም በክርስቲያን መሪዎች ላይ ጥቃት የሚከፍትባቸውንና የሚያሸንፍባቸውን መንገዶች ማወቅ ነው:: ሰይጣን አንድን መሪ ካሸነፈ፣ በብዙ ሰዎች ሕይወት ላይ ተጽዕኖ እንደሚያመጣ ያውቃል:: ስለዚህ ከተራ የቤተ ክርስቲያን አባላት ይልቅ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ ጠንካራ ጥቃት ይሰነዝራል:: አሜሪካ ውስጥ «የሰይጣን ቤት» አለ:: አንድ ቀን የሰይጣን ቤቱ አባላት ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን ለማዳከም ወሰኑ:: የሰይጣን ቤቱ መሪዎች ለሰይጣን የሚያደርጉት ጸሎት ቁልፍ የሆኑ የአሜሪካ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዝሙት ኃጢአት እንዲወድቁ በመጠየቅ ላይ እንዲያተኩር ወሰኑ:: ለወራት ከጸለዩ በኋላ፣ በጣም ቁልፍ የሚባሉ የአሜሪካ ክርስቲያን መሪዎች አንድ በአንድ በኃጢአት ወደቁና ከመሪነት ቢያንስ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ታገዱ:: ሰይጣን በመላው ዓለም ያሉ ክርስቲያን መሪዎችን በማጥቃት ላይ ይገኛል፣ ስለዚህ ሰይጣንን ድል ለማድረግና ንጹሕና አስፈላጊ መሪ ሆኖ ለመቀጠል የሰይጣንን ዕቅድና ዘዴ ማወቅ አስፈላጊ ነው::

21ኛ ጥያቄ:- ሀ) አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚፈጽሟቸውን ኃጢአቶች ዘርዝር:: ለ) እነዚህ ኃጢአቶች በቤተ ክርስቲያንና በወንጌል ምስክርነት ላይ የሚያመጡት ተጽዕኖ ምንድን ነው? ሐ) የሰይጣንን ጥቃት ለመወጣት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምን ማድረግ አለባቸው?

ለሚቀጥሉት ሁለት ትምህርቶች፣ ሰይጣን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን የሚያጠቃባቸውን ልዩ ልዩ መንገዶች እንመለከታለን:: ምንም እንኳን የዚህ የጥናት መምሪያ መጽሐፍ ደራሲ እነዚህን

እውነቶች ከሕይወት ጋር በማዛመድ ከሚያይባቸው እተያይ እሳብ ጋር ባትስማማም እንኳን፣ ጊዜ ወስደህ ልብህ ውስጥ ኃጢአት እንደ እረም መብቀል ጀምሮ እንደ ሆነ መርምር:: የትኛውም መሪ በድንገት ጭልጥ ባለ ኃጢአት ውስጥ አይወድቅም:: ይልቁንም፣ ውድቀታችን እንዳንድ እመለካከቶችን ባሳደግንና በልባችን ውስጥ ቦታ እንዲያገኙ ባደረግን መጠን አዝጋሚ በሆነ መልኩ የሚከሰት ነው:: እረሞች ገና ሲበቅሉ ወዲያውኑ ሰብሉን እንደሚያጠፉት ሁሉ፣ እነዚህ ኃጢአቶችም በሕይወትህ ገና ትንንሽ ይሆኑ ይሆናል:: ነገር ግን እረሞች ሲያድጉ፣ ሰብሉን ያጠፋሉ:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ መንፈስ ቅዱስ በሕይወትህ ያሉ የኃጢአት እረሞች ገና ትንንሽ እያሉ እንዲነቅላቸው መጠየቅ ያስፈልጋል፣ ምክንያቱም አገልግሎትህን፣ ቤተሰብህን፣ ቤተ ክርስቲያንህን ሁሉ ሊያጠፉብህ ይችላሉ:: ለምን እሁን ጊዜ ወስደህ መንፈስ ቅዱስ በልብህ ጠልቆ እነዚህ ኃጢአቶች ማደግ ጀምረው እንደ ሆነ እንዲመረምርህ አትጠይቅም::

ኃጢአት ከእግዚአብሔር ፍላጐት ውጪ የሆነ ማንኛውም ነገር እንደ ሆነ ታስታውሳለህ:: እነዚያ ነገሮች ስሕተት ሳይመስሉን ይችላሉ፣ ነገር ግን ከምንሠራው ሥራ በስተጀርባ ያለው እመለካከታችንን ስንመለከት፣ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር እየሄድን ላይሆን ይችላል:: በሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት፣ መሪዎች ከተለያዩ እተያዮች አንጻር ስለሚፈጽሟቸው ኃጢአቶች እንመለከታን:: <u>አንደኛ</u>፣ መሪዎች በልባቸው ውስጥ ስለሚሠሩት ኃጢአትና ስለሚመሩበት ዓላማ እናያለን:: <u>ሁለተኛ</u>፣ መሪዎች ከሌሎች መሪዎችና ከቤተ ክርስቲያን አባላት ጋር ባላቸው ግንኙነት ላይ ስለሚፈጽሙት ኃጢአት እንመለከታለን:: <u>ሦስተኛ</u> መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚመሩበት መንገድ ላይ የሚሠሩትን ኃጢአት እንመለከታለን::

## በልብ ውስጥ ያሉ ኃጢአቶችና የመሪው ዓላማ (ክፍል 1)



### 1. የሰዎችን ክብር፣ ምስጋናና ተቀባይነትን የመፈለግ ኃጢአት::

22ኛ ጥያቄ:- ማር. 12:38-40ን አንብብ:: ሀ) የሃይማኖት መሪዎች በሰዎች ፊት ለመታየት የሚያደርጓቸውን ነገሮች ዘርዝር:: ለ) በዘመናችን ያሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚያደርጓቸውን ተመሳሳይ ነገሮች ዘርዝር:: ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሰዎች ዓይን መንፈሳዊ መስሰው ለመታየት የሚጥሩባቸውን ሌሎች መንገዶች ዘርዝር::

በኢየሱስ ዘመን፣ የሕግ እስተማሪዎች እሁን በቤተ ክርስቲያን እንዳሉት ወንጌላውያንና ሰባኪዎች ናቸው:: መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናታቸው ሕዝቡ እንዴት እግዚአብሔርን እንደሚከተል ማስተማር ይጠበቅባቸዋል:: ሆኖም፣ ሰይጣን እግዚአብሔርን በትሕትና ከማገልገል ይልቅ የሰዎችን ትኩረትና ክብር ለማግኘት እንዲሹ በማድረግ ፈተናቸው:: እነርሱ ሲያገኙ የፈለጉትን ነገር ተመልከት፣ ምክንያቱም የዘመናችን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያንኑ ኃጢአት ማለትም የሰዎችን ትኩረት የመፈለግ፣ መንፈሳዊና ልዩ ለመምሰል በመፈለግ ኃጢአት በቀላሉ ሊወድቁ ስለሚችሉ ነው::

***ሀ. ልዩ መሆናችንን ለመግለጥ የተለየ ልብስ መልበስ:-*** በኢየሱስ ዘመን የነበሩት የሃይማኖት መሪዎች ሕዝቡን ለማስደነቅ ልዩ ልብስ ይለብሱ ነበር:: በጣም ረጅምና ኅብረ-ቀለም ያለው ዘርፋፋ ቀሚስ ይለብሱ ነበር:: በተጨማሪም እነርሱ መምጣታቸውን ሁሉም ሰው እንዲያውቅ ለማድረግ ከቀሚሳቸው ሥር ጽናጽል ያደርጉበት ነበር:: ጥሩ የሆነ አለባበስ ስሕተት ባይሆንም፣ ነገር ግን ስለምንለብስበት ዓላማ መጠንቀቅ አለብን:: ሰዎችን ለማስደነቅ የምንለብስ ከሆነ፣ ተሳስተናል:: ለምሳሌ፣ እንዳንድ ሰዎች ሙሉ ሱፍ ልብስና ክራባት ከሌላቸው ለስብከት እንወጣም ይላሉ:: ለምንድን ነው እምቢ የሚሉት? ለእግዚአብሔር ቃል ካላቸው ክብር ከሆነና የእነርሱን እስፈላጊነት ለማሳየት ከሆነ፣ መልካም ነገር ነው:: ነገር ግን ያላቸውን ምርጥ ልብስ ሳይለብሱ

በሕዝብ ፊት መቆም ስለሚያሳፍራቸው ከሆነ፣ ወይም በሚለብሷቸው ልብሶች አስፈላጊ መሆናቸውን ለማሳየት ከሆነ፣ ኢየሱስ ያስጠነቀቀውን ኃጢአት በመሥራት አደጋ ላይ ናቸው:: የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተመራቂዎች ሲመረቁ አዳዲስ በሆኑ ልብሶች የሚዘንጡት አስፈላጊ መሆናቸውን ለማሳየትና ስመደነቅ ከሆነ፣ በኢየሱስ ዘመን የነበሩት የሕግ መምህራን በወደቁበት ኃጢአት ወድቀዋል ማለት ነው:: የመዘምራን ልብስ የተጀመረው በጥሩ ዓላማ ነበር:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመዘምራን ልብስ ማሰፋት የጀመሩት ጥሩ ጥሩ ልብሶች የሌሏቸው ድሃ አባላት እንዳያፍሩ ለማድረግ ነበር:: አሁን እሁን እነዚህ የመዘምራን ቡድን ልብሶች የሚስበስት እነርሱ ልዩ መሆናቸውን ለማሳየት ይሆን ወይ? ከሰዎች ክብርን የሚያገኙበት መንገድ ይሆን ወይ? ሰይጣን ብዙውን ጊዜ እኛን ለመጣል የሚጠቀመው መልካም በሆነ ነገር ነው::

የዘመናችን ወጣቶች ፋሽን የሚከተሉት ልዩ ሆኖ ለመታየት ከሆነ ሊጠነቀቁ ይገባቸዋል:: በጣም የሚያምር ሹሩባ መሠራት፣ ጥቁር መነጽር ማድረግ፣ ፋሽን የሆኑ ልብሶችን መልበስ፣ እና የመሳሰሉት በእግዚአብሔር ፊት ልዩ አያደርገንም:: ሰይጣን በውስጣዊ ውበታችን፣ በስብዕናችንና በባሕሪያችን ላይ እንዳናተኩር ስለሚፈልግ በውጫዊ ነገር ላይ እንድናተኩር ይፈልጋል:: 1ኛ ጴጥ. 3:3-5 ሴቶች በውጫዊ ነገራቸው ላይ በጣም እንዳያተኩሩ ያስጠነቅቃል፣ ይልቁንም ባሕሪያቸውን በእግዚአብሔርና በሰዎች ዓይን ውብ እንዲያደርጉ ይጠይቃል:: ይህ ለሁላችንም ጥሩ ማስጠንቀቂያ ነው::

23ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልዩ ልብስ ለብሰው የሰዎችን ትኩረት ለመሳቢያ ሲያውሉት እንዴት እንዳየህ ግለጥ:: ክርስቲያን ወጣቶችስ ትኩረትን ለመሳብ ምን ያደርጋሉ? ለ) በሰዎች ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ጥሩ አድርጐ በመልበስና የሌሎችን ትኩረት ለማግኘት ጥሩ አድርጎ በመልበስ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?



24ኛ ጥያቄ:- ማቴ. 23:5-12 አንብብ:: ሀ) ኢየሱስ እንዳናደርገው ያስጠነቀቀው ምንድን ነው? ለ) በቤተ ክርስቲያናችን ምን ያህል ይህን ነገር እንታዘዛም?

**ለ. ከሰዎች ዘንድ የተለየ ሰላምታና ክብር መፈለግ:-** የአይሁድ ሃይማኖት መሪዎች ጥሩ ጥሩ ልብሶችን ለብሰው በእግራቸው ሲዘዋወሩ፣ ተራው ሕዝብ ሰላምታ ሲሰጣቸውና ኃይለኛና ታዋቂ የሆኑትን የሃይማኖት መሪዎች እጅ መጨበጥ ይፈልጋል:: የሃይማኖት መሪዎች እንዲጠሩ የሚፈልጉትም «ረቢ እገሌ» በሚለው የክብር ማዕረጋቸው ነበር:: ኢየሱስ እንደዚያ ያለውን የክብር ስምና ሰላምታ የሚናፍቁና የሚፈልጉ እንደሚቀጡ ተናግሯል:: እንዲያውም፣ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እነርሱ በእንደዚያ ዓይነት ስም እንዳይጠሩ፣ ሌሎችንም በዚያ ዓይነት ስም እንዳይጠሩ ወይም ልዩ የክብር ስም እንዳይኖራቸው ነግሯቸዋል:: ይልቁንም፣ ወንድምና እኅት በሚለው ከሌሎች ጋር እኩል በሚያደርግ መጠሪያ እንዲያተኩሩ ነው የተናገረው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሌሎች አገልጋይ መሆናቸው ላይ እንዲያተኩሩ እንጂ፣ ራሳቸው ልዩ ወይም በማዕረጋቸው ታላቅ መሆን እንደሌለባቸው ይናገራል::

ግን ብዙ ጊዜ ኢየሱስ ያስተማረውን ሳንታዘዝ በመቅረትና የሃይማኖት መሪዎችን መንገድ አንከተልም? «እንደ ምን ነዎት ዶክተር ተስፋሁን::» «ወንጌላዊ ዮሐንስ፣ ቤተሰብ እንዴት ነው?» «የቤተ ክርስቲያናችንን ሽማግሌ ግርማን አገኘኸው?» «ዛሬ የምናደምጠው ሰባኪ ስንታየሁን ነው::» ታላቅ በሆነ የሥነ መለኮት ትምህርት ቤት የተማረ መጽሐፎችን የጻፈ በአሁኑ ወቅትም ከሺህ የሚበልጡ አባላት ያላት የአገሊት ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ናቸው:: «መጋቢ ተስፋዬ አሁን መጥተው ይጸልዩልናል::» የመሳሰሉ አባባሎችን እንጠቀምም? ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቢያንስ «እንደ ምን ነህ?» ከሚባሉ ይልቅ «እንደ ምን ነዎት?» ቢባሉ ይመርጣሉ:: እነዚህ በሙሉ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዴት

የተለያዩ ማዕረጎችን እንደምንጠቀም የሚያሳዩ መግለጫዎች ናቸው:: ለውየው እንዲህ ብላችሁ ጥሩኝ ባይልም እንኳን፣ ሰይጣን እነዚህን የማዕረግ ስሞች በመጠቀም በመሪው ላይ ኃጢአትን ለማምጣት ይጠቀምበታል:: ታላቅ ክብርና እንክብካቤ የሚደረግላቸውና በማዕረግ የሚጠሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ መሆን ይከብዳቸዋል:: ሰይጣን ብዙ ጊዜ በትዕቢት እንድንወድቅ ይፈትነናል:: በአመራር ቦታ ላይ ያሉ ሰዎችን ለማክበር መፈለጋችን ሰይጣን እነርሱን በኩራት ለመጣል እንዲጠቀምበት ይሆን? ከሆነ፣ እነርሱ ኃጢአት እንዲሠሩ ሰይጣን የሚጠቀምበት መሣሪያ ሆንን ማለት አይደል?

25ኛ ጥያቄ:- ሀ) በመሪነት ላይ ላሉ ሰዎች ልናሳያቸው የሚገባ ተቀባይነት ያላቸው የአክብሮት መንገዶች ምንድን ናቸው? (ፊልጵ. 2:29-30፣ 1ኛ ጢሞ. 5:17) ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪን ሥልጣን ለመጉዳት ተቀባይነት የሌላቸው ምን ዓይነት መንገዶች ይመስሉሃል? ሐ) ተቀባይነት ባለው አክብሮትና ተቀባይነት በሌለው አክብሮት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

**ሐ. ልዩ የሆኑ መቀመጫዎች መሪዎች አስፈላጊ እንደ ሆኑ ያሳያሉ:-** መሪዎች የሚመሩት ሕዝብ ማንሣት የሚፈልገው ጉዳይና ምክር መቀበል የሚፈልግበት ጉዳይ ሊኖረው ስለሚችል በማንኛውም ሰዓት መገኘት አለባቸው:: ሆኖም፣ መሪዎች ልንጠነቀቅ የሚገባን ነገር የሽምግልና ሥልጣናችን ወይም የመዘምራን ቡድን አባልነታችን ምርጥ ወንበር ላይ ለመቀመጥ ወይም በቤተ ክርስቲያን አባላት ፊት ለመቀመጥ እንደሚያበቃን ልናስብ አይገባም:: የተለዩ መብቶችን የምንጠይቅ ከሆነ፣ የሕግ አስተማሪዎች የሠሩትን ኃጢአት በመድገም ላይ ነን ማለት ነው:: ሰዎች እንዲያዩን ስንል በሕዝብ ፊት የመቀመጥ ኃጢአትን በመሥራት ላይ ነን ማለት ነው:: ከሌሎች የተሻልን በመሆናችን ምርጥ በሆነ ወንበር ላይ መቀመጥ ይገባናል ብለን አሰበናል ማለት ነው:: ኢየሱስን የሚያሳሰበው ዋነኛው ጉዳይ መሪዎች «የት»



ተቀመጡ የሚለው አይደለም:: ይልቁንም፣ የሽማግሌዎች ልብ ነው:: የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ በቤተ ክርስቲያኒቱ ለሚገኙት ሰዎች አገልጋይ መሆኑን ረስቶ በሕዝብ ፊት መቀመጡ ከሌሎች የተለየና አስፈላጊ ሰው እንደ ሆነ ከተሰማው፣ ወይም የእርሱ እንደዚያ መሆን በሌሎች ሰዎች ልብ ቅናትን የሚፈጥር ከሆነ፣ ሰይጣን ቤተ ክርስቲያን ፊት መቀመጥን በሰዎች ልብ ውስጥ ኃጢአት ለመፍጠር ተጠቅሞበታል ማለት ነው::

**መ. የርኅራኄና ደግነት እጥረት:-** በኢየሱስ ዘመን የነበሩ የሃይማኖት መሪዎች ለሌሎች ችግር ግድ አልነበራቸውም:: ሰዎች እንደ ድኅነት ያለ ችግር ቢኖርበት ወይም ጋለሞታ ወይም የማደጎ ልጅ ቢሆን፣ የእግዚአብሔር ፍርድ ነው ብለው ያስቡ ነበር (ዮሐ. 9:2-3):: ይህ ማለት መንፈሳዊ ሰዎች ሊያሳስባቸው አይገባም ማለት ነው:: ምክንያቱም የሃይማኖት መሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ሐብታሞች ስለ ነበሩ፣ ድሃው እርዳታ ፍለጋ ወደ እነርሱ ይሄድ ነበር:: ነገር ግን የመሪዎቹ ልብ የደነደነ ነበር:: ፈሪሳውያን ለድሃው ሕዝብ ችግር ግድ ያልነበራቸው ሰዎች ብቻ አልነበሩም፣ ይልቁንም ድሃውን ከመርዳትና ፍትሕን እንዲቀበል ከማድረግ ይልቅ ከሃብታሞችና ከኃይለኞች፣ ከመንግሥት ባለ ሥልጣናት ጋር በመሥራት በድሃው ላይ ጥቅም ያገኙ ነበር::

ሰይጣን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ከሚያሸንፍባቸው መንገዶች ውስጥ ለሌሎች ሰዎች ችግር ግድ እንዳይኖረን በማድረግ ነው:: ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፣ ልባችን ይደነድናል:: የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች አብዛኛውን ጊዜ «የእግዚአብሔር አገልጋዮች» ነን ብለው ስለሚያስቡ፣ ለሌሎች ቸርነት ከማድረግ ይልቅ ሌሎች የሚያስፈልጓቸውን አካላዊ ፍላጎቶች እንዲያሟሉላቸው ይጠብቃሉ:: በአንዳንድ አገሮች፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በንፉግነትና ለሌሎች ችግር ግድ ባለመስጠት ይታወቃሉ::

በእርግጥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለሌሎች ችግር ግድ

ከሚያጡባቸው ምክንያቶች አንዱ ሰዎች ሁሉ ችግራቸውን ይዘው ወደ እነርሱ ስለሚሄዱ ነው። እናም አብዛኛዎቹ ችግሮች ከገንዘብ ጋር የተያያዙ ናቸው ወይም የሰውየው ኃጢአት ውጤቶች ናቸው። ለይጣን አብዛኛውን ጊዜ መሪዎች ሕዝቡ ድሃ የሆነው በኃጢአቱ እንደ ሆነና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግን እግዚአብሔርን በመታዘዛቸው ሃብታም እንደ ሆኑ እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል። መሪዎች ባላቸው «በረከት» ኮርተው ሌሎች ድሃ በመሆናቸው፣ ኃጢአተኛ በመሆናቸውና አናሳ እምነት ስላላቸው ይንቋቸዋል። በኤድስ የሚሞቱ ሰዎችን ሲያዩ፣ መሪዎች «ኃጢአትን በመሥራታቸው የሚገባቸውን አግኝተዋል» ብለው ያስባሉ። ግን ሁላችንም ዘላለማዊ ቅጣት የሚገባን ኃጢአተኞች አይደለን እንዴ? ሁላችንም በእግዚአብሔር ልንቀጣ አይገባንምን? እግዚአብሔር ምሕረቱን ስላወረደልን ብቻ ነው ሁላችንም ያልተቀጣነው። ታማኝ ባልሆነ ባል ጥፋት ያለ ጥፋታቸው የሚሠቃዩት ሚስቶችና ሕፃናትስ? ምንም እንኳን ኢየሱስ በኃጢአት መኖርን ባይደግፍም፣ ከፈወሳቸው በኋላ ዳግም ኃጢአትን እንዳይሠሩ በመናገር ኢየሱስ ርኅራኄውን በማሳየት ሲጐዱ ያገኛቸውን ረድቷል (ማቴ. 9:35-36፣ 15:32፣ 20:29-34)። ሰዎች ለሚጋፈጡት ችግር ልብህ እንዳይደነድን ተጠንቀቅ። እነዚያ ችግሮች አካላዊ (ድህነት፣ ሕመምና ሞት) ወይም መንፈሳዊ (ልማዳዊ ኃጢአት [መጠጥ]፣ በዝሙት ኃጢአት መውደቅ ሊሆኑ ይችላሉ። የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ መሆናችን፣ ዘጠና ዘጠኙን በጐቹን ትቶ የጠፋችበትን አንዲት በግ ሊፈልግ እንደሚወጣና በእርሷ ከመፍረድ ይልቅ እንደሚያቅፋት የበግ እረኛ መሆን አለብን (ማቴ. 18:10-14)። የልጁን መመለስ በናፍቆት እንደሚጠብቅና ልጁ ሊመጣም በነፃ ይቅር እንደሚለው፣ በኃጢአቱ ከመውቀስ ይልቅ በመመለሱ ደስ እንደሚሰኝ አባት መሆን አለብን (ሉቃስ 15:16-32)። አብዛኞቻችን ደስተኛ ከሆነው አባት ይልቅ እንደ ታላቁ ልጅ እንሆናለን።



26ኛ ጥያቄ፡- የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት፡- ማቴ. 9:35-36፤ 15:32፤ 20:29-34። ሀ) ኢየሱስ ድሆችን ለመርዳት ስላለው ልብ ከእነዚህ ጥቅሶች ምን እንማራለን? ለ) የአብዛኛዎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አመለካከት እንደ ኢየሱስ ይመስልሃል? መልስህን አብራራ። ሐ) ልብህ በምን ዓይነት መንገዶች ለሰዎች ችግር ግድ እጥቶብህ ያውቃል? ለተቸገሩ ሰዎች ልብህ ሁልጊዜ ርኅራኄ እንዲሰማው ምን ታደርጋለህ?

ሠ. ሌሎች እንዲያደርጉ የምናስተምረውን ነገር አለማድረግ፡- ምንም እንኳን ኢየሱስ የሃይማኖት መሪዎችን በዚህ በቀጥታ ባይከሳቸውም፣ እንዳደረገው ይገመታል። የሃይማኖት መሪዎቹ ከመጽሐፍ ቅዱሳቸው ጋር በጣም ይተዋወቃሉ። አይሁዶች ድሆችን ቸል እንዳይሉ እግዚአብሔር እንደ ተናገራቸው ያምናሉ። እንዲያውም፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ እውነተኛ ሃይማኖተኝነት እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ማለትም ጋለሞታዎችን፣ ወላጅ የሞተባቸውን፣ ድሆችንና ስደተኞችን መርዳትን ማካተት እንዳለበት ተናግሯል (ኢሳ. 1:17፣ 23፤ ሚክያስ 3:5)። የሃይማኖት መሪዎች ሕዝቡ ድሆችን እንዲረዳ ለማስተማራቸው ጥርጥር የለም። በእርግጥ፣ አብዛኛውን ጊዜ የሚሰብኩት ለድሃ የመስጠትን ዋጋ ሳይሆን አይቀርም። ነገር ግን የሃይማኖት መሪዎች ራሳቸው ለድሃ ሲሰጡ አይታዩም። ያንን ካደረጉ ግን፣ ድሃን ይረዳል የሚል ዋጋን ከእግዚአብሔር ለማግኘት ነው።

የቤተ ክርስቲያን መሪ ሆነን አንዳንድ ጊዜ ጋለሞታዎችን ወይም በመካከላችን ያሉ ድሆችን ላለመርዳት ጥሩና ተጨባጭ የሚመስሉ ምክንያቶችን እንሰጣለን። «እግዚአብሔር እንድሰጥ አልተናገረኝም» እንላለን። ወይም ምግብ ከመብላታችን በፊት «የሚበሉት የሌላቸውን አስባቸው» ብለን እንጸልያን፣ ነገር ግን አንድም ቀን መንገድ ላይ ለተራበው ሰው ከምንበላው ምግብ ለመውሰድ አስበን አናውቅም። እግዚአብሔር ድሆችን የሚረዳው በሕዝቡ ቸርነት ነው። ለእነርሱ ምግብ ከሰማይ አያዘንብላቸውም!

ሰዎች ለድሆች ደግ እንዲሆኑ እናስተምራለን። ነገር ግን ላጡና ለነጡት በጣም ትንሽ የሚሰጡት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ናቸው።

ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ በተለይም ለሚሰብኩና ለሚያስተምሩት፣ ከሚናገሩት ጋር የሚቃረን ነገር ማድረግ የሚቀላቸው ይመስላሉ። በየዕለቱ ስለ መጸለይ አስፈላጊነት፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስለ ማጥናት አስፈላጊነት፣ ለተቸገሩ ስለ መስጠት፣ ወዘተ. . . እንሰብካለን። ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ ራሳችን የምንሰብከውን አንፈጽመውም። እኛ ራሳችን ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ፊት በጸሎትና የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት ጊዜ አናሳልፍም፣ ለድሃ በልግስና አንሰጥም፣ ከችግራቸው እንዲወጡ ለማድረግም አንፈልግም። ይሄ ሌሎች እንዲያደርጉ የምንነግራቸውን ነገር አለማድረግ እግዚአብሔር ይጠየፈዋል።

| |
|---|
| 27ኛ ጥያቄ:- ሀ) በኢትዮጵያ የሚገኙ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ለድሃ በልግስና በመስጠት ይታወቃሉ? መልስህን አብራራ። ለ) ካልሆነ፣ ለድሆች በልግስና የማይሰጡበት ምክንያት ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ? ላለመስጠታቸው ምን ሰበብ ይሰጣሉ? ሐ) ባለፈው ወር በልግስና ስለ ሰጠህበት ነገር አስብ። ለተቸገሩ ሰዎች በልግስና የሰጠህባቸውን መንገዶች ዘርዝር። |

መጽሐፍ ቅዱስ «ድሆችን መርዳት» ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ መረዳት ያስፈልጋል። እግዚአብሔር ድሃ ራሱን እንዲችል እንድንረዳው ይፈልጋል። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች መሥራት ሲገባቸው እንዲለምኑ አያስተምርም። ሲሠራ የማይወድ አይብላ ተብሎ ተነግሮናል (2ኛ ተሰ. 3:6-10)። በብሉይ ኪዳን፣ እግዚአብሔር አይሁዳውያን ምርታቸውን ሲሰበስቡ የእርሻውን ድንበር ሁልጊዜ ለድሃ እንዲተዉት ተናግሯቸዋል። መሥራት የሚችሉት ድሆችም ወደ እርሻ ወርደው ለራሳቸው አጭደው መብላት ይጠበቅባቸዋል እንጂ ሰው የሚበላ እስከሚሰጣቸው መጠበቅ የለባቸውም (ዘፀአ. 23:11፤ ዘሌዋ. 19:9-10፤ 23:22)።



ታዲያ መጽሐፍ ቅዱስ ድሃን ስለ መርዳት ከሚያስተምረው ነገር ምን እንማራለን:-

1. ገንዘብን ከመስጠት ይልቅ፣ ሥራን መፍጠር የተሻለ ነው። ሥራ የሰውየውን ክብር ያስጠብቃል፣ እንዲሁም ሰዎች ሳይሠሩ በነፃ ስጦታን ከመቀበል አስተሳሰብ ያላቅቃቸዋል። የጥገኝነትን ስሜት ያቆማል። የነፃ እርዳታ መደረግ ያለበት አካላዊ ጉዳት ለደረሰባቸውና መሥራት ለማይችሉት ብቻ መሆን አለበት። ይህ ማለት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ለድሆች እርዳታን ሲሰጡ የሚችሉባቸውን ሥራዎች ማለት በቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ያለውን ሣር ማጨድ፣ በግድግዳ ላይ ያሉ ስንጥቆችን ለመድፈን ጭቃ መለጠፍ፣ ወዘተ. . . ያሉትን ማዘጋጀት አለባቸው። አንድ ሰው ለመሥራት ፈቃደኛ ካልሆነ፣ በእውነት እርዳታ አያስፈልገውም።

2. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎችን ከድህነት ኑሮ ለማውጣት መጣር አለባቸው። «ለሰው ዓሣን ብትሰጠው፣ ለአንድ ቀን ትመግበዋለህ፣ ዓሣ ማጥመድን አስተምረው፣ ለዕድሜ ዘመኑ ትመግበዋለህ» የሚል የቻይናውያን ምሳሌአዊ አነጋገር አለ። ሰዎችን ስንረዳ ሰዎች ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ከዚያ ችግር እንዲያወጡ ልንረዳቸው የምንችልባቸውን መንገዶች ማፈላለግ አለብን። ያ ምናልባትም እንዴት እናጺ እንደሚሆኑ በማስተማር፣ ትንሽዬ ሻይ ቤት እንዲከፍቱ በማድረግ፣ ጋሪ በመግዛት፣ የሚያርሱበትን በሬ በመስጠት፣ ወዘተ. . . ሊሆን ይችላል። የቤተ ክርስቲያን የልማት አገልግሎት እውነተኛ ግብ ሰዎች ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግ ነው። ቤተ ክርስቲያንን መሠረት ያደረገ ልማት እውነተኛ ግብ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሚያስፈልገውን የገንዘብ (ለምሳሌ፣ ለወንጌላውያን የሚሆን ገንዘብ) ማሰባሰብ ወይም ለጊዜያዊ ሁኔታ ችግር (ለምሳሌ:- ድርቅ) እፎይታ መስጠት አይደለም።

28ኛ ጥያቄ:- ሀ) የአናንተ ቤተ ክርስቲያን በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ ድሆችን እንዴት ነው የምትረዳው? ለ) ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት ነጥቦች አንጻር፣ ሰዎች ከድህነት ኑሮአቸው እንዲወጡ ስለሚያስችሉ መንገዶች የምትሰጠው ምክር ምንድን ነው?

*ረ. በረጃጅም ጸሎቶች መንፈሳዊነትን ለማሳየት መሞከር:-* የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ከሚያሸንፉ ኃጢአቶች አንዱ መንፈሳዊነታችንን ለሌሎች ለማሳየት መሞከር ነው። ከዚህ የተነሣ፣ የምንጸልይበትንና የምንሰብክበትን መንገድ መለወጥ እንጀምራለን። በኢየሱስ ዘመን የሃይማኖት መሪዎች በጣም መንፈሳዊ ሆኖ መታየትን ይወድዱ ነበር። ስለዚህ እንዲጸልዩ ሲጠየቁ፣ ለረጅም ጊዜ ነው የሚጸልዩት። ድምጻቸውን ጮክ አድርገው ነው የሚጸልዩት። ኢየሱስ ግን ይህንን ይጠላል፣ ምክንያቱም የጸሎት ዓላማ ያ አይደለም። ጸሎት ማለት ትሑት የሆነ ሰው ከታላቁ ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝበት ነው። መንፈሳዊነታችንን የምናሳይበት መሣሪያ ሊሆን አይገባውም። በሕዝብ ፊት የሚሰብኩ ወይም የሚያስተምሩ ሰዎች በዚህ ኃጢአት በቀላሉ ነው የሚወድቁት። የሚከተሉት ልክ እንደ ሕግ መምህራን እንዴት በኃጢአት እንደምትወድቅ የሚያሳዩ ምሳሌዎች ናቸው:-

1) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስንሆን ረዥምና መንፈሳዊነት የተላበሱ ጸሎቶችን ማድረግ። በግላችን የምንጸልየው በጉባዔ ከምንጸልየው ጋር አንድ ካልሆነ፣ ጸሎታችን ኃጢአተኝነት የተሞላበት የሚሆንበት ዕድል አለ። ለምሳሌ፣ የግል ጸሎታችን አጭርና በቀጥታ ወደ ጉዳዩ የምንሄድበት ሆኖ ሳለ (ለምሳሌ፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ እገሊት ታምማለች። እባክህ ፈውሳት።)፣ በሌሎች ፊት ስንጸልይ ግን ሌሎች ብዙ ነገሮችን የምናክልበት ከሆነ፣ ኃጢአት እየሠራን ሊሆን ይችላል። ጸሎታችንን በተለያዩ 15 መንገዶች በመደጋገማችን ኃይል እንጨምርለትም።

2) ጸሎታችንን ብዙ ሰዎች ሊረዷቸው በማይችሉ ሃይማኖታዊ



ቃላት ከሞላን፣ ልባችንን ልንመረምር ይገባል። «ሃሌ ሉያ» ወይም «አሜን» የሚሉ ቃላትን ባልተለመደ መንገድ የምንደጋግም ከሆነ፣ ለምን እንደምናደርገው ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባል። እነዚህን የመሳሰሉ ቃላትን ያለ ምንም ትርጉም በመደጋገም ጸሎታችን ተጨማሪ ኃይል እንዲያገኝ ማድረግ አንችልም። በግላችን እንደዚህ የማንጸልይ ከሆነ፣ ለምንድን ነው በሌሎች ፊት እንደዚያ የምናደርገው?

3) በሕዝብ ፊት ስንጸልይ እቤት የምንጸልይበትን መንገድ ከቀየርን፣ ኃጢአትን እየሠራን ሊሆን ይችላል። በምንጸልይበት ሰዓት እጆቻችንን ወደ ላይ በማንሣት፣ ጭንቅላታችንን ወደ ሰማይ ቀና በማድረግ፣ ድምጻችንን በማጉርነን፣ በልባችን ማልቀስ ሳይሰማን ለማልቀስ በመሞከርና በመሳሰሉት ሰዎችን ለማስደነቅ የምንሞክር ከሆነ፣ በኢየሱስ ዘመን እንደ ነበሩት የሕግ መምህራን ሆነናል ማለት ነው። እጅን ወደ ላይ አድርጎ መጸለይ፣ ፊታችንን ወደ ሰማይ ቀና ማድረግ፣ ልባችን በኃጢአት ሲከብድብን ማልቀስ፣ ወይም ለሌላ ሰው ፍላጐት መጸለይ ችግር የለባቸውም። ነገር ግን ከልባችን ካልወጣና መንፈሳዊነታችንን ለሌሎች ለማሳየት የማናደርገው ከሆነ፣ ወይም ሌሎች አብረውን እንዲያለቅሱ ፈልገን ከሆነ፣ ኃጢአትን እያደረግን ነው።

4) ሐረጐችን ያለ ትርጉም መጠቀም። ማንኛውም በተደጋጋሚ የምንጠቀማቸው ቃላት «ከንቱ ድግምግሞሽ» ይባላሉ (ማቴ. 6:7)። ለምሳሌ፣ በጸሎታችን ውበጥ ከእግዚአብሔር ስሞች አንዱን ወስደን በተደጋጋሚ ከጠራን፣ ምናልባት የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ እየጠራን ይሆናል ይህ ምናልባት የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥራ (ዘጸአ. 20:7) የሚለውን ሦስተኛውን ሕግ መጣስ ይሆናል። [ማስታወሻ:- አንድ ነገር ሲሆን፣ «በኢየሱስ ስም» ስንል፣ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥራ የሚለውን ሕግ እየጣስን ነው። የኢየሱስ ስም ልክ እንዲህ ሳታስበው እስከምትጠቀምበት ድረስ ለምዶብሃልን? እስወግደው! የእግዚአብሔርን ስም በማስብና

በመፍራት ብቻ ተጠቀም! «ሃሌ ሉያ» (ትርጉሙ «ጌታ ይመስገን» ማለት ነው) የሚለውን ዓይነት ቃላት ስንጠቀምም እንደዚያው መሆን አለበት። ትርጉሙ ሳይገባን ሃሌ ሉያ ወይም «አሜን» (በተባለው ነገር እስማማለሁ፣ እንደዚያ ይሁንልኝ» ማለት ነው) ካልን፣ ትርጉማቸውን ሳይረዱ ቃላቱን መጥራት ጥቅም የለውም። በእግዚአብሔር ዓይንም ኃጢአት ሊሆን ይችላል!]

5) ሰዎችን በጸሎት መልክ መስበክ። ጸሎት በእኛና በእግዚአብሔር መካከል የሚደረግ ግንኙነት ነው። ለስብከት የሚያገለግል መሣሪያ እንዲሆን፣ ወይም ኃጢአት የሠሩ ሰዎችን የምንጋፈጥበት አይደለም። ያለንን የእግዚአብሔር ቃል እውቀት የምናሳይበትም ቦታ አይደለም። ጸሎት በልባችን ውስጥ ያለውንና የቤተ ክርስቲያኒቱን ጥያቄ በእግዚአብሔር ፊት የምናቀርብበት ነው።

| |
|---|
| 29ኛ ጥያቄ፡- ሰዎች ብዙ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት እንደሚጸልዩ አስተውል። ሀ) ሰዎችን ለማስደነቅ ልዩ በሆነ «ሃይማኖታዊ» መንገድ የሚጸልዩባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ለ) ሳናስበው በተደጋጋሚ የምንደጋግማቸውን ቃላትና ሐረጐች ዘርዝር። ሐ) ጸሎትን ወደ እግዚአብሔር ከመጸለይ ይልቅ ሰዎችን ለመስበክና ለመክሰስ እንዴት እንደምንጠቀምበት ምሳሌ ስጥ። መ) የምንጸልየው ነገር ከልባችን መውጣቱን ወይም ሰዎችን ለማስደነቅ አለመሆኑን በምንድን ነው የምናውቀው? |

## 2. ከእግዚአብሔር ይልቅ ስለ ሌሎች አመለካከት የመጨነቅ ኃጢአት።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቀላሉ የቤተ ክርስቲያን አባላት አመለካከት ወይም የሌሎች ሽማግሌዎች አመለካከት ወይም የመንግሥት አመለካከት በጣም ሊያሳስባቸው ይችላል። ያላቸው ደረጃና እምነት እንዲለዋወጥ ይፈቅዳሉ፣ ወይም ሌሎችን ሰዎች ላለማስከፋት አቋማቸውን ይደብቃሉ። አስቀድመን እንደ ተመለከትነው፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን



ከማስደሰት ይልቅ ሰዎችን በማስደሰት ላይ ያተኩራሉ። ጳውሎስ የሰው አገልጋይ ከመሆን ይልቅ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆንን መርጧል (ገላ. 1:10)። የሰው አገልጋይ ማለት ጳውሎስ ሰዎች ስሕተት ሊሠሩ የተጋፈጠበት ጊዜ ነበር። በገላትያ 2:11-14 ላይ ጳውሎስ፣ ሌሎችን ፈርቶ የሐሰት ትምህርት በቤተ ክርስቲያን እንዲስፋፋ መፍቀድ የጀመረውን ጓደኛው፣ በርናባስን ተቃውሞ ሲቆም እናያለን። ጳውሎስ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታላቁ ሐዋርያና የኢየሩሳሌሟ ቤተ ክርስቲያን መሪ የነበረውን ጴጥሮስን በሕዝብ ፊት ነው ፊት ለፊት የተቃወመው። ጳውሎስ እግዚአብሔርን ለመታዘዝና የወንጌልን ቅንነት ለመጠበቅ፣ ሕዝብን መፍራት እንደሌለበት ተረድቷል።

ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎችን የመፍራትን ተመሳሳይ አመለካከት እንዴት እናያለን? አንዳንድ ጽንፈኛ ዓይነት አምልኮዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸው ብለው የማያምኑ ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አሉ። ነገር ግን አቋም መያዝን ይፈራሉ። «ያንን ካደረግን፣ ወጣቶች በሙሉ ቤተ ክርስቲያናችንን ለቅቀው ሌላ ቦታ ይሄዳሉ» ይላሉ። እነዚህ መሪዎች ሰውን መፍራት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም ብለው የሚያምኑትን ነገር ከመቃወም አግዷቸዋል።

እነዚህ መሪዎች በአንድ ጉዳይ ላይ አቋም መያዝ ያለበት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነና ሚዛናዊነት የጐደለው እንደ ሆነ ሊረዱ ነው። እነርሱ ያልለመዱትን ነገር አንድ ሰው ስላደረገ ብቻ ወይም የማይወዱትን ነገር ስላደረገ ብቻ ጸብ ሊፈጥሩ አይገባም። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ አለባቸው። አንድን ልምምድ የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ እንደሚቃወመው ከተረዱ፣ በቤተ ክርስቲያናቸው እንዲገባ ፈጽሞ መፍቀድ የለባቸውም። [ለምሳሌ፡- ሥላሴን የሚቃወሙ ሰዎች (ኢየሱስ ብቻ)፣ በምስባክ ላይ ሆነው ያትርጉም ልሳን ይናገራሉ (1ኛ ቆሮ. 14:27-28ን ተመልከት)።] የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ

የሚያስቀምጣቸው ጉዳዮች ሲኖሩ ግን፣ እንዴት ስለዚያ ጉዳይ እንደምናስተምር የእግዚአብሔር ጥበብ ያስፈልገናል (ለምሳሌ፡- ወደ ሲኒማ ቤት መሄድ)::

> 30ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ቤተ ክርስቲያን የምታስተምራቸው ነገር ግን በግልጽ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሌሉ ትምህርቶችን ዘርዝር:: ለ) አንዳንድ አማኞች የማይወዷቸው፣ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የማይከለክላቸውን ነገሮች ዘርዝር:: ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪ ብትሆንና አንድ የቤተ ክርስቲያን አባል ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ የሆነ ነገር ሲሠራ ስታየው፣ እንዴት አድርገህ ነው የምታስተካክለው? እውነቱን መከተል እንዲፈልጉ በጽናት መግለጥንና በጨዋነት እነርሱን መመለስን እንዴት አንድ ላይ ታስኬዳለህ? (2ኛ ጢሞ. 2:23-26)

ሰውን መፍራት የቤተ ክርስቲያንን ችግር እንዳንፈታው ከማድረግ ያለፈ ተጽዕኖ አለው:: ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተሰባቸው አባላት ወይም የብሔራቸው አባላት በሚቃወሙት ነገር ላይ አቋም ለመውሰድ ይፈራሉ:: ለምሳሌ፣ አንደኛው የቤተሰባቸው አባል በኃጢአት ቢወድቅ፣ ቤተ ክርስቲያን የሥነ ሥርዓት እርምጃ እንዳትወስድበት ለማድረግ ይጥራሉ:: ወይም አንድ ሰው «አንተ ከእገሌ ብሔር የመጣህ ነህ፣ ስለዚህ ለራስህ ብሔርማ ይህንን ማድረግ አለብህ» ቢለው፣ ሰዎች የራሱን ብሔር አይረዳም ብለው ያስባሉ ብሎ ስለሚፈራ፣ ለራሱ ብሔር ያደላል:: መሪዎች የእግዚአብሔር ቃል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ «ግሪክና አይሁዳዊ» የሚባል ነገር እንደሌለና ሁሉም ብሔሮች እኩል እንደ ሆኑ ይረሳሉ (ገላ. 3:28፤ ቆላ. 3:11):: ወይም አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር የተናቁ ብሔሮችን እንደ ተቀበለ ያውቃሉ (ለምሳሌ፡- ሸክላ ሠሪዎች፣ ቀጥቃጮች፣ ቆዳ ፋቂዎች):: ነገር ግን ሌሎች ያገልሉኛል በሚል ፍርሃት፣ እነዚህን ሰዎች ልክ እንደ ተረገሙ ይቆጥሯቸዋል:: ከእነርሱ ጋር አይነጋገሩም፣ አብረዋቸው አይበሉም፣ ቤታቸው ሄደው አይጎበኟቸውም፣ ወይም አንዳንዴ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ እንኳ አይፈቅዱላቸውም:: አስፈላጊው ነገር ሰውየው የእግዚአብሔር ልጅ



ነው ወይ የሚለው እንጂ፣ ከየትኛው ብሔር መጣ የሚለው አይደለም::

ወይም አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሌላ ሽማግሌ ኃጢአት ሲሠራ አየ እንበል:: ለምሳሌ፣ ሽማግሌው ከቤተ ክርስቲያን ገንዘብ እንደ ወሰደ አወቀ፣ ነገር ግን ከዚያ ሽማግሌ ጋር ወይም ከቤተሰቡ ጋር መጣላት አልፈለገም:: ስለዚህ ዝም በማለት ሽማግሌውን ፊት ለፊት መጋፈጥም ሆነ የቤተ ክርስቲያን የሥነ ሥርዓት እርምጃ እንዲወስድበት አያደርግም:: ወይም እርሱና ሌሎች ሽማግሌዎች በምሥጢር ተሰብስበው ሰውየው እንዳያውቅና የቤተ ክርስቲያን አባላት ስለ ኃጢአቱ እንዳያውቁ ምሥጢራዊ ቅጣት ይጥሉበታል:: አንዳንዴ ደግሞ በግልጽ ስሕተት የሠራን የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ከመቅጣት ይልቅ፣ ቤተ ክርስቲያን ሳዎች ስለ ጉዳዩ ወደማያውቁበት ሌላ ቦታ ታዛውረዋለች::

እነዚህ ሁሉ ምሳሌዎች የሚያሳዩት መሪዎች እንዴት ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰዎችን እንደሚፈሩ ነው:: እነዚህ ሁሉ ኃጢአቶች ንጹሕና የተባበረች ቤተ ክርስቲያን እንዳይኖረን ለይጣን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኃጢአትን የሚያስፋፋባቸው መሣሪያዎች ናቸው::

> 31ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሰውን መፍራት መሪዎች በሚመሩበት መንገድ ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድር እንዳየህ ግለጥ:: ለ) በቤተ ክርስቲያን ንጽሕናና በቤተ ክርስቲያን አባላት አስተሳሰብ ላይ የሚያመጣው ውጤት ምንድን ነው? ሐ) አንተ የቤተ ክርስቲያን መሪ ብትሆን፣ «ሰውን ከመፍራት» ይልቅ «እግዚአብሔርን መፍራት» ምን ያህል ጉዳዮችን በምትይዝበት መንገድ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያመጣ ግለጥ::

## 3. ጤናማ ያልሆነ ጉጉት ኃጢአት፡- በደረጃ ማደግን መፈለግ::

ሰዎች በአመራር ላይ ማደግ ወይም በሰው ዘንድ ያላቸው አክብሮት እንዲጨምር መፈለጋቸው ጤናማ ነው:: እግዚአብሔር በሰጠን ጸጋ በሙላት ማደግ መፈለጋችንም ጤናማ ነገር ነው:: ነገር

ግን ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በመሪነት ሥልጣን ማደግ ወደ መፈለግ ወይም በዓለማውያን ደረጃ ክብር እንዲያገኙ ወደ መፈለግ ማዘንበል ቀላል ነው። ልባችን በቀላሉ ዓለም በሚፈታው መንገድ «ዕድገትን» ሊፈልግ ይችላል። ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪነት ወደ አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት መሪነት፣ ወይም ከዞን አስተዳዳሪነት ወደ አገር አቀፍ መሪነት ማደግ ይፈልጋሉ። እንደዚያ ዓይነት መሻት በልባችን ውስጥ ካለ፣ ለአመራር ያለን የልባችን መሻት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ካሉን ውጫዊ የብቃት ማረጋገጫዎች ተነሥተን በሌሎች ዘንድ ያለን ዝና እንዲጨምር ከፈለግን፣ መሪነትን ኃጢአታዊ በሆነ መንገድ ተረድተናል ማለት ነው።

ዓለም ስኬትን የሚተነትነው በመሪነት ቦታ ላይ ማደግ፣ ከተራ ሠራተኝነት ተነሥቶ የአንድ ክፍል ኃላፊ መሆንና የቢሮ አስተዳዳሪ መሆንና የመሳሰሉት ናቸው። ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያ ትክክለኛ እንደ ሆነ በማሰብ በመሪነት ሥልጣን ማደግን ይፈልጋሉ። ከተራ አባልነት ወደ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌነት፣ ከሽማግሌነት የአውራጃ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌነት፣ ወዘተ . . . ማደግ ይፈልጋሉ። ዓለም ስኬትን የሚፈታው ዓለም የሚያከብራቸው እንደ ትምህርትና ገንዘብን በማግኘት በሰዎች ፊት ክብርን ማግኘት አድርጐ ነው። ብዙ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች «በክብር» እና «በደረጃ» ማደግ የሚፈልጉት ይበልጥ በመማርና ብዙ ክፍያ በማግኘት ነው፣ በዚያም ተጨማሪ ክብርና በሕይወታቸውም ተጨማሪ ጥቅም ማግኘት ይፈልጋሉ።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስኬትን የሚፈታው የትም ብንሆን ወይም ሌሎችን ምንም ያህል ብናከብራቸውም፣ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ መቅረት አድርጐ ነው። ኢሳይያስ በቤተ መንግሥት ውስጥ ሠርቷል፣ ነገር ግን ገበሬ ከነበረው አሞጽ ይበልጥ አልተሳካለትም። ሁለቱንም እግዚአብሔር በነቢይነት



ተጠቅሞባቸዋል። በጥንት ዘመን የነበሩ መንፈሳዊ ሰዎች ከትምህርታቸው የተነሣ የበለጠ የመሪነት ደረጃ ወይም ክብር ቢሰጣቸውም ባይሰጣቸውም ግድ አልነበራቸውም። ስኬታማ መሆን የሚፈልጉት መንፈሳዊ በመሆን፣ ምንም ዓይነት ነገር ቢመጣ እግዚአብሔርን በመታመንና በመሳሰሉት ነበር። ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ሰው በማያስተውላቸው፣ ውጫዊ በረከት በሌላቸውና ሰዎች በማይቀበሉት ነገር ላይ ሕይወታቸውን እንዲሰጡ ይጠይቃቸው ነበር። እግዚአብሔር አንተ የትንሽዬ የገጠር ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሁን ወይም ከተማ ውስጥ የሚገኝ ግዙፍ ቤተ ክርስቲያን ግድ አይሰጠውም። ጥቂት ተማር ወይም ብዙ ግድ የለውም። አስፈላጊው ነገር ግን የትም ያስቀምጠን የትም እግዚአብሔርን በምንችለው አቅም ሁሉ በታማኝነት ማገልገላችን ነው።

ጥንቃቄ ካላደረግን፣ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያለውን አገልግሎት ልክ ዓለም ሥራን እንደሚያየው ልናይ እንችላለን። ራሳችንን ከፍ ወዳለና ወደ ተሻለ አመራር እንገፋለን። ያንን እድገት ካላገኘን፣ እንማረራለን። ይህ አገልጋይ መሪነትን እንዳልተረዳንና የዓለምን መንገድ እንደምንከተል የሚያሳይ ምልክት ነው። ከፍተኛ አክብሮትን ለማግኘት ይበልጥ መማር ከፈለግን የተሳሳተ መሻት ኃጢአት ወሮናል ማለት ነው።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ የእድገት መንገድ ምንድን ነው?

<u>አንደኛ</u>፣ በትክክለኛው ነገር ላይ ማተኮር አለብን። ለእግዚአብሔርና እርሱ ለሰጠን አገልግሎት ታማኝ መሆንን ልንፈልግ ይገባል። እግዚአብሔር የሚሸልመን ብዙ ስለ ተማርን፣ ብዙ ስላገለገልን፣ የቤተሰብ ውርስ ስላለን፣ ወዘተ . . . ሳይሆን፣ ስለ ታማኝነታችን ነው።

<u>ሁለተኛ</u>፣ ራሳችንን በሥልጣን ለማደግ ወደ ላይ ከመግፋት ይልቅ እግዚአብሔር ሰዎችን ተጠቅሞ እንዲያስነሣን ልንፈቅድ

ይገባል:: ሰዎች ለበሰጠ አገልግሎት ሳይመርጡን በመቅረታቸው በልባችን ከተጐዳን፣ የምናገለግለው ለእግዚአብሔር ዓላማ ሳይሆን ለሥጋችን እንደ ሆነ ያሳያል:: እግዚአብሔር እንደ ፈለገ ከፍ እንዲያደርገንና ዝቅ እንዲያደርገን የምናምነው ከሆነ፣ እርሱን መታዘዝ ብቻ የምንፈልግ ከሆነ፣ ከፍ ያለ እድገት አገኘን አላገኘን ግድ አይሰጠንም:: ድጋሚ ባለመመረጣችን ከተጐዳን፣ የምናገለግለው ለእግዚአብሔር ዓላማ ሳይሆን ለሥጋ ፍላጐት እንደ ሆነ የሚያሳይ ምልክት ነው:: ሳንመረጥ ቀርተን ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ስብሳቢነት ተነሥተን ተራ የቤተ ክርስቲያን አባል ስንሆን ፈጽሞ ልንጐዳ አይገባም::

<u>ሦስተኛ</u>፣ ራሳችንን እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ምርጥ መሣሪያ አድርገን ለማሳደግ መፈለግ አለብን:: ምንም እንኳን በደነዝ መጥረቢያ እንጨት መፍለጥ ቢቻልም፣ ብዙ መሥራትን የሚጠይቅና አደገኛ ነው:: መጥረቢያውን የምናስለው የተሻለ እንዲሠራ ነው:: በተመሳሳይ ሁኔታ በምንችለው አቅም ሁሉ እርሱ በሚሰጠን ችሎታና ስጦታ የእግዚአብሔር ምርጥ መሣሪያ መሆንን ልንፈልግ ይገባል:: ያ ማለት ይበልጥ መማርን ለደረጃ ዕድገት ሳይሆን ለአገልግሎት የተሻለ ዝግጅት ለማድረግ እንጠቀምበታለን ማለት ነው:: የተሻለ ትምህርት ካገኘን በኋላ፣ ወደ ቀድሞ አገልግሎታችን የምንመለሰው ተጨማሪ ደመወዝም ሆነ የደረጃ ዕድገት ሳንፈልግ ነው:: በልባችንም ይበልጥ መማርን የተሻለ ገንዘብ ማግኛና አካላዊ ጥቅማ ጥቅሞችና ክብር ማግኛ አድርገን እንዳናስብ ልንጠነቀቅ ይገባናል:: እግዚአብሔር ባስቀመጠን ቦታ መልካም ሥራ መሥራት እስካስቻለን ድረስ እግዚአብሔር በሰጠን የትምህርት ደረጃ ሊበቃን ይገባል::

<u>አራተኛ</u>፣ የትም እናገልግል የትም፣ የልባችን መሻት እግዚአብሔርን ማስከበርና ለእርሱ ታማኝ መሆን በመሆኑ ልባችንን ልንጠብቅ ይገባል:: ጥሩ አገልጋይ ለመሆን የሚጠላ የለም:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሌሎች ባሪያዎች



ናቸው፣ ስለዚህ ለሥልጣን ልንጣላ አይገባም:: ይልቁንም እግዚአብሔር ለዚያ ሲጠራን በትሕትና ልንቀበል ያገባል:: ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ ሊኖረን የሚገባው ብቸኛ መሻት ለእግዚአብሔርና ለሕዝቡ ከሁሉ የሚበልጥ ባሪያ መሆን ነው::

*32ኛ ጥያቄ:- ሀ) ይህ የደረጃ ዕድገት እንዴት ነው አብዛኞዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስኬትን ከሚረዱበት መንገድ የሚለየው? ለ) የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና መሪነትን በዚህ መንገድ ብንረዳ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊኖረው የሚችለውን ለውጥ ግለጥ::*

*33ኛ ጥያቄ:- በዛሬው ትምህርት የተበረዘሩትንና ብዙዎቹ መሪዎች የሚሠሯቸውን ኃጢአቶች ከልስ:: ሀ) የትኞዎቹን ኃጢአቶች ነው ሰይጣን አንተን ለማሸነፍ በተደጋጋሚ የሚጠቀመው? ለ) የትኞዎቹ ናቸው አንተን የማይፈታተኑህ? ሐ) መንፈስ ቅዱስ ኃጢአት የሠራህበትን ቦታ እንዲያሳይህ ለ15 ደቂቃዎች ያህል ጸልይ:: እነዚያን ክፍሎች ሰኄታ ተናዘዝ:: ሰይጣን አንተን የሚያሸንፍበት መንገድ እንዳይኖረው አሠራርህን ለመለወጥ ወስን::*

**አራተኛ ቀን:-** ለሳምንታዊ ስብሰባው ዝግጅት ይሆንህ ዘንድ የሳምንቱን ትምህርት ከልሰ::

## ሳምንታዊ ስብሰባ

### የውይይት ጥያቄዎች:-

1. ሀ) በዚህ ትምህርት ያጠናናቸውንና የቤተ ክርስቲያን መሪ መንፈሳዊ በሆነ መንገድ መምራት እንዲችሉ የሚያስፈልጓቸውን ባሕርያት ዘርዝር:: ለ) እያንዳንዱ ባሕሪ ለቤተ ክርስቲያን መሪ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ሐ) አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያሉዋቸው የትኛዎቹ ባሕርያት ናቸው ብለህ ታስባለህ? መ) ለአብዛኛዎቹ መሪዎች አስቸጋሪ የሆኑት የትኛዎቹ ባሕርያት ናቸው? ሠ) እኛ ያላጠናናቸውን ነገር ግን ለቤተ ክርስቲያን መሪ ያስፈልጋሉ የምትላቸውን ሌሎች ባሕርያት ዘርዝር:: ረ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎችን በዓለም መሥፈርት መሠረት ከመምረጥ

*ይልቅ እንዲህ ያሉ መሪዎችን ለመምረጥ ምን ማድረግ አለብን?*

*2. ሀ) እያንዳንዱ ሰው የጸጋ ስጦታውን ቢረዳና የጸጋ ስጦታው በሚሠራበት አገልግሎት ቢሰማራ፣ በቤተ ክርስቲያን ያለው አገልግሎት ምን ያህል ይሰወጥ ነበር? ለ) መሪዎች የየራሳቸውን የጸጋ ስጦታ ቢያውቁና እያንዳንዱ ባለው የጸጋ ስጦታ ቢያገለግል፣ የቤተ ክርስቲያን አመራር ምን ያህል ይለወጥ ነበር? ሐ) እርስ በርሳችን የጸጋ ስጦታችን ምን እንደ ሆነ ለማወቅና አገልግሎታችንንም በዚያ ላይ ለማተኮር ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?*

*3. ሀ) እግዚአብሔር መሪዎች በይፋ ስለሚሠሩት ኃጢአት ከተራው ሕዝብ ይልቅ ተጠያቂ የሚያደርጋቸው ለምን ይመስልሃል? ለ) የመሪዎች ኃጢአት በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለውን የኢየሱስ ክብር የሚያጐድፍባቸውን መንገዶች ግለጥ:: ሐ) የመሪው ኃጢአት የቤተ ክርስቲያን አባላትን የሚጐዳበትን መንገድ ግለጥ:: መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ኃጢአታቸውን ከመናዘዝ ይልቅ መደበቅን የሚመርጡት ለምንድን ነው?*

*4. ሀ) ካጠናናቸው የኃጢአቶች ዝርዝር ውስጥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች በአስተሳሰባቸውና በሚያገለግሉበት ምክንያት የሚሠሯቸውን ኃጢአቶች ዘርዝር:: ለ) እነዚህ ኃጢአቶች በቤተ ክርስቲያን መሪውና በቤተ ክርስቲያን ላይ ያመጡትን ውጤት ዘርዝር:: ሐ) ከእነዚህ ኃጢአቶች መካከል በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ ያልተሰመዱት የትኞቹ ይመስሉሃል? መ) ከእነዚህ ኃጢአቶች ውስጥ አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚቸገሩባቸው ኃጢአቶች የትኞቹ ናቸው? ሠ) በተለየ ሁኔታ ለእነዚህ ኃጢአቶች የተጋለጡት ለምን ይመስልሃል? ረ) መሪዎች እነዚህን ኃጢአቶች ለማሸነፍ ይችሉ ዘንድ ለመረዳዳት ምን ማድረግ አለባቸው?*



# ትምህርት ስድስት

## *የመጀመሪያ ቀን:-* የቤተ ክርስቲያን *መሪዎች* በተለየ ሁኔታ የተጋለጡባቸው ኃጢአቶች (ክፍል 2)

በዚህ ሳምንት ሰይጣን ትኩረቱን እንዴት የቤተ ክርስቲያን *መሪዎች* ላይ በማድረግ በኃጢአት ሲፈትናቸው እንደሚችል የጀመርነውን ትምህርት እንቀጥላለን:: *መሪዎች* በኃጢአት ሲወድቁ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ከባድ ተጽዕኖ እንደሚመጣ ያውቃል:: የቤተ ክርስቲያን *መልካም* ዝና ይጐዳል፣ የእግዚአብሔርም ስም ይሰደባል:: ብዙ የቤተ ክርስቲያን አባላትም በቅድስና *መኖርን ያቆማሉ*:: ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን *መሪ* እንደ *መሆናችን*፣ ሰይጣን የቤተ ክርስቲያን *መሪዎች* በተለየ ሁኔታ በተጋለጡባቸው ኃጢአቶች እንዳያሸንፈን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን::

## በልብ ውስጥ የሚሠሩ ኃጢአቶችና የመሪው ዓላማ (ክፍል 2)

ጌታሁን በአካባቢው ከሚገኙ *የመጀመሪያ አማኞች* አንዱ ነው:: ከ40 *ዓመታት* በላይ የቤተ ክርስቲያኒቱ *መሪ* ነበር:: ቤተ ክርስቲያኒቱ ሕንፃ እንድትገነባ *መሬቱ* ሰጥቷል:: ጐብኚዎች ሲመጡ ጌታሁን ሁልጊዜ የሚመሰክርላቸው እንዴት ቤተ ክርስቲያኒቱን እንደ ገነባና ቤተ ክርስቲያኒቱ የተገነባችበትን *መሬት* እንደ ሰጠ ነው:: *ሆኖም*፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ አዲስ የተማረ ትውልድ ተነሣ:: *መሪነቱንም* ከጌታሁን መውሰድ ፈለጉ:: ይህ ደግሞ ጌታሁንን በጣም አስቆጣው:: «በፍጹም *ማንም* ሰው እንደ እኔ ሲ*መራ* አይችልም:: አ*መራሩን* ለሌሎች ሰዎች ከሰጠሁ፣ ይህችን ቤተ ክርስቲያን ያጠፏታል:: ደግሞ ይሄ የ ‹እኔ› ቤተ ክርስቲያን ነው:: *የመሠረትኳት* እኔ ነኝ:: *እንድታድግ ያደረግሁትም* እኔ ነኝ:: ስለዚህ እስከምሞት ድረስ ልመራት ይገባኛል» ብሎ አሰበ::

1ኛ ጥያቄ:- ሀ) በምን ዓይነት መንገዶች ነው ለረጅም ዓመታት ቤተ ክርስቲያንን የመሩ መሪዎች በቀላሉ እኛ ከሌለን ቤተ ክርስቲያኒቱ ልትቀጥል አትችልም ብለው የሚያስቡት? ለ) እንደዚህ ባለው አመለካከት ውስጥ ያለው ኃጢአት ምንድን ነው?

ዛሬ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በልባቸውና በዓላማቸው ላይ ስሚፈጽሟቸው ኃጢአቶች የምናደርገውን ጥናት እንቀጥላለን። እነዚህን ኃጢአቶች ስታጠና፣ መንፈስ ቅዱስ የእነዚህ ኃጢአት አረሞች በሕይወትህ ካሉ እንዲያሳይህ ጠይቀው። ያሉ ከሆነ፣ ኃጢአቱን ተናዝዝና እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ መኖር ትችል ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ድል እንድታደርግ እንዲረዳህ ጸልይ።

## 4. ትዕቢት:- እኔ ከሌሎች የተሻልኩ ነኝ ብሎ የማሰብ ኃጢአት።

2ኛ ጥያቄ:- ሕዝ. 28:11-17ን አንብብ። ሀ) የጢሮስ ንጉሥ በምን ኃጢአት ነው ተከስሶ ወደ መሬት የተጣለው? ለ) ምሳ. 8:13፤ 16:18፤ ኢሳ. 2:12-17፤ ማቴ. 23:12፤ ያዕ. 4:6ን አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች ሁሉ እግዚአብሔር ስለ ትዕቢት ስላለው አመለካከት ምን ያስተምሩናል? ሐ) ሰዎች፣ በተለይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትዕቢተኛ የሚሆኑባቸውን መንገዶች ግለጥ።

እግዚአብሔር ከኃጢአቶች ሁሉ እጅግ አብልጦ የሚጠላው ኃጢአት ቢኖር የትዕቢት ኃጢአት ነው። ትዕቢት የአብዛኛዎቹ ኃጢአቶች መሠረት ነው። «እግዚአብሔር የሚፈልገውን ሳይሆን እኔ የምፈልገውን አደርጋለሁ» ብለን እንድናስብ የሚያደርገን ትዕቢት ነው። ትዕቢተኛ ስንሆን፣ ሕይወታችንን መቆጣጠር እንፈልጋለን። ትሑት ስንሆን ግን፣ በእግዚአብሔር ላይ እንደገፍና እርሱ ሕይወታችንን እንዲቆጣጠር እንፈልጋለን።

በመጀመሪያ የተፈጸመው የትዕቢት ኃጢአት ነው። ብዙ ምሁራን ኢሳ. 14:12-15፤ ሕዝ. 28:11-17 ላይ ያሉት ጥቅሶች ሰይጣን እንዴት በኃጢአት እንደ ወደቀ የሚያሳዩ ናቸው ብለው ያምናሉ። ለመውደቅ ያበቃው እንደ እግዚአብሔር መሆንና እንደ



እግዚአብሔር መከበር መፈለጉ ነው። ሰይጣን በኃጢአት ሲወድቅ፣ ብዙ መላእክትን በዐመፅ መርቶ ነው፣ ከዚያ በኋላም አዳምና ሔዋንም በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምፁ ፈተናቸው። ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታ እግዚአብሔር በትዕቢት ላይ ያለውን የመረረ ጥላቻና ትዕቢተኞችን ትሑት የማድረግ ቁርጠኝነት ያሳያል። በፈቃደኝነት ራሳችንን ትሑት ካላደረግን፣ በእርሱ ላይ ካልተደገፍን፣ ክብሩን ካልፈለግንና ካልታዘዝነው እግዚአብሔር በኃይል ትሑታን ያደርገናል። ትሑት የማድረግ ሂደት በምድር ላይ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ይህንን ኃጢአት ካልተናዘዝን፣ በሰማይ ቤት ትሑት እንድንሆን እንደረጋለን። ይህ የትዕቢት ኃጢአት ብዙ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ያሸንፋል።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በትዕቢት ኃጢአት የሚወድቁባቸው ብዙ መንገዶች አሉ።

ሀ. በቤተ እምነታቸው ወይም በቤተ ክርስቲያናቸው መጠነ ትልቅነት ላይ የሚነሣ ትዕቢት። ብዙ ጊዜ «ቤተ ክርስቲያናችን ትልቋ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያናት ናት።» ወይም «የቤተ ክርስቲያን ሕንጻችን በከተማው ውስጥ ከሚገኙት ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሕንጻዎች ትልቁ ነው።» ወይም «እኛ እንደ ሌሎቹ ቤተ ክርስቲያናት አይደለንም፤ ትኩረታችን በወንጌል ስርጭት ላይ ነው።» ወይም «መንፈስ ቅዱስ በታላቅ ኃይልና ተአምር በእኛ ስለሚሠራ፣ ከሌሎች ይልቅ መንፈሳዊ ነን።» የሚሉ ንግግሮችን እንሰማለን። እነዚህ ዓረፍተ ነገሮች በሙሉ ከሌሎች የተሻልን ነን ብለን እንደምናስብ ይገልጣሉ፣ ያም ትዕቢት ነው። ሰይጣን እግዚአብሔር ትልቅ ቤተ ክርስቲያን በመስጠት ለይቶ የባረከን ከሌሎቹ የተሻልን በመሆናችን እንደ ሆነ እንድናስብ ያደርጋል።

ለ. በሥራችን ስኬት የሚመጣ ትዕቢት። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለሠሩት ሥራ ምስጋናና ውዳሴ ለመቀበል በጣም ቀላል ነው። «ይህችን ትንሽ ቤተ ክርስቲያን ተቀብዬ ታላቅ ቤተ

ክርስቲያን አደረግኋት።» ወይም «በዚህ ወር ብቻ 20 ሰዎችን ወደ ጌታ አምጥቻለሁ።» ወይም «ሰዎች በጌታ በማደግ ላይ ያሉት ከእኔ ትምህርት የተነሣ ነው።» ወይም «ዛሬ ጥሩ ስብከት ሰበክሁ። ብዙ ሰዎች ጥሩ እንደ ነበር አስተያየታቸውን ገልጠዋል» የሚሉ ዓይነት አባባሎችን እንሰማለን። ታዲያ እነዚህ ሁሉ የትዕቢት አስተሳሰብ እንዳለን ያሳያሉ። ጳውሎስ ስኬት በሕይወታችን የመጣው እግዚአብሔር በእኛ ካደረገው ነገር የተነሣ እንደ ሆነ ይገልጣል (1ኛ ቆሮ. 4:7)። እግዚአብሔር የምናገለግልበትን ጸጋና ኃይል ሰጥቶናል። እግዚአብሔር ነው ቃሉን ተጠቅሞ አንድ ሰው ጌታን እንዲቀበል ያደረገው። እግዚአብሔር ነው በሰዎች ልብ ውስጥ ቃሉን የመማር ጥማትን ያስቀመጠው። እግዚአብሔር ነው ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ ያደረገው። እኛ የእርሱ መሣሪያ ብቻ ነን። መዶሻ ግሩም የሆነ ቤት ሠራሁ ብሎ አይኩራራም። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እኛም በአገልግሎታችን በመጣው ውጤት ልንኩራራ አይገባም። ልክ እንደ መዶሻው፣ እግዚአብሔር ተጠቅሞብናል። ነገር ግን ክብሩ ለእርሱ ይገባዋል። የእግዚአብሔርን ክብር ላለመንካት እንጠንቀቅ። እግዚአብሔር «ክብሬን ለሌላ . . . አልሰጥም» ብሏል (ኢሳ. 42:8)።

ሐ. ያለ እኛ ሥራው ሊሠራ አይችልም፣ ይወድቃል ብሎ በትዕቢት ማሰብ። በልባችን ውስጥ ይህንን ኃጢአት ማየት አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሣ ይሄ አደገኛ ትዕቢት ነው። ይህ ኃጢአት እግዚአብሔር አገልግሎታችንን ሲባርክና ለብዙ ዓመታት በአገልግሎት ላይ ስንቆይ እያደገ የመሄድ አዝማሚያ አለው። ወደ አገልግሎት የምንገባበትና እግዚአብሔር ያንን አገልግሎት ለመባረክ የሚፈልግበት ጊዜ አለ። ነገር ግን እግዚአብሔር እኛን ለማንሣት ወሰነ። ወይም ከቤተ ክርስቲያን ቢሮ ወደ ሌላ ቦታ እንድንዘዋወር ተናገረን። ያኔ «እኔ በዚህ ከሌለሁ ሥራው ይበላሻል። እኔ ጥሩ አድርጌ የምመራውን ያህል ሊመራ የሚችል ሰው የለም» ካልን፣ በልባችን ትዕቢት አለ ማለት ነው። እግዚአብሔር በእኛ ሊሠራ



እንደ መረጠንና ወደ አገልግሎት እንደ መራን ሁሉ፣ ሌላ ሰውን ወደ አገልግሎት በማምጣት አገልግሎቱ እንዲቀጥልና እንዲያድግ ማድረግ ይችላል። ሥራው ለጥቂት ጊዜ ቢጎዳም፣ እግዚአብሔር እያንዳንዱ አማኝ ሌላ ሰውን ሳይሆን እግዚአብሔርን እንዲያምን ይፈልጋል። ሌሎች አማኞችም የተቀባ አገልጋይ ቢኖርም ባይኖርም ለእግዚአብሔር መምራትና አገልግሎት መቀጠል ይኖርባቸዋል። በአገልግሎት ላይ ለረጅም ጊዜ ከቆየን፣ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ከመደገፍ ይልቅ በእኛ ላይ መደገፍ ይጀምራሉ። የእግዚአብሔርን መንግሥት መገንባት ትተን የራሳችንን መንግሥት መገንባት እንጀምራለን። ራሳችንን «እንደ እኔ አድርጎ ሥራውን ሊሠራ የሚችል ሰው የለም» ብሎ ሲያስብ ካገኘነው፣ ትዕቢት በልባችን ለመግባቱ ምልክት ነው። በዚህም ሌሎች ምንም ማድረግ እንደማይችሉና የእኛን ያህል መሥራት እንደማይችሉ እያሰብን ነው ማለት ነው። ስለዚህ ሰዎች እንዲሞክሩት አንፈቅድም። ስለዚህ ጥቂት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሥራውን ሁሉ ለመሥራት ሲሞክሩ፣ አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን አባላት ቁጭ ብለው ይመለከታሉ።

መ. በቤተሰባችን ወይም በዘር ሐረግ ውርሳችን ላይ ያለ ትዕቢት። ከአገሌ ቤተሰብ ወይም ጎሳ ስለ ወጣን ልዩ ዘር ነን ብሎ ማሰብ ቀላል ነው። «እኔ እኮ የወንጌላዊ አገሌ ልጅ ነኝ» ሲባል እንሰማለን። ያ ልዩ ያደርገናል ወይ? እግዚአብሔር የሚመለከተው የእኔን ልብና ታዛዥነት እንጂ፣ በቤተሰቦቼ ያደረገውን ነገር አይደለም። «እኔ እኮ ከእገሌ ብሔር ነኝ። ወንጌል መጀመሪያ የተመሠረተው እኛ ጋ ነው። በመቶዎች የሚቆጠሩ የወንጌል መልእክተኞችን በመላው ኢትዮጵያ ልከዋል» እንላለን በብሔራችን ስንመጻደቅ። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ጎሳችንና ውርሳችን አስፈላጊ አይደሉም። መጽሐፍ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብሔር እንደሌለ፣ አይሁዳዊና ግሪክ የሚባል ነገር እንደ ሌለ ተናግሯል (ገላ. 3:26-29)። እግዚአብሔር ከዚህ በፊት የእኛን

ብሔር መጠቀሙ ዛሬ እኛን ልዩ አያደርገንም:: በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ የምንሆነው በዘመናችን ወንጌል ሰብከናል አልሰበክንም በሚለው እንጂ ስላለፈው ስኬት አይደለም:: ብዙ ድሮ እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው አብያተ ክርስቲያናት አሁን በራስ ወዳድነትና በፀብ ተሞልተዋል:: እግዚአብሔር እንደ በፊቱ ሊጠቀምባቸው አይችልም:: ሰይጣንም የዛሬውን ሕይወታችንን መርምረን ንስሐ እንዳንገባና እግዚአብሔርን እንዳንታዘዝ ባለፈው ስኬት እንድንመጻደቅ ያደርገናል:: እግዚአብሔር እስቀድሞ ስለ ሠራው ነገር ልናመሰግነው ይገባናል፣ በተጨማሪም ከዚህ በፊት እግዚአብሔር በታላቅ ኃይል የሠራባቸውን ሰዎች ምሳሌም ተከትለናል ወይስ አልተከተልንም ብለን ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባል::

ሠ. ምድባችን ከሽክላ ሠሪዎች፣ ከቀጥቃጮች፣ ከፋቂዎችና ከመሳሰሉት ባለመሆናችን በትዕቢት መነፋት:: ወይም በዘራችን ውስጥ ባሪያ ስላልነበረ መኩራት:: እግዚአብሔር መለያየትን የማያደርግ አምላክ ነው:: እርሱ ለሽክላ ሠሪዎች ያለው ፍቅር ለገበሬዎች፣ ለዶክተሮች ወይም ለአስተማሪዎች ካለው ፍቅር ጋር እኩል ነው:: በልባችን ውስጥ ከሌላው እንሻላለን የሚል ምንም ዓይነት አመለካከት ካለ የትዕቢት ምልክት ነው:: ሴት ልጃችንን ለተናቁ ብሔሮች አንሰጥም የምንል ከሆነ፣ ወንጌል እንዲህ ያለውን ግድግዳ እንዳፈራረሰ ገና እንዳልተረዳን ያሳያል (ኤፌ. 2:11-22):: እነዚህ የትዕቢት ምልክቶች ናቸው፣ እግዚአብሔርም ይጠላቸዋል::

ረ. በትምህርት ደረጃችን መኩራራት:: ብዙ ጊዜ ሰዎች የትምህርት ደረጃቸው ልዩ እንደሚያደርጋቸው በማሰብ ሲመጻደቁ እንሰማለን:: «12ኛ ክፍልን ጨርሻለሁ:: በዲግሪ ተመርቂአለሁ:: ሁለተኛ ዲግሪዬን ጨርሻለሁ:: እኔ ዶክተር ነኝ::» ይላሉ:: እነዚህ ምሳሌዎች ሁሉ ሰዎች በግልጽ የሚመጻደቁባቸው ወይም በልባቸው የሚያስቧቸው ናቸው:: እነዚህም የትዕቢት ምልክቶች ናቸው:: እግዚአብሔር ነው ለመማር ዕድልና ችሎታውን የሰጠን፣



ራሳችን አላገኘነውም:: ስለዚህ ለምንድን ነው ጉራ የሚሰማን? እግዚአብሔር እነዚህን ዕድሎች የሰጠን ለክብሩ እንጂ ለእኛ ደረጃን ለመጨመር አይደለም:: በእኛ ላይ ትዕቢትን ከመፍጠር ይልቅ፣ ትሑት ሊያደርጉንና እግዚአብሔር በዚህ መልክ የመረጠን ለአገልግሎቱ እንደ ሆነ እንድንረዳ ሊያደርጉን ይገባል:: በእኛ ውስጥም እነዚህን ነገሮች ለእግዚአብሔር ክብር እንጂ ለራሳችን ጥቅም ያለመጠቀምን ቁርጠኝነት ሊፈጥር ይገባል::

ሰ. ከሌሎች ሰዎች ይልቅ እኛ ይበልጥ መንፈሳዊና ቅዱስ ነን ብሎ መኩራት:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቀላሉ ሌሎችን የሚያጠቋቸው ኃጢአቶች እነርሱን ስለማያጠቋቸው ሊኩራሩ ይችላሉ:: «ፈጽሞ ጫት አልቅምም:: ፈጽሞ በዝሙት ኃጢአት ወድቄ አላውቅም::» ብለን ክርስቲያን ላልሆኑትና ክርስቲያን ሆነው በእነዚያ ኃጢአቶች ለሚፈተኑ ሰዎች እንናገራለን:: የእኛን ያህል «ቅዱስ» ካልሆኑ ሰዎች ልንርቅ ሁሉ እንችላለን:: የእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት በሕይወታችን ባይበዛልን፣ ልክ እንደ እነዚህ ሰዎች በኃጢአት እስራት ውስጥ እንደምንገባ እንዘነጋለን:: ከትዕቢት ይልቅ፣ እግዚአብሔር ከኃጢአት ጋር ለሚታገሉት ሩኅሩኅ በመሆን ልናመሰግነው ይገባል:: ኢየሱስ ቅድስናውን ጠብቆ ግን ለኃጢአተኛ ደግ ነበረ:: የተናቁ ግብር ቀራጮች፣ ሴተኛ አዳሪዎችና የጎዳና ሕፃናት ከኢየሱስ ጋር መሆን ደስ ይላቸው ነበር፣ ምክንያቱም ኢየሱስ ከእነርሱ በመሻሉ ፈጽሞ ትዕቢት አይሰማውም ነበር፣ ይልቁንም ወዳጅነትና ርኅራኄ ያሳያቸው ነበር:: ዛሬ እነዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጽድቅ የሆነ ሕይወት እየመሩ ለኃጢአተኞች ወዳጅነትና ርኅራኄ በማሳየታቸው ምን ያክል ኃጢአተኞች (የዳኑትም ያልዳኑትም ክርስቲያኖች) ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር መሆን ያስደስታቸዋል? ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖችም ክርስቲያን ያልሆኑትም ከመሪዎች ጋር መሆን ምቾት አይሰጣቸውም:: ምክንያቱም ከእነርሱ የተሻሉ ለመምሰል የሚጥሩ በመሆናቸው ነው:: በመንፈሳዊነት ላይ ያለን «ትዕቢት» ከእነርሱ ጋር ይለየናል::

ወይም አንዳንድ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን አባላት ጋር ስናወራ በየቀኑ ለ2 ሰዓታት እጸልያሁ::» «መጽሐፍ ቅዱስን ሁልጊዜ እጠናለሁ» ብለን በግልጽ እንናገራለን:: እንደዚህ ዓይነት አባባሎች በቀላሉ ምን ያህል ከእነርሱ የተሻልን እንደ ሆን እንደምናስብ በዚያ የተነሣ የቤተ ክርስቲያን አባላት እንደ እኛ መንፈሳዊ ባለመሆናቸው ብርቱ ወቀሳ ይሰማቸዋል:: በመንፈሳዊ ዕድገትህ ትዕቢት እንዳይሰማህ ተጠንቀቅ:: ይልቁንም፣ በትሕትና እንደ ኢየሱስ ለመሆን ምን ያህል ብዙ እንደሚቀርህ አስብ::

ሸ. እንደ መሪነታችን የምንወስዳቸው ውሳኔዎች ሁልጊዜም ትክክል እንደ ሆኑ በማሰብ መኩራራት:: መሪዎች ከኩራት ጋር ከሚታገሉባቸው መንገዶች አንዱ ሌሎችን መስማት እንደሌለባቸውና አንድ ጊዜ ውሳኔ ከወሰዱ ትክክል እንደ ሆኑ ማሰብ ነው:: በ2ኛ ዜና 18:1-19:4 መንፈሳዊ የነበረው ንጉሥ ኢዮሳፍጥ ትዕቢት እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን ነቢይ እንዳይሰማ እንዳደረገውና ያም ሕይወቱን ሊያጠፋው እንደ ነበር የሚገልጠውን አሳዛኝ ታሪክ እናነብባለን:: በኩራት የተሞሉ መሪዎች ወደ ስብሰባዎች ሲመጡ አስቀድመው ወስነው ነው:: ሌሎች ሰዎች ያላቸውን አሳብ እንዲናገሩ ሊፈቅዱ ይችላሉ፣ ነገር ግን አይሰሙም:: የራሳቸውን ውሳኔ ለማስፈጸም ግፊት ያደርጋሉ:: ስለዚህ ሌሎችን (መሪዎችንም ሆነ ተራ አማኞችን) መስማትን ልንማርና በውሳኔ አሰጣጥ ላይ እርዳታ ማግኘት ይገባናል:: ሰሎሞን «በአመራር ጉድለት መንግሥት ይወድቃል፤ የመካሮች ብዛት ግን ድልን ርግጠኛ ያደርጋል» (ምሳሌ 11:14) ብሏል::

ወይም መሪዎች ውሳኔ አድርገው በኋላ ውሳኔው መጥፎ ሆኖ ቢገኝ፣ ለወሰዱት ውሳኔ ኀላፊነቱን መቀበልን አይፈልጉም:: ይልቁንም፣ ለውድቀታቸው ሌሎችን ይወቅሳሉ:: መሪ «ተሳስቻለሁ:: ያንን ያደረግሁት ጥሩ መስሎኝ ነበር:: ነገር ግን ስሕተት ነበርኩ» ሲል መስማት የማይገኝ ነገር ሆኗል:: መሪዎች ሰዎች መሆናችንን ልትዘነጉት አይገባም:: ሰዎች እንደ መሆናችን፣



መሪዎች ሁሉ ስሕተት እንሠራለን:: ሁልጊዜም ጥሩ የሆነ ውሳኔ ለመውሰድ የሚያስችል ብቃትና መረጃ የለንም:: ስሕተቶችን ፈጽመን እንደማንሠራ ከማስመሰል ወይም በራሳችን ስሕተት ሌሎችን ከመውቀስ ይልቅ፣ መሪዎች ስሕተታችንን ልንቀበል ይገባል:: ብዙ ጊዜ መሪ ሆነን ስሕተት ብንሠራና ስሕተቱን ብንቀበል፣ ሰዎች ለእኛ ያላቸውን ክብር የሚያጡ አድርገን እናስባለን:: ብዙ ጊዜ ግን የዚህ ተቃራኒ ነው የሚሆነው:: ሁሉም ሰው መሪው ስሕተት እንደ ሠራ አውቋል:: ስሕተቱን ከተቀበለ፣ ድፍረቱን ያደንቁለታል:: ነገር ግን መሪው ያንኑ ስሕተት መደጋገሙን ከቀጠለ፣ ያኔ ነው በሕዝቡ ዘንድ ያለውን ክብር የሚያጣው::

> 3ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርስቲያን መሪ ሕይወት ውስጥ እንደዚህ ያሉት ኩራቶችን እንዴት እንዳየህ አብራራ:: ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትዕቢትን የሚያሳዩባቸውን ሌሎች መንገዶች ዘርዝር:: ሐ) ከእነዚህ የትዕቢት ዓይነቶች ውስጥ የትኛው ነው በጣም የሚያስቸግርህ? ሕይወትህን መርምርና የትዕቢት ኃጢአትህን ለእግዚአብሔር ተናዘዝ:: በትሕትና ትኖር ዘንድ ትዕቢትህን ለማሸነፍ እንዲረዳህ ጸልይ::

ቀ. ሳናውቀው የቀረነውና መማር ያለብን ነገር እንደሌለ በመቁጠር መኩራት:: መሪዎች ብዙ ጊዜ ሁሉን ነገር እንደምናውቅና ተጨማሪ ትምህርት እንደማያስፈልገን እናስባለን:: ይልቁንም፣ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መሄድ የሚገባቸው ተራ አባላት እንጂ እኛ አንዳልሆንን እናስባለን:: የሚገርመው፣ ለሌሎች ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች ውስጥ መግባት ወይም ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መሄድ አስፈላጊ ነው ቢሉም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ክፍለ ጊዜ የሚሳተፉ ወይም በእግዚአብሔር ቃል እውቀት ለማደግ ፈልገው መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት የሚገቡ መሪዎች ጥቂት መሆናቸው ናቸው::

መሪዎች ብዙ ጊዜ በልባችን ያለውን ኃጢአት መቀበል ያስቸግረናል:: ለዚህ ነው ኩራት ሲሰማን በግልጽነት ሲነግሩን

የሚችሉ ታማኝ ጓደኞች የሚያስፈልጉን:: ነገር ግን ኩራታችንን የሚገልጡ ነገሮች እሉ:: ብዙ ጊዜ ስለ ራሳችን፣ ስለ እገልግሎታችንና ስለ ሠራነው ሥራ እናወራለን? እኛ በሠራነው ሥራ ሌላ ሰው እውቅና ሲያገኝበት እንቆጣለን? እኛ የምንፈልገው የመሪነት ቦታ ለሌላ ሰው ሲሰጥ ቁጣ ወይም ቅናት ይሰማናል? ብዙ ጊዜ ከራሳችን ስሕተት ይልቅ የሌሎች ስሕተት ይታየናል? ሳንናደድ እንተቻለን? ሌሎች በሠሩት ሥራ ምስጋናውን እንወስዳለን፣ ወይም ሰዎች ለሠሩት ሥራ ምስጋናውን ለእርሱ እንሰጣለን? ብዙ ጊዜ እኛ ሌሎችን እናመሰግናለን ወይስ መመስገን እንፈልጋለን? ለተሠራው ሥራ እግዚእብሔርን በማመስገኑ ላይ እናተኩራለን ወይስ ሰዎች ምስጋናውን ለእኛ እንዲሰጡት እንፈልጋለን? ለእነዚህ ጥያቄዎች የምንሰጠው ምላሽ «አዎን» ከሆነ በትዕቢት ኃጢእት ወድቀናል ማለት ነው::

በኤር. 9:24 ላይ ልንኮራ የሚገባን እግዚእብሔርን በማወቃችን ብቻ እንደ ሆነ ተነግሮናል:: ዋናው እርሱ ነው:: የትኛዎቹም የምንኮራባቸው ነገሮች ዘላለማዊ ሕይወታችንን የሚቀይሩ እይደሉም:: እነዚህ ነገሮች ከመቃብር በኋላ አይከተሉንም:: ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የጠበቀ ግንኙነት አሁን ባለን ሕይወትም ሆነ በዘላለማዊ ሕይወታችን ላይ ተጽዕኖ ያመጣል:: ከሌሎች ሰዎች ይልቅ እስፈላጊ ነኝ ብሎ ከማሰብና በኩራት ከመውደቅ ይልቅ እግዚአብሔርን በይበልጥ በማወቅ ላይ ብናተኩር እይሻልም?

## 5. ለምንሠራው ሥራ ኀላፊነትን ሳንወስድ የመሪነትን ሥልጣን ማጣጣም እንደምንችል የማሰብ ኃጢእት::

ምንም እንኳን ብዙ ጊዜ ይህንን «ኃጢእት» ባንለውም፣ ሰይጣን መሪዎችን ከሚያሸንፍባቸው መንገዶች ውስጥ ባገኘነው የመሪነት ማዕረግ እንድንደሰት ማድረግና ነገር ግን ከመሪ የሚጠበቀውን ኃላፊነት እንዳንወጣ ማድረግ ነው:: ይህ ትዕቢት ራሱን በመሪው



ሕይወት የሚገልጥበት ሌላው መንገድ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁል ጊዜ አንድ መሪ የመሪነት ሥልጣን ከተሰጠው፣ የመሪነት ሥልጣኑ የሚያመጣለትን አገልግሎቶች በሙሉ የመፈጸም ኀላፊነት አለበት:: እግዚአብሔር በመሪነቱ የሰጠውን ኀላፊነት እንዴት እንደሚወጣ ተጠያቂ ያደርገዋል:: እግዚእብሔር በመሪው ኀላፊነት ላይ እንጂ በመሪው ሥልጣን ላይ አያተኩርም::

ሆኖም፣ ሰይጣን የመሪዎች ትኩረት በመሪነት ሥልጣን ላይ እንዲሆን ያደርጋል:: ብዙ መሪዎች ለመሪነት ሥልጣን በፍጥነት ነው የሚስማሙት:: ነገር ግን ከዚያ የመሪነት ሥልጣን ጋር እብሮ የሚመጣውን ኀላፊነት ለመቀበል ያመነታሉ:: የሚከተሉት ምሳሌዎች ሰይጣን እንዴት መሪዎች ከመሪነት ኀላፊነት ይልቅ መሪ በመሆን ላይ እንዲያተኩሩ በማድረ‘? እንደሚያሸንፋቸው ያሳያሉ:-

ሀ. እንድ ሰው ሽማግሌ እንዲሆን ይመረጣል:: ሰዎች እንዴት እንደሚያከብሩት የሚያሳይ በመሆኑ ያስደስተዋል:: ነገር ግን ያ ሰውዬ በወርሐዊው የሽማግሌዎች ስብሰባ ላይ ከመገኘት በቀር፣ ሽማግሌ በመሆኑ ምንም የሠራው የለም:: መጽሐፍ ቅዱስ ሽማግሌ በቤተ ክርስቲያን ያሉ አባላት በእምነታቸው እንዲያድጉ የማድረግና «የመንከባከብ» ኀላፊነት እንዳለበት ይናገራል:: ያ ደግሞ መሪው ራሱን ለሕዝቡ መሥዋዕት እንዲያደርግ የሚጠይቅ አስቸጋሪ ሥራ ነው:: ሰውየው ራሱንና ጊዜውን ለሌሎች ለመሠዋት ዝግጁ ስላልሆነ፣ በሚችለው ሁሉ ትንሽ ብቻ ለመሥራት ይሞክራል:: እንደዚያ ያለ መሪ እግዚአብሔር በሽማግሌነቱ መወጣት የሚገባውን ባለመወጣቱ በኀላፊነት እንደሚጠይቀው ዘንግቷል::

ለ. እንድ ሰው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ እንዲሆን ይቀጠራል:: ሰውየው መጋቢ በመባሉ ከመደሰቱ ሌላ፣ በደመወዙም ደስተኛ ይሆናል:: ሆኖም፣ ከሥራው እስካልተባረረ ድረስ ሥራውን ጥሩ እድርጎ መሥራቱ አያሳስበውም:: ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር እንድ ሰው መጋቢ ሲሆን የገባውን ቃል ኪዳን

ያያል:: አሁን ሰውየው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ የእያንዳንዳቸው ሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት ኀላፊነት አሰበት:: እግዚአብሔር ያንን ሰው አባላቱን በማወቅ፣ ችግሮቻቸውን በመወጣት፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በማሳደግና እግዚአብሔርን ለማገልገል መንፈሳዊ ስጦታውን እንዲጠቀሙ በማድረግ በኩል በኀላፊነት ይጠይቀዋል::

ሐ. አንድ ሰው ወንጌላዊ ሆኖ ይቀጠራል:: አብዛኛውን ጊዜ ትኩረቱ ወንጌላዊ በሚለው ማዕረጉ ላይ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ግን ለአካባቢው ሰዎች ወንጌልን በመስበክ ተጠያቂ ያደርገዋል:: በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከተቀጠረ፣ በዚያ ቀበሌ ውስጥ ወንጌል የመስበክ ኀላፊነት አሰበት:: በአውራጃ ቤተ ክርስቲያን ከተቀጠረ፣ በዚያ አውራጃ ውስጥ ወንጌልን የማስራጨት ኀላፊነት አሰበት:: ለጠፋት ወንጌልን የመስበክን ኀላፊነት ስለ ተቀበለ፣ በአውራጃው ውስጥ ምን ያህል ወንጌልን በታማኝነት እንደ ሰበከ ተጠያቂ ይሆናል::

መ. የአውራጃዋና የዞኗ ቤተ ክርስቲያን በጋራ የሚጠቀሙባቸው ንብረቶች አሏቸው:: በእነዚያ ንብረቶች ላይ የይገባኛል ጥያቄ ተነሣ:: ወራትን ከፈጀ ኃይለኛ ክርክር በኋላ፣ ንብረቱ ለአውራጃዋ ቤተ ክርስቲያን «ይገባል» በሚለው ይስማማሉ:: የአውራጃዋ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የንብረቱ «ባለቤት» በመሆናቸው ተደሰቱ:: ነገር ግን አጥሩን የማሳደስ፣ ሣሩን የማጨድ ወይም እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ ንብረቶቹን የመንከባከብ ኀላፊነታቸውን አልተወጡም:: እነርሱ በንብረቱ ባለቤትነት ላይ ሲያተኩሩ፣ የእግዚአብሔር ትኩረት ግን ባለቤትነት በሚያመጣው ኀላፊነት ላይ ነው:: የእግዚአብሔርን ንብረት በሚጠብቁበት መንገድ ላይ በኀላፊነት ይጠየቃሉ:: በእግዚአብሔር ዓይን፣ ንብረቱ የሚገባው ለዞኗ ወይም ለወረዳዋ ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን፣ ለራሱ ነው:: ስለዚህም ንብረቱን ወይም የቤተ ክርስቲያን ሕንጻውን ካልተቆጣጠርን፣ ንብረቱን በማባከን



ተጠያቂ እንሆናለን::

አስታውሱ፣ ደስ በሚያሰኘን የኀላፊነት ቦታ ሁሉ፣ ከሥልጣኑ ጋር አብሮ የሚመጣውን ኀላፊነት በታማኝነት እንድንፈጸም እግዚአብሔር በኀላፊነት ይጠይቀናል:: እግዚአብሔር በትሕትና አገልግሎት እንድናገለግል ለባረከን በረከት ሁሉ ለእርሱ ክብርን በሚያመጣ መንገድ ንብረቱን የመጠበቅ ኀላፊነት አለብን:: ሥልጣን ኀላፊነትን ያመጣል፣ ተጠያቂነትንም ያስከትላል::

4ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሰዎች የሥልጣን ቦታ እንዲኖራቸው የሚፈልጉበትን፣ ነገር ግን ሥልጣኑ የሚያመጣውን ኀላፊነት የማይፈጽሙባቸውን ሌሎች መንገዶች ዘርዝር:: ለ) እግዚአብሔር ሥልጣን የሰጠህ አገልግሎቶች ምንድን ናቸው? ያ ሥልጣን የሰጠህ ኀላፊነቶች ምንድን ናቸው? እንዴት ነው ኀላፊነትህን የምትወጣው? ሐ) እግዚአብሔር ለአንተና ለቤተ ክርስቲያንህ የሰጣቸው በረከቶች ምን ምን ናቸው? እነዚያ በረከቶች ያመጧቸው ኀላፊነቶች ምን ምን ናቸው? ቤተ ክርስቲያንህ የእግዚአብሔር በረከት መጋቢ የመሆንን ኀላፊነት ምን ያህል እየፈጸመች ነው? ምን ብታደርግ የተሻለ ይሆናል ብለህ ታስባለህ?

5ኛ ጥያቄ:- ሀ) ነህ. 6:10-13ን አንብብ:: ሀ) ነህምያ እንዲሠራው የተፈተነው በምን ኃጢአት ነው? ለ) ይህ ለምን ኃጢአት የተባለ ይመስልሃል? ሐ) ዛሬ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህንን ኃጢአት እንዲሠሩ የሚፈተኑት እንዴት ነው? መ) ራእይ 1:3ን አንብብ:: ዮሐንስ ራሱን እንዴት ነው የገለጠው? በዚህ መንገድ ራሱን ለምን የገለጠ ይመስልሃል?

## 6. በችግር ጊዜ የመሸሽ ኃጢአት::

ሰይጣን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለማሸነፍ የሚጠቀምበት ኃጢአት ሌሎች የቤተ ክርስቲያን አባላት የማያገኙትን ጥቅም መጠበቅ ነው:: በትዕቢት ተሞልተን ከእነርሱ የተሻለ ሕይወት መምራት እንደሚገባን፣ ትልቅ ቤት፣ ብዙ ገንዘብ፣ ለፋፊ እርሻ፣ ወዘተ. . . ሊኖረን እንደሚገባ እንናገራለን:: ይህ ኢየሱስ የራሱን የቤተ ክርስቲያን መሪነት አገልግሎት ከሚያይበት መንገድ እንዴት

ይለያል። እርሱ ራሱን በጣም ዝቅተኛ ከሆነው ሰው ጋር አመሳሰሏል። ጳውሎስ ሲናገር ኢየሱስ ክብሩን ትቶ ባሪያ ሆነ ይላል (ፊልጵ. 2:6-7)። በዕብራውያን መጽሐፍ ላይ ኢየሱስ ሊቀ ካህናችን የሆነው በመጀመሪያ እኛ እንደ ተሠቃየነው በመሠቃየቱ ነው (ዕብ. 4:14-16)። መሪዎች ከቤተ ክርስቲያን አባላት የተለየ የአኗኗር ዘዬ ሲኖራቸው፣ በመሪውና በሕዝቡ መካከል ክፍተት ይፈጠራል። ከዚያ የተነሣ መሪዎች ውጤታማ በሆነ መልኩ ማገልገል ያቅታቸዋል። አባላት ሁልጊዜ፣ «እርሳቸው አይረዱኝም። ቢታመሙ የሚታከሙበት ብዙ ገንዘብ አላቸው። እኔ ግን ምንም የለኝም። ታማሚዋን ባለቤቴን እንኳን ወደ ጤና ጣቢያ የምወስድበት ገንዘብ የለኝም።» ብለው ያስባሉ። በእኛና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለው ሰፊ ክፍተት የቤተ ክርስቲያን አባላት በችግር ጊዜ በእምነት እንዲጸኑ ለማበረታታት ያለንን ችሎታ ይቀንሰዋል።

በስደት ጊዜም ተመሳሳይ ሁኔታ ይፈጠራል። ለመሪዎች ቤተሰቦቻቸው ተራ የቤተ ክርስቲያን አባላት በሚቸገሩበት ነገር እንዳይሠቃዩ ማድረግ ቀላል ነው። ይህ ነገር የታየው በደርግ ዘመን ነበር። ብዙ መሪዎች ያላቸውን ተጽዕኖ በመጠቀም ልጆቻቸው ወደ ጦር ግንባር እንዳይላኩ አድርገዋል። ነገር ግን ተራው አባል ይህንን የማድረግ ችሎታ ስላልነበረው ልጆቹ ወደ ጦር ግንባር ተልከዋል። ምናልባትም በርካታ አማኞች በደርግ ዘመን እምነታቸውን ለመጠበቅ የታገሉት መሪዎቻቸው በኢየሱስ ላይ ያላቸውን እቋም መጠበቅ ሲገባቸው እምነታቸውን ሲደብቁ ሲሞክሩ ስላዩዋቸው ይሆናል።

ነህምያ ሰው ሊገድለው ስለሚፈልግ እንዲደበቅ ሲነገረው፣ ለእርሱ መደበቅ ኃጢአት እንደ ሆነ ነበር የተናገረው። ያ ኃጢአት ነው፣ ምክንያቱም በእርሱ የመሪነት ደረጃ መሪነት የሚያመጣቸውን መዘዞች መቀበል ነበረበት። እርሱ ከተደበቀ ግንቡን የሚሠሩ ሰዎች ተስፋ ሊቆርጡና ሥራውም ሊቋረጥ



ይችል ነበር። ሐዋርያው ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት ሆኖ የራእይን መጽሐፍ ሲጽፍ፣ «መከራውንና . . . ትዕግሥቱንም ተካፋይ የሆንሁ» ይላል። ሽማግሌ እንደ መሆኑ፣ በሮማውያን እንዳይማረክ ኤፌሶንን መልቀቅ ይችል እንደ ነበረ ጥርጥር የለውም። ወይም ራሱን መደበቅ ይችል ነበር። ለዚያ ማንም ሰው አይወቅሰውም ነበር። «የቀረኸው ብቸኛው ሐዋርያ አንተ ነህ። ራስህን ልትጠብቅ ይገባል። መሪ እንፈልጋለን። ስለዚህ አሁን ተደበቅ፣ ነገሮች ሲስተካከሉ እንጠራሃለን» ብለው ሌሎች ሊከራከሩ ይችላሉ። ነገር ግን ዮሐንስ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ መሪ እንደ መሆኑ መጠን፣ መደበቅ እንደሌለበትና ተራ አማኞች ብቻቸውን መከራ እንዲቀበሉ ማድረግ እንደማይገባው ተረድቷል። እንዴት በእምነት መከራን እንደሚቀበሉ ሊያሳያቸው ይገባል። ስለዚህ ወደ እስር ቤት ሄደ። መሪዎች አባላቶቻቸው ሊያመልጡ ከማይችሉት መከራ ለማምለጥ ሲሞክሩ፣ በቤተ ክርስቲያን አባላት ላይ ተስፋ መቁረጥን ያመጣሉ። በእምነት ጸንቶ መቆምን የሚያሳያቸው ምሳሌ የሚሆን ሰው በማጣታቸው፣ ብዙ የቤተ ክርስቲያን አባላት እምነታቸውን ይደብቃሉ። በመከራ ጊዜ መሪዎች ሊጠፉና ያም ተራውን አባል ተስፋ ካስቆረጠ፣ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ነው።

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ራሳቸውን ከተራው የቤተ ክርስቲያን አባላት የሚለዩባቸውና በአገልግሎት ላይ ያላቸውን ውጤታማነት የሚቀንሱባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ለ) ተራው አባል ከችግር ሊያመልጥ የማይችልባቸው ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊደበቁ የሚችሉባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ይህ ነገር በቤተ ክርስቲያን አባላት እምነት ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ ምንድን ነው? |

## ሁለተኛ ቀን:- የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በተለየ ሁኔታ የሚገለጡባቸው ኃጢአቶች (ክፍል 3)

### የልብ ኃጢአቶችና የመሪው ዓላማ (ክፍል 3)

7. ገንዘብን የመውደድ ኃጢአት:- በገንዘብ ጉዳይ ቅንነትን አለማሳየት

አቶ ስንታየሁ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ያዥ ለመሆን የተመረጡ የተከበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነበሩ። ሰዎች እርሳቸው እምነት የሚጣልባቸው ሰው እንደ ሆኑ ያውቃሉ፣ ስለዚህ የመባውና የአሥራቱ ገንዘብ ኃላፊነት በእርሳቸው በመያዙ ደስ ተሰኙ። አንድ ቀን የአቶ ስንታየሁ ልጅ ታመመች። ወደ ሆስፒታል የሚወስዱበት ገንዘብ ግን አልነበራቸውም። ስለዚህ «ከቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ተበድሬ በኋላ እከፍላለሁ» ብለው በማሰብ፣ ከመባው ገንዘብ ላይ ወሰዱ። ነገር ግን ገንዘቡን መመለስ ረሱ። ከተወሰነ ጊዘ በኋላ ታላቅ ልጃቸው አገባ። ለድግሱ የሚሆን ገንዘብ አልነበራቸውም። ስለዚህ በድጋ ከቤተ ክርስቲያን ገንዘብ «ተበደሩ»። «ወደ ፊት ላሜን ስሸጥ፣ ገንዘቡን እከፍላለሁ» ብለው አሰቡ። ነገር ግን ላማቸውን ሲሸጡ፣ ሌላ አጣዳፊ ችግር ስለነበረባቸው፣ ገንዘቡን ሳይመልሱ ቀሩ። አንድ ቀን የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያኒቱን ሕንፃ ለማስፋፋት ወሰኑ። የቆርቆሮ መግዣ እንዲሆናቸው ጋሽ ስንታየሁን ገንዘቡን ብለው ሲጠይቁ በጣም ትንሽ ገንዘብ ብቻ ያገኛሉ። ሽማግሌዎቹ አቶ ስንታየሁ ገንዘቡን እንደ ወሰዱ አወቁ። ነገር ግን እንዳይታወቅባቸው፣ አቶ ስንታየሁ በሌላ ጉዳይ ላይ ጭቅጭቅ በማንሣት ቤተ ክርስቲያኒቱን ለቅቀው ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ሄዱ። ኃጢአታቸውን ተናዝዘው የወሰዱትን ገንዘብ የሚከፍሉበትን መንገድ ከመፈለግ ይልቅ፣ እፍረው ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ኮበለሉ። ከመባው ገንዘብ «የተበደሩትን» ገንዘብ ፈጽሞ ሳይከፍሉ ቀሩ። ከዚያ በኋላ አቶ ስንታየሁን የሚያምንና የሚያከብር ሰው ጠፋ። መልካም ዝናቸው ጐደፈ።

> 7ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አቶ ስንታየሁን ወደ ኃጢአት የመራቸው ምንድን ነው? ለ) በተሳሳተ መንገድ ላንጀምረው በኋላ ቀስ በቀስ እያደገ በሚሄድ ነገር ቀስ በቀስ በኃጢአት መውደቅ ቀላል የሆነው ለምንድን ነው? ሐ) ብዙ ጊዜ ገንዘብ ሰይጣን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን የሚያሸንፍበት ዋንኛ መሣሪያ ለምን እንደ ሆነ አብራራ። በእናንተ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተከበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ የደረሰ ተመሳሳይ ነገር ካለ ግለጥ።



> 8ኛ ጥያቄ፡- ምሳሌ 22፡1ን አንብብ። ሀ) ሰሎሞን ሐብታም ከመሆን ይልቅ አስፈላጊ ነው ያለው ምንድን ነው? ለ) ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጥሩ ዝና አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

ጥሩ ዝና የመንፈሳዊ አመራር መሠረት ነው። አስቀድመን በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ከምንመራባቸው ዋነኛ መንገዶች አንዱ ሕይወታችንን ምሳሌ በማድረግ እንደ ሆነ ተመልክተናል። ወይም ሌሎችን የምንመራው በዝናችን ነው ልንል እንችላለን። በምድር ላይ ከኖሩት እጅግ ጥበበኛ ሰዎች አንዱ የሆነው ሐብታሙ ንጉሥ ሰሎሞን ይህንን እውነት ተረድቷል። ስለዚህ መልካም ስም በምድር ላይ ያለን ገንዘብ ከማግኘት እንደሚበልጥ ተናግሯል። ሰዎች የሚያከብሩን በመልካም ዝናችን ነው፣ ምሳሌአችንንም ሊከተሉ ይፈልጋሉ። መጥፎ የሆነ ዝና የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን የመምራት ችሎታ ያሳጣል። ሰዎች እነርሱን ማመን ከማቆም አልፈው እንደ እነርሱ መሆንን ያቆማሉ። እንደ አለመታደል ሆኖ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በኃጢአት ሲወድቁ፣ የቤተ ክርስቲያን አባሎችም በኃጢአት መውደቅ ይጀምራሉ። ከዚያ የተነሣ የቤተ ክርስቲያኒቱና የክርስትና መልካም ስም ይጐድፋል።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የምንመራው ባለን መልካም ዝና እንደ ሆነ ሊያስታውሱ ይገባል። መልካም ዝናን ስለ ማግኘት የሚከተሉትን እውነቶች ማስታወስ አስፈላጊ ነው፡-

1) መልካም ዝናን ማግኘት ረጅም ጊዜ የሚወስድ ነገር ነው። ሰዎች ከልባቸው እንዲያምኑንና ምሳሌእችንን እንዲከተሉ በቋሚነት ለረጅም ጊዜ መንፈሳዊ ባሕሪን ማሳየት አለብን። በአዲስ ኪዳን ያሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች «ሽማግሌዎች» ከሚባሉባቸው ምክንያቶች አንዱ መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች መንፈሳዊ ባሕሪን ለማሳደግና መልካም ዝናን ለማዳበር ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው ስለሚያምን ነው።

2) መልካም ዝና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊጠፋ ይችላል። ሰዎች

መሪን ለማመን ረጅም ጊዜ ሲወስድባቸው፣ ኃጢአት የሆነ ነገር ስንሠራ ሲያዩን ወይም እንደ ሠራን ሲሰሙ ለእኛ ያላቸውን ክብርና እምነት ወዲያውኑ ሲያጡት ይችላሉ። በአንድ ትልቅ ኃጢአት ስንወድቅ ለዓመታት የነበረን መልካም ዝና ይናዳል።

3) መልካም ዝናን ለመጠበቅ ሊያሳስበን የሚገባው ኃጢአት ብቻ ሳይሆን፣ የኃጢአቱ መገለጫም ጭምር መሆን አለበት። እንዱ የ1ኛ ተሰ. 5:22 ትርጉም «ከኃጢአት መገለጫዎች ይከልከሉ» ይላል። ስለዚህ ከመባው ገንዘብ ላይ ገንዘብ በመውሰድ ኃጢአት አለመሥራት አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ሰዎች ከመባው ገንዘብ እንደምንወስድ እንዳይገምቱ ጥንቃቄ ማድረግም አስፈላጊ ነው። ከዝሙት ነፃ መሆንም አስፈላጊ ነው፤ በተጨማሪም ሰዎች ዝሙት የሠራን ሊመስላቸው ከሚችለው ነገር መጠንቀቅም አስፈላጊ ነው። ስለዚህ አንድ ሽማግሌ ለአንዲት ሴት ሲጸልይ ማንም ሰው ኃጢአት እንዳልተሠራ ሊያውቅ ይገባል። በሮቹንና መስኮቶቹን ዘግተን ጸልየን ከሴት ጋር ስንወጣ በጣም የከፋ ነገር ያደረግን ነው የሚመስላቸው። ወይም ሁለት የመዘምራን ቡድን አባላት፣ ወንድና ሴት ሆነው፣ እሑድ ማለዳ የሚዘምሩትን መዝሙር ብቻቸውን ሲለማመዱ ቢቆዩ፣ ሰዎች ዝሙት እንደ ሠሩ ሊያስቡ ይችላሉ። አንድ ጊዜ ሰዎች ኃጢአት የሠራን ከመሰላቸው፣ ኃጢአቱን እንዳልሠራን ለማግለጥ ወይም ስለ እኛ ያላቸውን አመለካከት መቀየር በጣም አስቸጋሪ ነው። ኃጢአት እንደ ሠራን የሚያምኑ ከሆነ፣ ሰዎች ፈጽሞ አያምኑንም። መልካም ስማችንንም እናጣለን።

9ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በአንድ ኃጢአት የተነሣ የአንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ዝና እንዴት በቀላሉ ሊበላሽ እንደሚችል አብራራ። ለ) አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ስሕተት ሳይሠራ ሰዎች ስሕተቱን እንደ ሠራ ከማመናቸው የተነሣ እንዴት መልካም ስሙ ሲጠፋ እንዳየህ አብራራ። ሐ) ያ መሪ በመንፈሳዊነቱ ያገኘው መልካም ዝና እንዳይበላሽ ምን ማድረግ ነበረበት? መ) በአማኞችና በዓለማውያን ፊት ያለህን መልካም ዝና ለማላደግ ምን በማድረግ ላይ ትገኛለህ?



10ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ጢሞ. 6:3-10ን አንብብ። ሀ) በዚህ ክፍል ላይ ጳውሎስ ገንዘብ በሰዎች ሕይወት ስለሚያመጣው ተጽዕኖ ምን ዓይነት ማስጠንቀቂያ ይሰጣል? ለ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የጳውሎስ ማስጠንቀቂያ እውነት እንደ ሆነ እንዴት እንዳረጋገጥክ አብራራ።

በሕይወታችን ውስጥ የግልና የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ አጠቃቀምን ያህል የቤተ ክርስቲያን መሪን መልካም ዝና በተደጋጋሚ የሚያጠፉ ነገሮች ጥቂት ናቸው። በ1ኛ ጢሞ. 6:5-10 ላይ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እምነታቸውን ለገንዘብ ማትረፊያ ከሚጠቀሙት እንዲጠነቀቅ ይነግረዋል። እርሱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትኩረታቸውን በገንዘብ ላይ ከሚያደርጉ ይልቅ እግዚአብሔር በሰጣቸው ነገር እንዲረኩ ያበረታታቸዋል። ጳውሎስ ለብዙ አማኞች ገንዘብ የማሰናከያ ድንጋይ እንደ ሆነባቸው ተናግሯል። ስለዚህ እኛም መልካም ዝናችን እንዳይጐዳ ከፈለግን፣ በገንዘብ አጠቃቀማችን ላይ ጠንቃቃ መሆን ይኖርብናል። በገንዘብ ላይ ያለን ትኩረት እንዴት ነው የሚያስተን?

ሀ. ለቤተ ክርስቲያን ስንሠራ በደመወዝ ወይም ጥቅም ላይ ከሚገባው በላይ ትኩረት የማድረግ ችግር። የቤተ ክርስቲያን ደመወዝተኛ ተቀጣሪዎች፣ ደመወዛችንን የምናይበት አተያይ መልካም ዝናችንን ሊጨምረው ወይም ሊያጠፋው ይችላል። ደመወዝን በተመለከተ እንደ ወንጌላዊና መጋቢ ያሉት የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ሊያስቡባቸው የሚገቡ ነገሮች ምንድን ናቸው?

1) የደመወዛችን መጠን መልካም ዝናችንን ሲያጠፋ አይገባም። እንደ ወንጌላዊና መጋቢ ሆነን ስንሠራ የሚከፈለን ገንዘብ የምናገለግለው ለገንዘብ እንደ ሆነ የሚያመለክት ከሆነ፣ ሰዎች እኛን አያከብሩንም ወይም አይከተሉንም። ትምህርታችንን ሊወዱት ይችላሉ። ነገር ግን በልባቸው፣ «እንደ እገሌ ዋጋ ከፍዬ ማገልገል አለብኝ» አይሉም። የምንመራው ሕዝብ እኛ እንደዚያ ብናስብም ስለ መሪነት ያለው አስተሳሰብ የሥጋ ይሆናል። በ1ኛ ቆሮ. 9:6-18

ላይ ጳውሎስ ማንም ሰው ስአገልግሎት ያለውን መልካም አሳብ ጥያቄ ውስጥ እንዳይከትበት ከጊዜያዊ ስጦታዎች በስተቀር ገንዘብ የሚባል ነገር እንዴት አልቀበልም እንዳለ ተናግሯል።

2) የገንዘብ አከፋፈልን በተመለከተ የትምህርት ደረጃ እንደ መሥፈርት ሊታይ አይገባውም። የዚህ የጸሐፊው የግል አመለካከት በቤተ ክርስቲያን ያሉ ሰዎችን በዓለም ደረጃ መክፈል አለብን ብሎ ማሰብ አደገኛ እንደ ሆነ ነው። «እንዴት ይህችን ብቻ ትከፍሉኛላችሁ? እኔ እኮ ዲግሪ አለኝ፣ ብዙ ሊከፈለኝ ይገባል። ያ ለእኔ ስድብ ነው።» ካልን፣ የምናገለግለው ጥሪ ስላለን ወይም እግዚአብሔርንና ሕዝቡን ስለምንወድ ላለመሆኑ ግልጽ ነው። እግዚአብሔር ባለን የትምህርት ደረጃ አይደነቅም፣ ነገር ግን እርሱን የሚወድና ውጤታማ አገልግሎትን ሊያመጣ የሚያስችል ባሕሪ ያለውን ሰው ይፈልጋል። ደመወዝ ሊከፈል የሚገባው ውጤታማ ለሆነ አገልግሎት እንጂ ለትምህርት ደረጃ አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔርንና ቤተ ክርስቲያንን የምናገለግለው ጥሩ ሕይወት ለመኖር ፈልገን እንደ ሆነ መምሰል የለበትም።

3) ከአንድ አገልግሎት ወደ ሌላ አገልግሎት ለመቀየር ምክንያታችን የተሻለ ክፍያ ከሆነ፣ በአገልግሎት ላይ ያለንን አመለካከት ልንጠይቅ ይገባል። በማገልገል ላይ ያለነው ከእግዚአብሔር ጥሪ በላለን ሳይሆን፣ ለግል ዕድገት ነው ማለት ነው። የምናገለግለው በትልቅ ቤተ ክርስቲያን ይሁን በትንሽ ቤተ ክርስቲያን ሊያሳስበን አይገባም። ወደ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን የመግባት ዕድል ስናገኝ፣ ዕድሉን ልንጠቀም የሚገባው ከጸለይንና የእግዚአብሔርን ምሪት ከተቀበልን በኋላ፣ እግዚአብሔር በዚያ እንድናገለግለው እንደሚፈልግ ስናረጋግጥ ብቻ ነው። ውሳኔአችን በቀዳሚነት በደመወዝና በማዕረግ ዕድገት ላይ ያተኮረ መሆን የለበትም።

4) የደመወዝ መጠን ለአንድ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኛ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ሊያገለግል የሚችልበት ምክንያት መሆን



የለበትም። አንድ ሰው «ስንት ትከፍሉኛላችሁ?» ወይም «የውሎ አበል አለው፣ የጡረታ አበል አለው፣ የነፃ ሕክምና አገኛለሁ፣ የትምህርት ዕድልስ?» ወዘተ. . . ብሎ የሚጠይቅ ከሆነ፣ ሁለት ነገሮች ይሆናሉ። አንደኛ፣ ያ አገልጋይ ሰይጣን ለአገልግሎት ያለውን ተነሣሽነት እንዲያበላሽ ፈቅዷል ማለት ነው። ሁለተኛ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት ሰውየው የሚያገለግለው ስገንዘብ ብሎ ነው ብለው በለሚያስቡ፣ ለእርሱ ያላቸው ክብር ይቀንሳል።

5) የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ከቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ጋር ሲነጻጸር መካከለኛ ገቢ ቢኖረው መልካም ነው። ደመወዝ በቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች የትምህርት ደረጃ ላይ የተመሠረተ መሆን የለበትም። በ2ኛ ቆሮ. 8:13-15 ላይ ጳውሎስ አንዱ ሀብታም አንዱ ድሃ እንዳይሆን ሁሉም እኩል ሊከፈለው ይገባል ነው የሚለው። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ከተራው ሕዝብ የሚበልጥ የሚያገኙ ከሆነ፣ በሕዝቡ ገንዘብ ሀብታም ሆኑ ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን፣ እግዚአብሔር የ«አሥራት»ን ሕግ ያወጣው ለሌዋውያን ደመወዝ ለመክፈል ነው (ዘኁል. 18:20-32፤ ዘዳግ. 26:12-15)። አሥራ ሁለቱ ነገዶች ከምርታቸው ላይ ለእግዚአብሔር አሥራት ሲከፍሉ፣ የተወሰነው ገንዘብ ለካህናት አገልግሎት ይከፈለው። ያ ማለት ሌዋውያን ሁልጊዜ ከሌሎቹ ነገዶች ጋር የተመጣጠነ የኑሮ ደረጃ ይኖራቸዋል ማለት ነው። ብዙ ምርት ካልተገኘ፣ ሌዋውያን ከሕዝቡ እኩል ይጐዳሉ። ብዙ ምርት ሲኖር፣ ሌዋውያንም ብዙ ያገኙ ነበር። የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ስንት ያገኛል ለሚለው ይህ ፍትሐዊ መልስ አይደለም?

6) ቤተ ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላሉ አገልጋዮች ስንት እከፍላለሁ የሚለው ጥያቄ ሊያሳስባት ይገባል። ጳውሎስ «ሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል» (1ኛ ጢሞ. 5:17-18) ይላል። በለዚህ በቤተ ክርስቲያን ለሚያገለግሉ ሰዎች ቤተ ክርስቲያኒቱ ከሕዝቡ እኩል ሊያኖራቸው የሚችል ጥሩ ክፍያ ልትከፍል ይገባል። (ማስታወሻ፡- አብዛኛውን ጊዜአቸውን በቤተ ክርስቲያን ለሚያገለግሉ

ሰዎች በቂ ክፍያ አለመክፈል በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ነው፣ ምክንያቱም በዚህ መንገድ የሚያገለግሉንን እንድንከፍላቸው እርሱ ስላዘዘ ነው።) «እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ነገር ያሟላላቸዋል፣» ወይም «እግዚአብሔርን ስለሚያገለግሉ የተባረኩ ናቸው» ብሎ በማሰብ ጥቂት ብቻ መክፈል መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። ያ በቤተ ክርስቲያን ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ያመጣል። ያ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚያገለግሉን ሰዎች ያለንን አክብሮትና ፍቅር አያሳይም። የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችንና ቤተሰቦቻቸውን በቂ ገንዘብ ባለመክፈል እንዲሠቃዩ ካደረግናቸው፣ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ተስፋ በማስቆረጥና በማጥፋት የሰይጣን መሣሪያ ሆንን ማለት ነው። አገልጋዩ እግዚአብሔርና ሕዝቡ እንደ ተዉት ስለሚያስብ፣ ተስፋ ይቆርጣል። አብዛኛውን ጊዜውን ለራሱና ለቤተሰቡ የሚሆነውን ገንዘብ እንዴት ሊያገኝ እንደሚችል ስለሚያስብ፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሳያገለግል ስለሚቀር አገልግሎቱ ይደናቀፋል።

> *11ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ትኩረታቸውን በደመወዝ ላይ ማድረጋቸው የእግዚአብሔር ጥሪ እንደሌላቸው እንዴት እንደሚያሳይ አስረዳ። ለ) ቤተ ክርስቲያን ፍትሐዊ የሆነ ክፍያ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልትከፍል የምትችልበት ሚዛናዊ መንገድ ምንድን ነው? የትምህርት ደረጃ፣ የቤተሰብ ብዛት፣ የአገልግሎት መጠን፡- ወዘተስ? የትኛው መንገድ ነው ይበልጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው? ሐ) ለምን ይመስልሃል አንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት ለአገልጋዮቻቸው አባላት ከሚያገኙት ገንዘብ ጋር የሚመጣጠን ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ ያልሆኑት? ይህ በእግዚአብሔር ዓይን ትክክል ይመስልሃልን? መልስህን አብራራ።*

ሰ. በቤተ ክርስቲያን በአደራ የተሰጠውን የመባና የአሥራት ገንዘብ በአግባቡ ያለመጠቀም ኃጢአት፡- «ሕዝቡ እኮ ፈጽሞ አሥራትና መባውን ለጌታ ሥራ አይሰጥም። ስለዚህ፣ የቤተ ክርስቲያን ሥራን መሥራትና ለአገልጋዮች ደመወዝ መክፈል አልተቻለም።» የሚል ቅሬታ ምን ያህል ጊዜ ሰምተሃል? የቤተ ክርስቲያን አባላት ለእግዚአብሔርና ለእርሱ ሥራ መስጠት



የሚገባቸውን ያህል የማይሰጡት ለምንድን ነው? አብዛኛውን ጊዜ ችግሩ የሚፈጠረው በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነው። ሰዎች ገንዘባቸው እንዴት ለእግዚአብሔር ሥራ እንደሚውል ካወቁ፣ ገንዘባቸውን ለእግዚአብሔር ሥራ መስጠት ያስደስታቸዋል። ይሄ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር ከምናሳይባቸው መንገዶች አንዱ ነው። ነገር ግን ሰዎች ለእግዚአብሔር ከማይሰጡባቸው ምክንያቶች አንዱ በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አባላት መካከል የሚፈጠር አለመተማመን ነው። የቤተ ክርስቲያን አባላትን እምነት ለማግኘት የምንፈልግ ከሆነ አሥራትና መባ አጠቃቀማችን በጣም አስፈላጊ ነው።

በ1ኛ ቆሮ. 4:1-2 ላይ፣ ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔር «ባለ አደራዎች» ናቸው ይላል። በአዲስ ኪዳን ጊዜ ባለ አደራ የጌታውን ጉዳይ የማስፈጸም ብቃቱን የሚያሳይ ነበር። አገልጋዩ የቤቱ ባለቤት አይደለም ወይም የጌታውን ንብረት በመቆጣጠሩ የሚያገኘው ጥቅም የለም። ይልቁንም፣ አገልጋይ ጌታውን ለመጥቀም በሚችለው ኃይል ሁሉ ይሠራል። ለጌታው ምርጥ የሆነ ነገር ለማስገኘት ሌሎች ባሪያዎችን፣ ገንዘብና አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ይጠቀማል። ታዲያ ከአገልጋይ ምንድን ነው የሚጠበቀው? ጳውሎስ ታማኝነት ነው ይላል። <u>በዚህ ዓይነት ታማኝነት ማለት የእግዚአብሔር ሕዝብና እግዚአብሔር በሙላት እንዲጠቀም የእግዚአብሔርን ገንዘብ በምንችለው ኃይል ሁሉ በጥሩ ሁኔታ ማስተዳደር ነው።</u> በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ አገልጋይ እንደ ሆነ መሪ ልናስታውሳቸው የሚገቡ ብዙ ነገሮች አሉ፡-

1) ሕዝቡ፣ ንብረቱና ገንዘቡ ሁሉ የእግዚአብሔር ነው። የእኛ አይደሉም። የእኛ ግብ እግዚአብሔር ከእነዚህ ሁሉ ከፍተኛውን ጥቅም እንዲያገኝ ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲስፋፋ ባለን ችሎታና ጥበብ ሁሉ ልንጠቀምና የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ልናዳምጥ ይገባል። በጣም ትንሽ የሆነችውን የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ በጥበብ ከተጠቀምን፣ እግዚአብሔር ከፍተኛ ጥቅም

እንድታስገኝ እድርጐ ይባርካታል።

ይህንን ገንዘብ ለራሳችን በምንጠቀምበት ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር ወይም ለሌሎች እየሠራን ሳይሆን፣ ለራሳችን የግል ጥቅም እየሠራን ነው ማለት ነው። ለምሳሌ፣ በጉዞ ወቅት የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ ጥሩ ሆቴል ለማረፍ ወይም ጥሩ ጥሩ ምግቦችን ስመብላት ብጠቀምበት፣ የእግዚአብሔርን ገንዘብ በጥበብ የተጠቀምኩበት ይመስልሃል? ያንን ሳደርግ የመጣውን ገንዘብ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ለሚበልጠው ነገር አልተጠቀምኩም ማስት ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔርን ገንዘብ ወጪ ከማድረጋቸው በፊት «የእግዚአብሔርን ገንዘብ የምጠቀምበት ምርጡ መንገድ ይሄ ነውን? ገንዘቡን በዚህ መንገድ መጠቀሙ የእግዚአብሔርን መንግሥት በተሻለ ሁኔታ ሊያስፋፋ ይችላል ወይ?» ብለው ሊጠይቁ ይገባል። የቤተ ክርስቲያንን የገንዘብ አቅርቦት ስቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ጥቅም ሊያመጡ ለሚችሉ (ለምሳሌ፡- ስዎች በእውቀት ሊያድጉባቸው የሚችሉባቸውን ሥነ ጽሑፎች ለመግዛት፣ ለአገልጋዮች ደመወዝ ለመክፈል፣ አማኞችን ደቀ መዛሙርት ሊያደርጉ የሚችሉ አገልጋዮችን ለመቅጠር) መጠቀም ሲገባን፣ ያን ያህል መንፈሳዊ ጥቅም ለማያመጡ (ለምሳሌ፣ ለመዘምራን ቡድን የሚሆን ልብስ፣ ለሽማግሌዎች ስብሰባ ለሚቀርብ ምግብ) የምንጠቀምበት ከሆነ፣ መልካም ያልሆንን የእግዚአብሔር አገልጋዮች ነን ማለት ነው። እግዚአብሔርም ይፈርድብናል። ገንዘቡን መጠቀም ያለብን በሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅ በሆኑ (እንደ መዘምራን ቡድን ልብስ፣ የሙዚቃ መሣሪያና የተሻለ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ) ነገሮች ከማውጣት ይልቅ፣ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ባላቸው እምነት ሊያድጉ በሚችሉባቸው ነገሮች ላይና የጠፉትን በመድረስ ላይ መሆን አለበት።

2) የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እንደ ባለ አደራነታቸው ተጠሪነታቸው ለእግዚአብሔርና ለሕዝቡ ነው። ለምናደርገው ነገር



በሙሉ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ዘንድ ሙሉ ተጠያቂነት እንዳለብን ልንረዳ ይገባል። እግዚአብሔር በእኛ ኃላፊነት ሥር ያስቀመጠውን ገንዘብ በታማኝነትና በጥበብ እንድንጠቀም ነው የሚፈልገው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያን አባላት ባለ አደራዎችም ናቸው። ሰዎች ገንዘባቸውን የሚሰጡት ለእግዚአብሔር ቢሆንም፣ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ባለ አደራነት ነው የሚያስቀምጡት። የቤተ ክርስቲያን አባላት ገንዘባቸውን ባለን ኃይል ሁሉ ለወንጌል ሥራ እንድናውል ይፈልጋሉ። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአደራነት ለአነርሱ የተሰጠውን ገንዘብ የሚጠቀሙበትን መንገድ በተመለከተ በእግዚአብሔርና በቤተ ክርስቲያን አባላት ዘንድ ተጠያቂ ይሆናሉ።

ሰዎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመባውንና የአሥራቱን ገንዘብ እንዴት እንደሚጠቀሙ በጣም ያሳስባቸዋል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን እስካመኑ ድረስ፣ አባላት በቸርነት ነው የሚሰጡት። ነገር ግን ሰዎች ሀ) ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን አሥራት መሪዎች ለራሳቸው ጥቅም የሚወስዱ መሆኑን፣ ወይም ለ) መሪዎች ገንዘቡን በአግባቡ በጥበብ የማይጠቀሙበት ከሆነ፣ ወይም ለወንጌል ሥራ እንዳልዋለ ከተጠራጠሩ፣ ወዲያውኑ ነው ገንዘብ መስጠት የሚያቆሙት። ስለዚህ እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪነታችን፣ የገንዘብ አጠቃቀማችንን በተመለከተ አምስት ሳንቲም እንኳ ወደ እኛ ኪስ እንዳይገባ በማድረግ ንጽሕናችንን ልንጠብቅ ይገባል። በሳንቲም ደረጃ እንኳን ፍጹም ታማኝ ስመሆን ልንወስን ይገባል። በተጨማሪም፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት ገንዘባቸውን በሚገባ እንደ ተጠቀምን እርግጠኛ በሚሆኑበት መንገድ ልንጠቀም ይገባል።

በእግዚአብሔር ባሕሪ የምንመራ ከሆነ፣ በቅድሚያ በእኛና በቤተ ክርስቲያን አባላት ዘንድ መተማመን የሰፈነበትን ግንኙነት በመፍጠር እንመራስን። ያንን መተማመን በጥንቃቄ ልንጠብቅ ይገባል። ያንን መተማመን የሚያፈርስ ማንኛውም ነገር የቤተ

ክርስቲያን ጠላትና የሰይጣን መሣሪያ በመሆን የእግዚአብሔርን ሥራ ለማደናቀፍ ይሠራል። ሰይጣን የቤተ ክርስቲያን አባላት ገንዘባቸውን ለእግዚአብሔር ሥራ እንዳይሰጡ ለማድረግ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ሊጠቀም ይችላል። የቤተ ክርስቲያን አባላት አሥራትና መባቸውን ካልሰጡ፣ ለእግዚአብሔር በልግስና በመስጠት የሚገኘውን በረከት አይቀበሉም።

## የቤተ ክርስቲያን አሥራትና መባን ስንይዝ ልናስታውሳቸው የሚገቡ አስፈላጊ ነገሮች ምንድን ናቸው?

1) የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ ፈጽሞ ብቻችንን ልንቆጣጠር አይገባም። የቤተ ክርስቲያን መሪ ወይም ዲያቆናት በቤተ ክርስቲያን ገንዘብ አያያዛቸው ላይ የሚመጣ ማናቸውም ዓይነት ጥርጣሬን የሚገድብ ጥሩ የሆነ አሥራር መኖር አለበት። «እነርሱ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አይሠርቁም ብለው ያምናሉ። ስለዚህ፣ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ አጠቃቀምን በተመለከተ ለምን ወደዚያ እንሄዳለን?» «በጣም ግልጽ የሆነ ተጠያቂነት መኖር አለመታማመን መኖሩን አያሳይም?» ብለን እንጠይቅ ይሆናል። ነገር ግን ሁልጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገንዘብ የሚይዙ ቢያንስ ሁለት ሰዎች ካሉ ጥሩ የሆነ የገንዘብ አያያዝ ሊኖረን የሚችልባቸው ሁለት ምክንያቶች አሉ።

<u>አንደኛ</u>፣ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ በኃላፊነት የማይዘውን ሰው የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ለራሱ ጥቅም ለማዋል እንዳይፈተን ይገድበዋል። ገንዘቡን ብቻችንን በኀላፊነት ለንቆጣጠር ሰይጣን ፈጥኖ ያሸንፈናል፣ ማንም ሰው ሳያውቅ ትንሽ ትንሽ ልንሰርቅ እንችላለን። ነገር ግን ሌላ ሰው ካለ፣ አንዳችን የአንዳችንን ንጽሕና ለመጠበቅ እንረዳዳለን።

<u>ሁለተኛ</u>፣ ገንዘቡን ይወስዳሉ የሚል ጥርጣሬን ያስወግዳል። መልካም ዝናችንን እንደ ጠበቅን እንድንቆይ ይረዳናል። አስታውስ፣ ሊያሳስበን የሚገባው ከኃጢአት መጠበቅ ብቻ ሳይሆን፣ ከክፉት



መገለጫዎች በመራቅ መልካም ዝናችንን መጠበቅ ሊሆን ይገባል።

በዕዝራ 8:24-34 ላይ የፋርስ ንጉሥና በፋርስ የቀሩት አይሁዳውያን እንዴት ለዕዝራ በኢየሩሳሌም ያለችውን መቅደስ ለመገንባት ገንዘብ እንደ ሰጡት እናነብባለን። ዕዝራ ገንዘቡ ለእግዚአብሔር ሥራ እንዲውል እንጂ ለራሱ እንዳልሆነ በመረዳቱ ገንዘቡን ለሌላ ነገር አላዋለውም። ዕዝራ ማንም ሰው የልቡን ቅንነት በተመለከተ ጥርጣሬ እንዲገባው ስላልፈለገ ከገንዘቡ ጋር አልተነካካም። ይልቁንም፣ አሥራ ሁለት ታማኝ ሰዎችን መርጦ ለገንዘቡ ኃላፊዎች እንዲሆኑ ሾማቸው። በእነርሱ ፊት፣ ገንዘቡን ቆጥሮ ሰጣቸው። አይሁዳውያን ኢየሩሳሌም ሲደርሱ፣ ገንዘቡን በድጋሚ ቆጠረው። ከዚያም ለመቅደስ ሥራ እንዲውል ለካህናት ተሰጠ። በመንፈሳዊነቱ የሚታወቀው ዕዝራ ቅንነቱን ለመጠበቅ ያንን ካደረገ፣ እኛም ያንን ማድረግ ያለብን አይመስልህም? ሁሉም ሰው የሚሰጡት ገንዘብ በምን ሁኔታ ላይ እንደ ዋለ እንዲያውቁ ለማድረግና ለአሥራት የሚሰጡትን ገንዘብ በሚቆጣጠሩት ሰዎች ላይ ያላቸው እምነት እንዲጨምር ለማድረግና የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ ለመቆጣጠር ጥሩ አሠራር መዘርጋቱ መንፈሳዊ ጥበብ ነው።

ይህ ማለት አሥራትና መባው ሲሰበሰብ፣ ቢያንስ ሁለት ዲያቆናት ወይም ሽማግሌዎች ገንዘቡን መቁጠር አለባቸው ማለት ነው። ለቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ያዥ ገንዘቡን ሲሰጡ፣ የተሰጠው ገንዘብ ጠቅላላ ድምር ተመዝግቦ መሆን አለበት። ዲያቆናት የተሰጠውን የገንዘብ መጠን በተመለከተ በመዝገቡ ላይ መፈረማቸው ጥሩ ነው። ባንክ ባለባቸው አካባቢዎች ያሉ ቤተ ክርስቲያናት ደግሞ፣ ገንዘቡን ለመጠበቅ ሲባል በሁለት ሰዎች ፊርማ የሚንቀሳቀስ የባንክ ሂሳብ መክፈታቸው አስፈላጊ ነው። ምን ያህል ገንዘብ ገቢ እንደ ተደረገና ምን ያህሉ ደግሞ ለልዩ ልዩ ወጪዎች እንደ ዋለ የሚገልጥ የሂሳብ መዝገብ መዘጋጀት ይኖርበታል። ገንዘቡን የምናስቀምጥበት ባንክ ከሌለ፣ ገንዘብ ያዥ

በቤቱ በሁለት ቁልፍ የሚቆለፍ ሳጥን ያስፈልገዋል:: የአንደኛው ቁልፍ እርሱ ዘንድ ሌላኛው ቁልፍ ደግሞ የሽማግሌዎች ሰብሳቢ ጋ ሊሆን ይገባል:: ገንዘብ ሲያስፈልግ፣ ሁለቱም ሰዎች ቁልፉን ከፍተው ገንዘቡን ሊያወጡና ገንዘቡን ማውጣታቸውንም በሂሳብ መዝገቡ ላይ ጽፈው መፈረም አለባቸው:: ገንዘቡ የወጣበትንም ዓላማ መጻፍ አለባቸው:: በወርሐዊ የሽማግሌዎች ስብሰባ ላይ ገንዘብ ያዡ ምን ያህል ገንዘብ እንደ ተቀበለ፣ ምን ያህል ገንዘብ ወጪ እንደ ሆነ፣ ለምን ምክንያት ወጪ እንደ ሆነና በሳጥኑ ውስጥ ምን ያህል የእግዚአብሔር ገንዘብ እንደ ቀረ ማብራራት አለበት:: ቢያንስ በየሦስት ወሩ፣ ሽማግሌዎች ወይም ተወካያቸው በሳጥን ውስጥ ያለውን ገንዘብ ቆጥረው አለመጉደሉን ማረጋገጥ አለባቸው:: ይህ የተጠያቂነት አሠራር ቁልፉን የያዙት ሽማግሌዎች ያላቸውን ቅንነት እንዲጠብቁና ገንዘቡን እንዳያባክኑ ይረዳቸዋል:: የቤተ ክርስቲያን አባላትም ገንዘባቸው በዚህ መልክ ቁጥጥር እንደሚደረግበት ካወቁ፣ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን በይበልጥ ስለሚያምኑ ገንዘቤን ሌላ ሰው ለራሱ ጥቅም ይወስደዋል የሚለው ጥርጣሬአቸው ይቀንሳል:: (ማስታወሻ:- ከኋላ ባሉት ትምህርቶች የገንዘብ አያያዝ ተጠያቂነትን አሠራር በተመለከተ እንመለከታለን::)

| |
|---|
| *12ኛ ጥያቄ:- በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ገንዘብ የሚሰበሰብበትና የሚቆጠርበት አሠራር ምን ይመስላል? ሀ) የገንዘብ አሰባሰቡን በተመለከተ ወይም መባውን የሚሰበስቡት ሰዎች ገንዘቡን ሊወስዱ ይችላሉ የሚለውን ጥርጣሬ ለማስወገድ ቤተ ክርስቲያን ምን ታደርጋለች? ለ) በዚህ አቅጣጫ ሰይጣን ድል እንዳያገኝ ምን ማድረግ አለባቸው?* |

2) አሥራትና መባው ሊውል የሚገባው የቤተ ክርስቲያን አባላት በሚስማሙባቸው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ላይ ነው:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ «ለጌታ ሥራ ገንዘብ ስጡ» ብለን እንናገራለን:: ነገር ግን አንዳንዴ ያንን ገንዘብ ወስደን አስፈላጊ ሳልሆኑ ነገሮች እናውለዋለን:: ለምሳሌ፣ በአንድ የሽማግሌዎች ስብሰባ ላይ ገንዘብ ያዥ ተነሥቶ ባለፈው ወር በቤተ ክርስቲያኒቱ



ከተሰበሰበው አሥራትና መባ መቶ ብር እንደ ተገኘና 40 ብሩ ለሽማግሌዎች ወርሐዊ ስብሰባና ለጐብኚዎች ለምግብ እንደ ወጣና 40 ብሩ ደግሞ ለሽማግሌዎች ስብሰባ ለትራንስፖርት እንደ ወጣ ተናገረ እንበል:: «ለጌታ ሥራ» የቀረው 20 ብር ብቻ ነው:: ያ የእግዚአብሔርን ገንዘብ በጥሩ ሁኔታ አለመያዝ ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎች አብዛኛው ገንዘባቸው በዚህ መልክ እንደሚውል ሲያውቁ ምን ይፈጠራል? «ሽማግሌዎችን ለመመገብ ብቻ ለምን ገንዘባችንን እንሰጣለን?» ብለው በማለብ መስጠት ያቆማሉ:: ሰዎች ውድ የሆነውን ገንዘባቸውን ሽማግሌ ለመመገብ፣ ጐብኚዎችን ለመመገብና ለእነርሱ የትራንስፖርት ወጪ ለመክፈል እንዲውል አይፈልጉም:: ገንዘባቸውን የሚሰጡት ወንጌላውያን ወጥተው ወንጌልን እንዲያሰራጩ ወይም ቤተ ክ:ስቲያን እንድታድግ ለሚረዱ ግልጽ አገልግሎቶች ነው:: እንደ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ይህ የአባላትን ጥርጣሬ የሚያስወግድ ከሆነ፣ ለጌታ ሥራ ከኪሳችን አውጥተን የትራንስፖርት ብንከፍልና ያሰንንም ለጌታ ሥራ እንዳደረግነው አስተዋጽኦ ብንቆጥረው አይሻልም? ሰዎች ገንዘቡን በምግብ እንደ ጨረስነው ከሚያስቡ በወርሐዊው ስብሰባችን ላይ ብንጾም አይሻልም?

ግን እንግዶችን ስለ መቀበልስ? በእኛ ባህል ሊጐበኙን የመጡ ሰዎችን በጥሩ ሁኔታ መመገብ አስፈላጊ ነው:: ይህንን በተሰያየ መንገድ ልንይዘው እንችላለን:-

<u>አንደኛ፣</u> ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ባህሪ ውስጥ አንዱ ደግነትና እንግዳ ተቀባይነት እንደ ሆነ መመልከታችንን ታስታውሳለህ? ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ሽምግሌዎች እንግዶችን ማሳረፍና ምግባቸውን መቻልን እንደ አገልግሎታቸው ክፍል ሊያዩ ይገባል:: በቤተ ክርስቲያን አቅራቢያ በሚኖር ሽማግሌ ላይ ሸክሙን ከመጣል ይልቅ፣ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ የእንግዶችን ቀለብን በተመለከተ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱበትን መንገድ መፈለግ አለባቸው:: ሸክሙን ከተከፋፈልነው፣ በእያንዳንዱ ሰው ላይ

የሚደርሰው ትንሽ ነው።

<u>ሁለተኛ</u>፣ በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት፣ መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማስታወቂያ ያስነግራሉ። «በዚህ ሳምንት ሦስት እንግዶች ከቀጠና ጽ/ቤት ይመጣሉ። ሦስቱን እንግዶች በቤታችሁ በመቀበልና እዚህ በሚቆዩባቸው ሦስት ቀናት ምግባቸውን በመስጠት ጌታን ማገልገል የምትፈልጉ ሰዎች አላችሁ?» ብለው ይጠይቃሉ። ብዙ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አባላት እንግዶችን ለመቀበል ፍጹም ፈቃደኛ ስለሚሆኑ ደስ እያላቸው ነው ወደ ቤታቸው የሚወስዷቸው። በሌሎች ቤተ ክርስቲያናት፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አባላትን ሀ) ለእንግዶች መኝታና ምግብ ማቅረብ የሚፈልግ ማን ነው? ለ) ማን ነው ለጐብኚዎች ቁርስ የሚያዘጋጀው? ሐ) ማን ነው ምሳ የሚጋብዘው? ብለው ይጠይቃሉ። አባላትም እንግዶቹ ምን ጊዜ ወደ ቤታቸው መምጣት እንዳለባቸው ይናገራሉ። ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡ እንግዶችን የመቀበልን ሸክም ለቤተ ክርስቲያን አባላት ካካፈልናቸው ለአንድ ሰው አይከብደውም። ምንም እንኳን ለጐብኚዎች ምቹ ባይሆንም፣ ይህ አሠራር የቤተ ክርስቲያን አባላት የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በማወቅ ከእነርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲፈጥሩ ያደርጋል። ከብዙ ዓመታት በፊት ይህ ሲገጥመኝ፣ ከቤተ ሰቡ ጋር ለመተዋወቅና ስለ ልጆቻቸው ለመጠየቅ ቻልኩ። ይህ ግንኙነት በቤተ ክርስቲያን አባላትና ለጉብኝት በመጡ መሪዎች መካከል መተማመንን ይፈጥራል።

<u>ሦስተኛ</u>፣ ምናልባትም ይህንን ጉዳይ በግልጥ ወደ ቤተ ክርስቲያን ልናመጣው እንችላለን። እኛ ሽምግሌዎች ለእንግዶች ተገቢ ነው የምንለው ምግብ ምን ያህል እንደሚያወጣ ልንነግራቸው እንችላለን። ከዚያም ገንዘቡ ከእሥራቱና ከመባው ይውጣ ወይ ብለን እንጠይቃቸዋለን። ገንዘቡን በጥንቃቄ እንደምንጠቀምበት እናስረዳቸዋለን። (ለምሳሌ፡- የምግብ ወጪውን የምናወጣው ለእንግዳው እንጂ ለሌሎች ሽማግሌዎችና



ለቤተሰባቸው አለመሆኑን እንገልጥላቸዋለን።) ለዚያ ድጋፋቸውን ከሰጡ፣ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በአባላቱ መካከል ያላቸውን መልካም ዝና ይጠብቃሉ። የቤተ ክርስቲያናት አባላት ካልደገፉ፣ መልካም ዝናችንን ከምናበላሽ ወይም ሰዎች ገንዘብ መስጠት እንዲያቆሙ ከምናደርጋቸው ይልቅ፣ እንግዶችን የምንቀበልበትን መንገድ ማፈላለግ አለብን።

3) በእኛ ኃላፊነት የተሰጠንን ገንዘብ እንዴት እንደ ተጠቀምን ለቤተ ክርስቲያን አባላት በግልጽ ልንነግራቸው ይገባል። ሰዎች እውነቱን ካላወቁ፣ በጣም የባሰ ነገር ነው የሚጠራጠሩት። ሰዎች ገንዘባቸው በምን ሁኔታ ላይ ጥቅም ላይ እንደ ዋለ በግልጽ ካላወቁ፣ ትክክለኛ ባልሆነ ነገር ላይ እንደ ወጣ ያስባሉ። እንዲያውም፣ አብዛኛውን ጊዜ ሽማግሌዎች ገንዘቡን እንደ ሰረቁ ይገምታሉ። ምንም እንኳን እኛ ፍጹም ታማኝና ገንዘቡን የማንሰርቅ ብንሆንም፣ እንደዚያ ያስባሉ። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያንን የሥራና የገንዘብ እያያዝን በተመለከተ በየጊዜው (ምናልባትም በየሦስት ወሩ) ለቤተ ክርስቲያን ሪፖርት ማቅረቡ አስፈላጊ ነው። በዚያ ጊዜ ምን ያህል ገንዘብ ለቤተ ክርስቲያን በአሥራትና በመባ መልክ እንደ ሰጡ ልንነግራቸው ይገባል። ከዚያም ገንዘቡ በምን ላይ እንደ ዋለ ሪፖርት ልናደርግላቸው ይገባል። የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሊያደርጉ የሚፈልጉት (ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አስፈላጊ የሆነ ነገር) ነገር ግን በገንዘብ እጥረት ማድረግ ያልቻሉትንም ነገር መናገር ጥሩ ነው። ይሄ የቤተ ክርስቲያን አባላት በልግስና እንዲሰጡ ያበረታታል።

> 13ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁ ሽማግሌዎች ምን ያህል ገንዘብ እንደ ተሰበሰበና ምን ያህሉ ደግሞ በጥቅም ላይ እንደ ዋለ ሪፖርት ያቀርባሉ? ከሆነ፣ በየስንት ጊዜው? ካልሆነ፣ ለምን? ለ) የቤተ ክርስቲያን አባላት ምን ያህል ገንዘብ እንደ ወጣና ወይም አላግባብ የሆነ ወጪ እንደ ወጣ ወሬ ቢሰሙ እንዴት ጥርጣሬ ሊገባቸው እንደሚችል ግለጽ። በዚያ የተነሣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ይፈጠራል? ሐ) የቤተ ክርስቲያን አባላት እንዲያምኑና ጥርጣሬአቸው እንዲወገድ ለማድረግ የቤተ ክርስቲያንን ሪፖርት አቀራረብ እንዴት ነው የምናሻሽለው?

4) ገንዘቡ ለታሰበለት ዓላማ መዋል አለበት። አንዳንድ ጊዜ ለሰዎች ለተለየ ፕሮጀክት ገንዘብ እንዲሰጡ እንጠይቃለን። ያ ምናልባት ወንጌላውያንን ለአገልግሎት ለመላክ፣ የመዘምራን ቡድን የሚሆን ልብስ ለመግዛት፣ የሙዚቃ መሣሪያ ለመግዛት፣ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃን ለመገንባት፣ ወዘተ. . . ሊሆን ይችላል። እንደ መባና አሥራት ገንዘብ ሳይሆን፣ ይህ ገንዘብ ለታለመለት የተለየ ዓላማ ብቻ ነው የሚውለው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ገንዘቡ ለእነርሱ በኀላፊነት ስለ ተሰጠ ብቻ ቤተ ክርስቲያን ያስፈልጋታል ብለው በሚያስቡት ነገር ላይ ወጪ ሊያደርጉት እንደሚችሉ ሊያስቡ አይገባም። መሪዎቹ ገንዘቡን በእግዚአብሔር ፊት ለታለመለት ዓላማ የማዋል ግዴታ አለባቸው። ከአንድ ሰው ወይም ቡድን ለተለየ ዓላማ ገንዘብ ስንቀበል፣ ያንን ገንዘብ የተቀበልነው ለዚያ ዓላማ ልናውለው እንደምንችል ስለ ተረዱ ነው። ገንዘቡን የሰጡት ገንዘቡን የተቀበልነው ባልነው መሠረት ገንዘቡን እንደምናውለው ቃል በመግባታችን ነው። ነገር ግን ያንን ገንዘብ ለዚያ ዓላማ ስንቀበል ሌላ ችግር ሊከሰት ይችላል። ለምሳሌ፣ አባላት ለወንጌላውያን የሚያስፈልገውን ገንዘብ ይሰጡናል፣ እኛ የምንፈልገው ግን የመዘምራን ልብስ ይሆናል። ገንዘቡን ወስዶ የመዘምራን ቡድን ልብስ መግዛት ጥሩ ነውን? መልሱ አይደለም ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ቃላችንን የምንጠብቅ ሰዎች እንድንሆን ይናገረናል (ማቴ. 5:37)። ገንዘቡን ለአንድ ዓላማ እንጠቀማለን ብለን ከወሰድን፣ ቤተ ክርስቲያን ለሌላ ዓላማ ከፍተኛ የገንዘብ ችግር ቢገጥማት እንኳን በዚያ መንገድ ነው ልንጠቀምበት የሚገባው። እናደርጋለን ብለን ቃል ገብተን የወሰድነውን ገንዘብ በቃላችን መሠረት ካልተጠቀምን፣ ሕዝቡ በእኛ ላይ ያለውን መተማመን እናጣለን። ደግሞ የውሸት አካል ስለሆነ፣ በጣም ለሚያስፈልግ አገልግሎት ልናውለው አስበን ቢሆን እንኳን እግዚአብሔር አይባርከንም።

በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር ቢፈጠር ወይም የጠበቅነው



አገልግሎት ያሰብነውን ያህል ካልሄደልን፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን አባላት ወይም ገንዘቡን ወደ ሰጠን ሰው ሄደን ገንዘቡን ለሌላ ዓላማ ለማዋል ልናስፈቅደው ይገባል። መሪዎች እርስ በርስ ተሰብስበው ገንዘቡ የሚውልበትን መንገድ የሚለውጡ ከሆነ፣ ለአባላት ወይም ለእርዳታ ሰጪው የገቡትን ቃል አጥፈዋል ማለት ነው። አባላት ገንዘቡ ለሰጡለት ዓላማ እንዳልዋለ ከተረዱ፣ በሚቀጥለው ጊዜ ሽማግሌዎች ለሌላ ፕሮጀክት ገንዘብ ሲጠይቁ፣ ሰዎች አያምኗቸውም። አባላት በፈቃደኝነት አይሰጡም። የቤተ ክርስቲያን አባላት ላለባቸው የመስጠት ችግር ተጠያቂው የቤተ ክርስቲያን መሪው በሰዎች ዘንድ ያለውን ታማኝነት ባለመጠበቁ ነው።

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ቤተ ክርስቲያን ለተለያዩ ዓላማዎች ስላሰባሰበችው ገንዘብ ዘርዝር። ለ) ለዚያ ዓላማ ያስፈልግ የነበረው ገንዘብ ሁሉ በዚያ ላይ ውሏል ወይስ በሌሎች ነገሮች ላይ ውሏል? መልስህን አብራራ። ሐ) ሰዎች እነርሱ ላልፈለጉት ዓላማ ገንዘባቸው ሲውል በልግሥና የሚሰጡት ገንዘብ ምን ይሆናል? |

5) ለግል ጉዳዮች ፈጽሞ የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ ልንበደር አይገባም። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም የቤተ ክርስቲያን አባላት በእኛ ዘንድ በአደራ ያስቀመጡት ገንዘብ የእኛ ሳይሆን የእግዚአብሔር መሆኑን መረዳት አለብን። ይህ ገንዘብ ሰዎች ላም እንድንገዛበት፣ ቤት እንድንሠራበት፣ መኪና እንድንገዛበት፣ ወዘተ. . . ከባንክ እንደምንበደረው ዓይነት ገንዘብ አይደለም። ሊሆኑ የማይገባቸው ሁለት ነገሮች አሉ፡-

አንደኛ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪ ፈጽሞ ከቤተ ክርስቲያን ገንዘብ መበደር የለበትም። ሰይጣን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በጊዜ ሂደት ከሚያሸንፍባቸው መንገዶች አንዱ ያለ ፈቃድ ከቤተ ክርስቲያን ገንዘብ መበደር ነው። ለምሳሌ፣ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ያዥ ለቤቱ አዳዲስ ቆርቆሮዎች ያስፈልጉታል እንበል። በቂ ገንዘብ የለውም፣ ስለዚህ «ከሚቀጥሉት ሦስት ወራት ደመወዝ ላይ እከፍላለሁ» ብሎ በማሰብ በአደራ ከሚያስተዳድረው ገንዘብ ላይ

ይወስዳል። ነገር ግን ሁልጊዜ ደመወዝ ሲቀበል፣ ገንዘቡን በጣም አጣዳፊ ለሆኑ ነገሮች ይፈልገዋል። ትንሽ ቆይቶ ሒሳብ ገንዘቡን ባስታወሰው ቁጥር የተለያዩ ምክንያቶችን እየደረደረ ገንዘቡን መመለስ ያቆማል።

በመበደር የተጀመረው ነገር ወደ ስርቆት ያመራል። ይህ ሽማግሌ ገንዘቡን የሰረቀው ከሕዝቡ ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔርም ጭምር ነው። አንድ ጊዜ ለቤተ ክርስቲያን ከተሰጠ በኋላ የእግዚአብሔር ገንዘብ ነው። ከዚያ ገንዘብ ላይ አንዲት ሳንቲም የመውሰድ መብት የለንም። አንድ ቀን ኃጢአታችን ይደርስበታል። ያን ጊዜ የእኛ ዝና ከመበላሸቱ ሌላ፣ በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሁሉ ላይ ጥርጣሬአችን እንዲፈጠር ምክንያት እንሆናለን። ሰዎች አንድ ጊዜ መሪን ከተጠራጠሩ፣ መሪዎች የበፊቱን መልካም ዝናቸውን ማግኘት አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል። እምነት በሌለበት ሁኔታ፣ አባላት ለእግዚአብሔር ሥራ መስጠት ያቆማሉ። ሰይጣን አባላት አሥራታቸውን እንዳይሰጡ ያደርጋል፣ ያለ ገንዘብ ደግሞ የእግዚአብሔር ሥራ ይገደባል።

ሁለተኛ፣ ሽማግሌዎች ሌላ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ወይም የቤተ ክርስቲያን አባል ፈጽሞ ገንዘብ እንዲበደር ሊፈቅዱ አይገባም። ሰዎች ገንዘባቸውን ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጡት የመጣ ሁሉ ገንዘብ የሚበደርበት ባንክ ለማቋቋም አይደለም። ለእግዚአብሔር ሥራ እንጂ ሰዎች ገንዘብ ሊበደሩበት እንደሚችሉት እቁብ ሊቆጠር አይገባም። ከቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ስንበደር፣ ሰይጣን ያንን ቤተ ክርስቲያንን ለመደምሰስ ይጠቀምበታል። በመጀመሪያ፣ ሰዎች ገንዘብ ከቤተ ክርስቲያን ይወስዱና አይመልሱም። ስለዚህ ከእግዚአብሔር የሚሰርቁ ሌቦች ይሆናሉ። ያንን እንዲያደርጉ ደግሞ ፈቅደንላቸዋል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎቹ ገንዘቡን እንዲመልሱ ሊያደርጉ የሚችሉበት ምንም ዓይነት መንፈሳዊ መንገድ የላቸውም። ስለዚህ ሰይጣን ወንጌላውያንን ልናሰማራ የምንችልበትን ገንዘብ ወይም



ለመጋቢው ደመወዝ ልንከፍል የምንችለውን ገንዘብ እንድናጠፋ ያደርገናል። ሁለተኛ፣ መሪዎች ለብዙ ክስ እንዲጋለጡ በር ይከፍታል። «ለዘመድህ ገንዘብ ሰጥተሃል። ለእኔ ልትሰጠኝ ይገባል።» «ገንዘቡን ለምን ለዚያ ሰው ሰጠህ። መክፈል እንደማይችል ታውቃለህ።» የሚሉት ሊደርስባቸው ከሚችሉት ክሶች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው።

መሪው አንድ ሰው ገንዘብ ያስፈልገዋል ብሎ ካሰበ፣ የግል ገንዘቡን ነው ሊሰጥ የሚገባው። ወይም አማኞች ተሰብስበው ሰዎች ገንዘብ ሊበደሩ የሚችሉበት እቁብ ሊያቋቁሙ ይችላሉ። ነገር ግን ለእግዚአብሔር ከሚገባው ገንዘብ ላይ ፈጽሞ ሊበደሩ አይገባም።

6) አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ከመባው ገንዘብ ላይ ከሰረቀ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይፋ የሆነ የሥነ ሥርዓት እርምጃ መውሰድ አለባቸው። ከመባው ገንዘብ ላይ የሰረቁ ሰዎች ሲያዙ፣ በብዙ አንባ ነው «ንስሐ» የሚገቡት። በሽማግሌዎች ስብሰባ ላይ በሽማግሌዎች ፊት ወድቀው ነው ኃጢአታቸውን የሚናዘዙት። ሽማግሌዎች ከጠየቁ፣ በቤተ ክርስቲያን ፊት ወድቀው ኃጢአታቸውን ይናዘዛሉ። ነገር ግን ኃጢአታቸው ሳይጋለጥ በፊት ያንን አያደርጉም፣ ከተጋለጡ በኋላ እንጂ። ግን በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ፊት ለሠሩት ኃጢአት ንስሐ መግባታቸው ነው ወይስ በመያዛቸው የተነሣ እንዳይቀጡ የሚሰጡት ምላሽ ነው? ብዙ ጊዜ ንስሐው የእውነት መሆኑ ያጠራጥራል። በሚያስገርም ሁኔታ፣ ለውየው «ንስሐ» ማለት የሰረቁትን ገንዘብ አለመክፈል ይመስላቸዋል። «ይቅርታ አድርገንልሃል።» የሚሉ ሰዎች ካገኙ፣ ገንዘቡን መመለስ እንደሌለበት ያስባል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ይህንን አይደለም። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ንስሐ መግባት ምንድን ነው?

<u>አንደኛ</u>፣ መሪ የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ ከወሰደ፣ በሕዝብ ፊት ንስሐ መግባት አለበት። (1ኛ ጢሞ. 5:19-20ን ተመልከት።) እውነተኛ ንስሐ ማለት ሌሎች የሚያውቁትን ኃጢአት መናዘዝ

ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎች ሰዎች የማያውቁትንም ንስሐ መግባት ማለት ነው፡፡ ሽማግሌዎች ኃጢአት የሠራውን ሽማግሌ ዝና ለመጠበቅ ሲሞክሩ ኃጢአት ይስፋፋል፡፡ ሰዎች ሽማግሌዎቹ ለሠሩት ኃጢአት እንዳልተቀጡ የሚያስቡ ከሆነ፣ በሽማግሌዎች ላይ ያላቸው እምነት ይጠፋል፡፡ እንዲህ ያለ ኃጢአትን የሚሠሩ ሽማግሌዎች በይፋ ሊገለጡና ከቤተ ክርስቲያን ቢሮ ለተወሰነ ጊዜ ሊታገዱና በቤተ ክርስቲያን የሥነ ሥርዓት እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡ እንደዚያ ያለ ጥፋት የሠራ ሽማግሌ ወደ ሽምግልናው ሲመለስ፣ በሕዝብ ዘንድ ያለው አመኔታ እስኪስተካከል ድረስ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ደግሞ ሊቆጣጠር አይገባም፡፡ ወደ ገንዘብ ያዥነት ከተመለሰ፣ ሰዎች ገንዘባችንን እየሰረቀ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጥርጣሬያቸው ሁልጊዜ በአእምሮአቸው ይመላለሳል፡፡ ስለዚህ ነፃ ሆነው ለእግዚአብሔር ሥራ መስጠት ያቆማሉ (ማስታወሻ፡- ሽማግሌውን ለተወሰነ ጊዜ አገልግሎቱን እንዲያቆም ስንቀጣ፣ ሽማግሌዎች ሊያሳስበን የሚገባው ዋነኛው ነገር ለምን ያህል ጊዜ ያንን ሰው ልንቀጣው ይገባል የሚለው መሆን የለበትም፡፡ ይልቁንም፣ ሰዎች ከምን ያህል ጊዜ በኋላ ነው ሊያምኑት የሚገባው የሚለው መሆን አለበት፡፡ ደግሞ መታመን እስከሚችልና ራሱን መግዛት እስከሚለምድ ድረስ መሪ ለመሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መስፈርትን አያሟላም፡፡)

ጉዳዩን ከቤተ ክርስቲያን አባላት ምሥጢር አድርጐ ለመሰወር መሞከር ማለት ለምች ኃጢአት መዘዝ እንደሌለው እንዲማሩ ማስተማር ማለት ነው፡፡ ኃጢአት የሚፈራ ነገር ከመሆን ይልቅ እንደ ቀላል ነገር እንዲታይ ልናደርገው እንችላለን፡፡ ኃጢአቱን በወሬ የሚሰሙ ሰዎች ለሁሉም ሽማግሌዎች ያላቸው ክብር ይቀንሳል፡፡ ሌሎቹ ሽማግሌዎች ያላቸውን ታማኝነት የሚገልጡበት ብቸኛው መንገድ ሌላ ሽማግሌ ለሠራው ኃጢአት ሚዛናዊና ታማኝነትን በጠበቀ ሁኔታ ምላሽ ሲሰጡ ነው፡፡ የሽማግሌውንና የቤተሰቡን ቁጣ በመፍራት ዝም ካልን፣ ወይም በዚያ ሰው ላይ



ወይም በሽማግሌዎች ላይ ውርደትን ላለማምጣት ብለን ዝም ካልን በሕዝቡ መካከል በቅድስና እንድንመላለስ ከሚጠብቀው ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰዎችን እየፈራን ነው ማለት ነው፡፡

<u>ሁለተኛ</u>፣ እውነተኛ ንስሐ ከገባ፣ ሽማግሌው የሰረቀውን ገንዘብ በሙሉ ለመክፈል መዘጋጀት አለበት፡፡ ይህ በብሉይ ኪዳን ወቅት በጣም አስፈላጊ ስለነበረ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሲናገር የእነርሱ ሥራ ሌላውን ሰው ችግር ውስጥ የሚከት ከሆነ፣ የለውየው ገንዘብ ብቻ ሳይሆን በሰረቁት ገንዘብ ላይ 20% ጨምረው እንዲከፍሉ አዝዟል፡፡ ያን ጊዜ ብቻ ነው የይቅርታ መሥዋዕት ሊያቀርቡ የሚችሉት (ዘሌዋ. 6:1-7)፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር እውነተኛ ይቅርታ ለማድረግ ተግባራችንና ቃላችን አንድ እንዲሆን ይፈልጋል፡፡ ገንዘቡን እስኪመልስ ድረስ፣ ሽማግሌው «ሌባ» ነው፡፡ የእግዚአብሔር ገንዘብ ከሚጠፋ ይልቅ ሽማግሌው በችግር ቢጠበስ ይሻለዋል፡፡ ቤቱን፣ ላሞቹን፣ ፍየሎቹን፣ ቀለበቱን ወይም ሌሎቹን ሸጦ ስሕተቱን ማስተካከል መቻል አለበት፡፡ ሌሎች ሽማግሌዎች ገንዘቡን ለማስመለስ ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ ከእርሱ ጋር መሥራት አለባቸው፣ ነገር ግን የወሰዳትን እያንዳንዷን ሳንቲም ለመመለስ መወሰን አለበት፡፡ ሽማግሌው ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትን ለማግኘትና የልብ ቅንነቱ እንዲመለስ ለማድረግ፣ ገንዘቡን ለመመለስ መሥራት አለበት፡፡

እንደ ሽማግሌነታችን ብዙ ጊዜ ለሰውየው ይቅርታ አድርገንለት ገንዘቡን ለመተው እንፈተናለን፡፡ ነገር ግን ይህ ነገር በሦስት ምክንያቶች ትክክል አይደለም፡፡ <u>አንደኛ</u>፣ ገንዘቡ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አይደለም፡፡ ስለዚህ «ምንም አይደለም» ሊሉ አይችሉም፡፡ ገንዘቡ የእግዚአብሔርና የቤተ ክርስቲያን አባላት ነው፡፡ እግዚአብሔርን ስለ ገንዘቡ «ምንም አይደለም» ልንለው ስለማንችል፣ ገንዘቡን የሰረቁ ሰዎች ሊመልሱ ይገባል፡፡ <u>ሁለተኛ</u>፣ የቤቱን ጣራ ቆርቆሮ ለመሸፈን ወይም ላም በመግዛት የገንዘብን ጥቅም ለማግኘት የእግዚአብሔርን ገንዘብ ለሚሰርቀውም ትክክል

አይደለም። የእግዚአብሔር ሥራ ከሚጐዳ እርሱ ራሱ ቢጐዳ ይሻላል። <u>ሦስተኛ</u>፣ ገንዘቡን እንዲመልስ አለመጠየቅ ሌሎች ሰዎች ሰርቀው ገንዘቡን እንዳይመልሱ በማድረግ ያበረታታል። ለአንድ ሰው ከፈቀድን፣ ብዙዎች እንዲሰርቁና «ይቅርታ ይደረግልኝ» በማለት ራሳቸውን እንዲያገልሉ ያደርጋል።

ምናልባት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ያንን ሰው ገንዘቡን እንዳይከፍል ማድረግ የሚገባቸው ከቤተ ክርስቲያን የሰረቀውን ገንዘብ መመለሱ ቤሳ ቤስቲን የሚያሳጣውና ቤተሰቡን በረሃብ የሚጥል ከሆነ ብቻ ነው። የሽማግሌዎች ውሳኔ ያ ከሆነ፣ መወሰን ያለበት የቤተ ክርስቲያን አባላትን ሁሉ ካማከርን በኋላ ነው። ገንዘቡ ለቤተ ክርስቲያን ነው የሚገባው፣ ስለዚህ ኃጢአተኛውን ሰውዬ ገንዘቡን መክፈል አለበት የለበትም የሚለው ውሳኔ በቤተ ክርስቲያናቱ አባላት ትብብር ሊወሰን ይገባል።

(ማስታወሻ፡- በሌላ ሰው ላይ ኃጢአት ሠርቼ ሰውየው ይቅር እንዲለኝ ከፈለግሁ፣ መጥቼ ይቅርታ ልጠይቀው፣ ማለትም በልቡ ውስጥ በእኔ ላይ ያለውን ቁጣ እንዲያስወግድ ልጠይቀው ብቻ አይገባም። ነገር ግን የሠራሁትን ስሕተት ለማስተካከል የምችለውን ሁሉ ማድረግ አለብኝ። ያ ስሕተት ገንዘብ መስረቅ ከሆነ፣ ገንዘቡን መመለስ አለብኝ። በውሸት የሰውን ስም አጥፍቼ ከሆነ፣ ውሸት እንደ ተናገርኩ ለሌሎች በመናገር የሠራሁትን ስሕተት ማስተካከል አለብኝ። ስሕተቱን የሠራሁት እኔ በመሆኔ፣ የሠራሁትን ስሕተት ማስተካከል አለብኝ። ስሕተት የተፈጸመበት ሰው ደግሞ፣ ካለብኝ ግዴታ ነፃ ሊያወጣኝ ይችላል። «ምንም እንኳን 100 ብር ብትወስድብኝም፣ በቃ ትቼልሃለሁ። ለአንተ 100 ብሩን ትቼልሃለሁ» ሊለው ይችላል። ያን ጊዜ ብቻ ነው ኃጢአተኛው የወሰደውን ገንዘብ ከመመለስ ነፃ የሚወጣው። ከዚያ ውጪ ግን፣ የተሰረቀው ገንዘብ [ወይም ዕቃ] ሊመልስ ይገባል።)



| |
|---|
| 15ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሰው ከቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ተበደረ ሲባል ሰምተሃል ወይም አይተሃል? ምን ሆነ? ለ) ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ገንዘብ የሚበደሩበት ጊዜ አለ? ካለ፣ መቼ? ሐ) ወደ ዘመዶቻቸው ወይም ጓደኞቻቸው ከመሄድ ይልቅ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ አለባቸው ብለህ ታስባለህ? መ) የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ከቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ከወሰደ፣ በሕዝብ ፊት ሲገሠጽ የሚገባ ይመስልሃል? ገንዘቡን እንዲመልስ መጠየቅ ያለበት ይመስልሃል? መልስህን አብራራ። |

7) የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አሥራትና መባቸውን በመክፈል የልግስና ምሳሌዎች መሆን ይገባቸዋል። በቤተ ክርስቲያን ያለው አመራር ከመንግሥት ሥራ ወይም ንግድ በተለየ ሁኔታ በቀዳሚነት በማስተማርና የእግዚአብሔርን ቃል በመታዘዝ አርአያ በመሆን ላይ ያተኩራል። ይህ ማለት መሪዎች ለእግዚአብሔር በልግስና እንዲሰጡ አማኞችን ማበረታታት ከፈለጉ፣ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ለእግዚአብሔር የመስጠትን ደስታ ማሳየት አለባቸው። ለሌሎች ምሳሌ እንዲሆኑ በልግስና መስጠት አለባቸው። ለምሳሌ፣ አባላት ሁሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደመወዝ 700 ብር መሆኑን እያወቁ፣ ነገር ግን አንድ ብር ብቻ መባ ሲሰጡ የሚያዩዋቸው ከሆነ፣ አባላት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አሥራት መክፈል አለመክፈላቸው ያጠራጥራቸዋል። ሽማግሌው ምናልባት ለቤተ ክርስቲያን ቢሮ አሥራቱን ይሰጥ ይሆናል። ነገር ግን ሰዎች ያንን ስለማያውቁ ለእግዚአብሔር በልግስና መስጠትን ሳይማሩ ይቀራሉ። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ መሆናችን መጠን፣ ሌሎች የእኛን ምሳሌ እንዲከተሉ ገንዘብን በተመለከተ በልግስና እንደ መስጠት አለባቸው። ለምሳሌ፣ አባላት ሁሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደመወዝ 700 ብር መሆኑን እያወቁ፣ ነገር ግን አንድ ብር ብቻ መባ ሲሰጡ የሚያዩዋቸው ከሆነ፣ አባላት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አሥራት መክፈል አለመክፈላቸው ያጠራጥራቸዋል። ሽማግሌው ምናልባት ለቤተ ክርስቲያን ቢሮ አሥራቱን ይሰጥ ይሆናል፣ ነገር ግን ሰዎች ያንን ስለማያውቁ ለእግዚአብሔር በልግስና መስጠትን ሳይማሩ ይቀራሉ።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ መሆናችን መጠን፣ ሌሎች የእኛን ምሳሌ እንዲከተሉ ገንዘብን በተመለከተ በልግስና እንደምንሰጥ ማሳየት አለብን:: አስፈላጊ የሆኑ ሦስት እውነቶችን ልናስታውስ ይገባል:-

ሀ) አሥራትና መባችንን ስንሰጥ፣ በሰዎች መካከል ፉክክርን በሚፈጥር ወይም ለሰዎች ክብርን በሚሰጥ መንገድ ልናደርገው አይገባም:: ኢየሱስ ቀኝህ ሲሰጥ ግራህ አይወቅ ብሎ ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል (ማቴ. 6:2-4):: ይህንን ሲል አሥራትና መባን ስንሰጥ ለታይታ ከምናደርገው ይልቅ በምሥጢር ልናደርገው እንደሚገባ መግለጡ ነው:: ይህ ትምህርት በሕዝብ ፊት ለቤተ ክርስቲያን የሰጡ ሰዎችን ስም ዝርዝር ለሚያነቡ ሰዎች ማስጠንቀቂያ ነው:: ሰዎች በመስጠት እንዲፎካከሩ ማድረግንም ይቃወማል:: «አቶ ዮሐንስ ይህን ያህል መጠን ያለው ገንዘብ ሰጥተዋል:: እርስዎ ምን ያህል ይሰጣሉ?» የሚለው አባባል የእግዚአብሔር ቃል የሚፈቅደው አይደለም:: ሆኖም፣ ምን ያህል ገንዘብ እንደ ሰጡ ለማሳየት ሳይሆን፣ ሰዎች ከመሪዎቻቸው በልግስና መስጠትን እንዲማሩ ካስፈለገ፣ መሪዎች በልግስና እየሰጡ እንደ ሆነ ማወቅ አለባቸው::

ለ) በልግስና የመስጠት አስተሳሰባችንን ለመጠበቅ በገንዘብ ላይ ያለንን አመለካከት ልናጤን ይገባል:: መጽሐፍ ቅዱስ ገንዘብን መውደድ ልክ እንደ አረም በቀላሉ ልባችንን ሊወርር እንደሚችል ያሳያል:: ስለዚህ ባሎች፣ ሚስቶች፣ ተማሪዎች፣ ሌሎችም ሁሉ በቸርነት የመስጠትን አስተሳሰብ ማዳበር አለባቸው::

ሐ) ብዙ ይኑረን ወይም ትንሽ የሚያሳስብ አይደለም፣ ነገር ግን አማኞች ሁሉ እግዚአብሔር ከሰጣቸው ገንዘብ ላይ በልግስና መስጠት አለባቸው:: ሰይጣን የተሻለ ገንዘብ እስከምናገኝ ድረስ የምንሰጠውን ገንዘብ ለሌላ ጊዜ እንድናስተላልፍ ያደርገናል:: ተማሪዎች ድሃ ስለሆኑ ከኪስ ገንዘባቸው ለእግዚአብሔር አሥራትና መባ መክፈል የሌለባቸው ይመስላቸዋል:: ነገር ግን ያኔ በልግስና



መስጠትን ካልተማሩ፣ ሥራ ካገኙ ወይም ከገቡ በኋላ አሥራት አይከፍሉም:: ሰይጣን ሁልጊዜ ለእግዚአብሔር መስጠት እንደሌለብን ሊያሳምነን ስለሚሞክር፣ አሁኑኑ መስጠትን ልንማር ይገባል:: ሰድሆችም ድሃ ስለሆኑ ከኪስ ገንዘባቸው መስጠት እንደሌለባቸው ልንነግራቸው አይገባም:: «ገንዘብ የሌላቸውም መስጠት እንዲችሉ ገንዘብ ስጣቸው» ብለን ስንጸልይ፣ ሰዎች ድሃ ስለሆንኩ መስጠት የለብኝም ብለው እንዲያስቡ እያበረታታናቸው ነው:: እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ላሉት ሁሉ በቂ ገንዘብ ወይም ለዚያ ሳምንት የሚበቃ እህል ሰጥቷቸዋል:: ለእግዚአብሔር ያላቸውን ምስጋና ለማሳየት መባቸው ምንም ያህል ጥቂት ቢሆን እንኳን ለእግዚአብሔር መስጠት እንዳለባቸው ነው ልናስተምራቸው የሚገባው:: ኢየሱስ ሁለት ሳንቲም የሰጠችውን ጋለሞታ ሴትዮ አክብሯል:: ገንዘቡን አጠራቅማ ለራሷ እንድትጠቀምበት አላበረታታትም (ሉቃ. 21:1-4)::

መ) አዲስ ኪዳን 10 % የሚሆነውን ገቢያችንን አሥራት እንድናወጣለት የማይናገር በመሆኑ፣ ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ለመታዘዝ እንደሚያስፈልግ አድርገው አያስቡትም:: ኢየሱስ ግን በግልጽ አሥራት መክፈልን ያበረታታል (ሉቃ. 11:42):: ነገር ግን የአዲስ ኪዳን ትኩረት በልግስና ላይ ነው (2ኛ ቆሮ. 9:6-15):: በልግስና መስጠት የሚለካው የሰጠነው ገንዘብ እኛን ምን ያህል ይጐዳናል በሚለው ነው:: ስለዚህ ኢየሱስ ሁለት ብር የሰጠ ድሃ 100 ብር ከሰጠ ሃብታም ይበልጣል ነው የሚለው (ማር. 12:41-44):: ለሃብታም ሰው፣ 10 % መስጠት በልግስና መስጠት አይደለም:: በወር 1000 ብር ባገኝ፣ 100 ብሩን መስጠት ብዙ አይጐዳኝም:: በልግስና መስጠት ከዚያ በላይ መስጠት እንድችል ያደርገኛል:: ነገር ግን በወር 200 ብር የሚያገኝ ድሃ 10 %ቱን ማለትም 20 ብሩን ቢሰጥ ይበልጥ ይጐዳዋል:: ስለዚህ እርሱ በልግስና ሰጥቷል:: እግዚአብሔር የምንሰጥበትም አመለካከት ያሳስበዋል:: ያለ አሳብ በግድ የሰሸነት ከሰጠን፣ የሰጠነው

ለእግዚአብሔር ካለን ፍቅር፣ ለእኛ ስላደረገው ነገር ምስጋና፣ ወዘተ. . . አይደለም ማለት ነው። እግዚአብሔር የሚፈልገው ይህንን አይደለም።

10% መስጠት ከእኛ የሚጠበቀው ዝቅተኛው ገንዘብ ይመስላል። በልግስና መስጠት ማለት ከዝቅተኛው የበለጠ መስጠት ነው። ምናልባትም አሥራት የተሰጠን በቀዳሚነት በልባችን ውስጥ የገንዘብ ፍቅር መኖር አለመኖሩን ለመለካት ነው። ያም የለውነታችንን ሙቀት እንደሚለካው ቴርሞ ሜትር ነው። ከገቢያችን ላይ ቢያንስ 10%ቱን የማንሰጥ ከሆነ፣ ምንም ያህል የበዛ ወይም ያነሰ ገንዘብ ቢኖረን፣ የገንዘብ ፍቅር በልባችን ውስጥ ሊኖር የሚችልበት ዕድል የሰፋ ነው።

እንዳለመታደል ሆኖ፣ ለእግዚአብሔር ሥራ በልግስና የማይሰጡ ብዙ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች አሉ። ስለ አሥራት ይሰብካሉ፣ ሰዎች አስራት እንዲከፍሉ ያበረታታሉ፣ ነገር ግን ራሳቸው ለእግዚአብሔር ሥራ አይሰጡም። ለዚህ ግብዝነታቸው እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል። እኛ አሥራት የማንከፍል ከሆነ እንዴት ሰዎች አሥራት እንዲከፍሉ እንጠብቃለን?

8) መሪዎች የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ በተመለከተ ሙሉ በሙሉ ታማኝ መሆን አለባቸው። የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ በተመለከተ በቀላሉ ግድ የለሽ ልንሆን እንችላለን። አብዛኛውን ጊዜ ደረሰኝ የሌላቸውን ነገሮች እንገዛለን። ለምሳሌ፣ ለተጋባዥ ለባኪው የሆቴል ምሳ እንጋብዛለን። ለሁለት ሰው የሚሆን ምሳ ከቡና ጋር ብር 11:50 ይፈጃል። ሆኖም፣ የወጪ ሪፖርት ስናቀርብ፣ ለምሳ 12 ብር እንዳወጣን እንናገራለን። 50 ሳንቲም ሰረቅን ማለት ነው። ያዕቆብ እንዳለው «ሕግ ተላላፊዎች» ሆነናል (ያዕ. 2:8-11)። ገንዘቡ ብዙ (100 ብር) ይሁን ወይም ጥቂት (50 ሳንቲም) የምንወስድ ከሆነ፣ ሌቦች ነን። ከቤተ ክርስቲያንና ከእግዚአብሔር ሰርቀናል ማለት ነው። ሰይጣን «እነርሱ ግድ አይሰጣቸውም፣ አባክህ ይህንን



ያህል ሥራ ስለ ሠራህ ይገባሃል» ብሎ ሳንቲሙን ለራስህ እንድታስቀር ሲፈታተንህ ተጠንቀቅ። እንደዚያ ያለው አመለካከት ወደ ኃጢአት በደል የሚገፋና በስተመጨረሻም የመሪውን ዝና የሚጎዳ ነው። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲያውም ገንዘብ ለማግኘት ባለ ሱቆችን በደረሰኙ ላይ ትንሽ ገንዘብ ጨምረው እንዲጽፉላቸው ይጠይቃሉ። ይህ ደግሞ ሌላ የሌብነት መንገድ ነው።

9) መሪዎች የግል ገንዘባቸውን እንዴት እንደሚጠቀሙ መጠንቀቅ አለባቸው። አስታውስ፣ የሚያስጨንቀን ኃጢአት ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ሰዎች የእኛን ቅንነት በተመለከተ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዳይዙም ነው። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ መሆናችን መጠን፣ የግል ገንዘባችንንም ሆ፣ የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ እንዴት እንደምንጠቀም ልንጠነቀቅ ይገባል። አንድ ሰው የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ያዥ ሆኖ ተመረጠ እንበል፤ ከወር በኋላ ዘመናዊ የሆነ የቆርቆሮ ክዳን ያለው ቤት መገንባት ጀመረ። ሰዎች ምን ሊገምቱ ይችላሉ? ሊገምቱ የሚችሉት ሰውየው ከቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ላይ ወስዶ የጣራ ቆርቆሮ እንደ ገዛ ነው። ከዚያ የተነሣ እርሱ ያለው የታማኝነት ዝና በጥያቄ ላይ ይወድቃል። ሰውየው ምንም ዓይነት ገንዘብ ከቤተ ክርስቲያን ላይወስድ ይችላል። ምናልባትም ለአዲስ ቤቱ የሚሆን የጣራ ቆርቆሮ ለመግዛት ለዓመታት ገንዘብ አጠራቅሞ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ያሉ ሰዎች ያንን ስለማያውቁ፣ በዚያ ጊዜ መገንባት በመጀመሩ ዝናው ይጎድፋል። ቤቱን ከመገንባቱ በፊት ገንዘብ እያያዙን በተመለከተ ተአማኒነትን ማዳበር ወይም የሚገነባው በራሱ ገንዘብ እንደ ሆነ በሆነ መንገድ ማሳወቁ አስፈላጊ ነው። በራሳችን ገንዘብ በመግዛት ዝናችንን ከማጉደፍ ይልቅ የቤት ግንባታውን በማዘግየት፣ በሬዎችን ወይም በጎችን መግዛቱን ለሌላ ጊዜ በማስተላለፍ መልካም ስሙን ቢጠብቅ ይሻለዋል። ጥበበ መሪ እንደ መሆናችን መጠን የምናደርገው ነገር ስሕተት እንደ ሆነ